# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 82ኛ ዓመት ቁጥር 032 ጥቅምት 2 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# የሳይበር ደህንነት የብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ በመሆኑ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶታል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የሳይበር ደህንነት የብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ በመሆኑ ከቴክኖሎጂ ልማቱ እኩል ለደህንነቱም ትኩረት ተሰጥቷል ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን አስታወቁ፡፡

"የተቀናጀ የሳይበር ደህንነት ለሀገር ሉዓላዊነት" በሚል መሪ ቃል የሚከበረው የሳይበር ደህንነት ወር በትናንትናው ዕለት በይፋ ተከፍቷል፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን የሳይበር ደህንነት ወር ዝግጅትን በይፋ ሲከፍቱ፤ የዲጂታል ኢትዮጵያ መርሃ ግብር በብዙ ዘርፎች ላይ መተግበር ላይ መሆኑን አንስተው የ2025 ዲጂታል ኢትዮጵያን ራዕይ ለማሳካት ከቴክኖሎጂ ልማቱ እኩል ለሳይበር ደህንነትም ትኩረት ይሰጣል ብለዋል፡፡

መንግሥት የሳይበር ደህንነትን ማስጠበቅ ቁልፍ የብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ አድርጎ እየሠራበት ይገኛል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ሳይበር ቴክኖሎጂ ለኢትዮጵያ ዕድገት ስኬት ዋነኛ አውታር መሆኑን በመረዳት ከ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ከዋና ዋና ስትራቴጂክ የትኩረት መስኮች መካከል አንዱ ተደርጎ በመሠራት ላይ ይገኛል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

የሳይበር ጥቃት የዓለማችን የወቅቱ የሥጋት ምንጮች ከሚባሉት አንገብጋቢ ጉዳዮች መካከል አንዱ እንደሆነ የጠቆሙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህን በማገናዘብም ነው መንግሥት የሳይበር ደህንነትን ማስጠበቅ ቁልፍ የብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ አድርጎ እየሠራበት የሚገኘው ብለዋል፡፡

በሳይበሩ ዘርፍ የሀገሪቱ የመወዳደር አቅምና ተስፋ በታዳጊ ወጣቶች ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ በኢንፎርሜሽን

የሳይበር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - በሃይሽ አብርሃ

3ኛው አገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር የመክፈቻ መርሐግብር








## አንዳንድ የምዕራባውያን ሀገራት ተጽዕኖ የሚፈጥሩት በትህነግ በኩል ያገኙ የነበረው ጥቅም እንዳይቀር ነው"

- ጋዜጠኛና ደራሲ ጥበቡ በለጠ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- አንዳንድ የምዕራባውያን ሀገራት በኢትዮጵያ የሚዲያ ተጽዕኖ የሚፈጥሩት በአሸባሪው ትህነግ በኩል የሚያገኙት ጥቅም እንዳይቀር ነው ሲል ጋዜጠኛና ደራሲ ጥበቡ በለጠ ገለጸ።

አንዳንድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ግብርና ሚኒስቴር ለመከላከያ ሠራዊት ከ80 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አደረገ

## - ስንዴን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ዝግጅቱ እየተጠናቀቀ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የግብርና ሚኒስቴርና በስሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት ለመከላከያ ሠራዊት ከ80 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አደረጉ። ሚኒስቴሩ ስንዴን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ዝግጅቱን እያጠናቀቀ መሆኑን አስታውቋል፡፡

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ፕሮፌሰር ኢያሱ ኤሊያስ እንደገለጹት፤ የግብርና ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት ለሠራዊቱ ያላቸውን አጋርነት ለማሳየት ከ80 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ በቀጣይም የሚደረገው ሁለንተናዊ ድጋፍ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ለሰላም የዘረጋችውን እጅ በመግፋት የወረረው አሸባሪው ቡድን በመከላከያ ሰራዊት በብቃት እየተመከተና አኩሪ ድል እየተመዘገበ በመሆኑ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሠራዊቱን በመደገፍ እያደረገው ያለው ርብርብ በየተሰማራባቸው መስኮች በመድገም ለአገር ሠላም መከበር የድርሻውን

ግብርና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ወረዳው ለውጭ ገበያ የሚቀርብ 50 ሺ ኩንታል ስንዴ ለማምረት እየሰራ ነው

**አስቴር ኤልያስ**

ኢተያ፡- በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን የሔጦሳ ወረዳ አርሶ አደሮች የግብርና ስራቸውን ማዘመን እና ጸረ አረምና ጸረ ፈንገስ ኬሚካል በአግባቡ መጠቀም በመቻላቸው በ2014/2015 የምርት ዘመን ለውጭ ገበያ የሚቀርብ 50 ሺ ኩንታል ስንዴ ለማምረት መዘጋጀታቸውን የወረዳው ግብርና ጽህፈት ቤት አስታወቀ፡፡

ወረዳው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






ምክር ቤቱ በዚህ ዓመት ስድስት የማንነት ጥያቄዎችን ለመፍታት አቅዷል



ገጽ 3

# በአሜሪካ ለተፈናቃይ ወገኖች ድጋፍ የሚውል ከ65 ሺ ዶላር በላይ ተሰበሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአሜሪካ ሎስ አንጀለስ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ክስተቶች ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ የሚውል ከ65ሺ. ዶላር በላይ ተሰበሰበ።

አምባሳደር ስለሺ በቀለ በሎስ አንጀለስና አካባቢው ከተሞች ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ጋር ሲወያዩ እንደገለጹት፤ኢትዮጵያ ለህዝቧ የምትመች፣ ሰላም የሰፈነባት እና አንድነቷ የተጠበቀ ሀገር ሆና እንድትቀጥል በመንግስት በኩል ሰፊ እርምጃዎች እየተወሰዱ ናቸው። በመንግስት በኩል ያለውን ቁርጠኛ የሰላም ማስፈን አቋም በመጻረር አሸባሪው ሕወሓት ሶስተኛ ዙር ወረራ በመፈጸም የቆየ የህዝብ ጠላትነቱን አሳይቷልም ብለዋል።

በሎስ አንጀለስ እና አካባቢው የሚገኙ የዳያስፖራ ወገኖችም በዚህ ቡድን የፕሮፖጋንዳ ክንፍ የሚነዛውን የሀገር ስም የማጠልሸት ዘመቻ እና አላስፈላጊ ጫና እንዲደረግ የሚያደርገውን አፍራሽ ተግባር በተቀናጀ ጥረት እንዲያከሽፉም ጥሪ አቅርበዋል።

ባለፉት አራት ዓመታት የዲሞክራሲያዊ ስርዓት እና ተቋማት ግንባታ፣ የአረንጓዴ አሻራ፣ የተቀናጀ የግብርና ምርት ማሳደግ፣ የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን የማጠናቀቅ ብሎም አዳዲሶችን በማስጀመር ረገድ አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል።

በሎስ አንጀለስና አካባቢው ብሎም በመላው አሜሪካ የሚኖረው ዳያስፖራ እናት ሀገሩ ላቀረበችው ጥሪ ሁሉ ፈጥኖ በመድረስ ለሚያሳየው አለኝታነትም ምስጋና አቅርበዋል።

በአሁኑ ወቅት የአሸባሪው ሕወሓት በፈጠረው ወረራ እና ተፈጥሯዊ ክስተቶች ሳቢያ በርካታ ኢትዮጵያውያን ለችግር መጋለጣቸውን በማንሳት ዳያስፖራው እንደሁልጊዜው ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል አምባሳደር ስለሺ ጠይቀዋል።

በተሳታፊዎች በኩል ደግሞ "ያለአግባብ" የሚፈጸም የግለሰቦች እስር፣ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚከሰቱ የንጹሃን ግድያና መፈናቀል፣ የኤምባሲው አገልግሎት አሰጣጥ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ጥያቄዎች አንስተው ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል።


አምባሳደር ስለሺ በቀለ

ኤምባሲው ወቅቱን የሚመጥን በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት ለመስጠት ሰፊ ማሻሻያዎችን እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

በእለቱ በሀገራችን በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ክስተቶች ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ የሚውል ከ65ሺ. ዶላር በላይ ለማሰባሰብ ተችሏል።

ተሳታፊዎቹም የሕወሓትን ፕሮፖጋንዳ በማክሸፍ እንዲሁም ድጋፍ የሚሹ ወገኖችን በመርዳት ረገድ የሚያደርጉትን አኩሪ ተግባር በበለጠ ተነሳሽነት እንደሚገፉበት አስታውቀዋል።

በሎስ አንጀለስና አካባቢው ብሎም በመላው አሜሪካ የሚኖረው ዳያስፖራ እናት ሀገሩ ላቀረበችው ጥሪ ሁሉ ፈጥኖ በመድረስ ለሚያሳየው አለኝታነትም ምስጋና መቅረቡን ከኤምባሲው የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

# የትምህርት ሚኒስትሩ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ አደጋ የደረሰባቸውን ተማሪዎች ጎበኙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ከትናንት በስቲያ አደጋ የደረሰባቸውን በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሚፈተኑ የ12ኛ ክፍል ተፈታኞች በሀዋሳ ሪፈራል ሆስፒታል በመገኘት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ጠይቀዋል::

ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ "አሁን ዋናው የእናንተ ማገገም ነው፤ ለፈተናው አትጨነቁ" ብለዋል፤ የተጎዱ ተማሪዎች በጤንነታቸው ዙሪያ እንዲያተኩሩም መክረዋል:: በአደጋው ህይወቱ ላለፈው ተማሪም የተሰማቸውን ከፍተኛ ሀዘን ገልጸው፤ ለተማሪው ወላጆች እና ቤተሰቦች መጽናናትን ተመኝተዋል::

በደረሰው ጉዳት እንደ አገር እናዝናለን፤ ነገር ግን ሂደቱ የፈተና ስርዓቱ ከስርቆት ተጠብቆ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት ውጤታማ እንዲሆኑ እና የተሻለች አገር የመገንባት በመሆኑ በዚህ ተስፋ መቁረጥ የለብንም ብለዋል:: ወላጆችም ይህንን ተረድተው ከትምህርት ማህበረሰቡ ጋር በጋራ እንዲቆሙ ጠይቀዋል::

ሚኒስትሩ፣ የተከሰተው የድልድይ መደርመስ አደጋ ወደ ከፋ ደረጃ እንዳይሸጋገር ተማሪዎቹን ለማዳን ለተረባረቡ የጤና ተቋማት፣ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ እና የአካባቢው ነዋሪዎች ምስጋና አቅርበዋል::

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከትናንት በስቲያ በደረሰው አደጋ ምክንያት ተቋርጦ የነበረው ፈተና ትናንት የተጀመረ ሲሆን፤ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የፈተና አሰጣጡንም በአካል በመገኘት ተመልክተዋል::

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከትናንት በስቲያ ዋናውን ከቴክኖሎጂ ግቢ የሚያገናኝ የመሸጋገሪያ ድልድይ ባጋጠመው የመደርመስ አደጋ ምክንያት ፈተናው መቋረጡ ይታወሳል።


ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ለ2014 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ከ42 ሺህ በላይ ተማሪዎች የተመደቡ ሲሆን በመጀመሪያ ዙር በማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ የተመደቡ ከ34 ሺህ በላይ ተማሪዎች በሰባት ማዕከላት ፈተናውን እየወሰዱ እንደሚገኙ ኢዜአ ዘግቧል።

# ክልሉ በ2015 ከ75 ሺህ በላይ የውጭ ቱሪስቶችን ለመሳብ እየሰራ ነው

**ኃይሉ ሣህለድንግል**



ሳውላ፡- በተያዘው 2015 በጀት አመት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በቱሪዝም ዘርፍ ከ75 ሺ. በላይ የውጭ ቱሪስቶችን ለመሳብ በትኩረት እየሰራ መሆኑን የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይለማርያም ተስፋዬ በክልሉ የአለም ቱሪዝምን ቀን ‹‹ቱሪዝምና አዲስ እሳቤ›› በሚል መሪ ቃል ለ28ኛ ጊዜ በክልል ደረጃ ከትናንት በስቲያ የማዜ ብሄራዊ ፓርክን በመጎብኘት በተጀመረበት ወቅት እንዳሉት፤ የቱሪዝም ዘርፉ እንደ ሀገር ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን፣ የማስተዋወቁ ስራ ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድ ይሆናል፡፡

የአለም የቱሪዝም ቀን ዘንድሮ ‹‹ቱሪዝምና አዲስ እሳቤ›› በሚል የሚከበረው በዋናነት የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎችን በደንብ በማስተዋወቅና በማልማት የቱሪስቱን ቆይታ የሚያራዝሙ ተግባሮችን ለማከናወን እንደሆነም ተጠቁሟል፡፡

የቢሮ ኃላፊው የሀገሪቱም ይሁን የክልሉ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ታሪኮች ለቱሪዝሙ ዘርፍ ትልቅ አቅም ናቸው፤ በተጠናቀቀው መስከረም ወር የክልሉ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ያከበሩት የዘመን መለወጫ በአልን ከበአል በፊትና እስከ በአሉ ያሉትን ዝግጅቶች በደንብ በማስተዋወቅ ቱሪስቱን ከአንድ ወር በላይ ማቆየት እንደሚቻል ሂደቶቹ አመላክተዋል ሲሉ ጠቅሰዋል፡፡

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በክልሉ የቱሪስት መስህብ ስፍራዎች ላይ ጉብኝቶች ተደርገዋል፤ በጉብኝቱ ከተካተቱት ውስጥ በቅርቡ በዩኒስኮ እንደሚመዘገብ የሚጠበቀው የጌዲኦው ጥምር ግብርና ትልቅ የቱሪስት መስህብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፤ በአለም ቅርስነት የተመዘገቡት ኮንሶና የጢያ ትክል ድንጋይም ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፤ ሌሎችም እንደ ጊፋታ ያሉትን ባህላዊ ሁነቶችም የቱሪስት መስህብ በመሆን ጎልተው ሊወጡ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ሁነቶች በዩኔስኮ እንዲመዘገቡ ለማድረግ እንደሚሰራም ገልጸዋል፡፡

የኮቪድ ስጋት እየቀነሰ መምጣቱ እና በክልሉ ያለው ሰላም ለክልሉ ቱሪዝም እንቅስቃሴ ይበልጥ መነቃቃት ጉልህ ሚና እንደሚኖራቸው ጠቁመው፤ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክልል ያለው ችግር በሰላማዊ መንገድ ከተቋጨም ከቱሪዝሙ ዘርፍ የተሻለ ስራ እንደሚጠበቅ ጠቁመዋል፡፡

ባለፈው አመት 29 ሺ. የሚሆኑ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ክልሉን መጎብኘታቸውን ጠቅሰው፣ በዚህ አመትም እንደሚቀንስ የሚጠበቀው የኮቪድ ተጽእኖና በክልሉ ያለው ሰላም ክልሉ ለቱሪስቶች አንዱ ተመራጭ አካባቢ እንደሚሆን የሚጠበቅ መሆኑን አስታውቀዋል፤ ይህንንም ታሳቢ ያደረገ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የቱሪስት መስህቦችን አልምተን ማስተዋወቅ ከተቻለ በተያዘው በጀት አመት ወደ ሀገሪቱ የሚመጡ ቱሪስቶች ቁጥር ከ75 ሺ. በላይ ለማድረስ እየሰራን ነው ያሉት አቶ ኃይለማርያም፣ እንዲህ አይነቱ ዘርፉን የማስተዋወቅና ሚዲያዎችን ለዚህ አላማ የመጠቀም አቅጣጫ ለእዚህ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በማዜ ብሄራዊ ፓርክም የመንገድ፣ የውሃ ልማት ስራዎች እንዲሁም የእንግዳ መቀበያዎች ለመገንባት የተጀማመሩ ስራዎች እንዳሉም ገልጸዋል፡፡ ይህን በማጠናከር አካባቢውን የቱሪስት ማእከል እንዲሆን የሚሰራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የጋሞ ዞን አስተዳዳሪ ዶክተር ጌትነት በጋሻው በበኩላቸው እንዳሉት፤ ከለውጡ በፊት ለዘርፉ ትኩረት ባለመሰጠቱ በተለይ የጋሞ ዞን በተፈለገው ደረጃ ባለመልማቱና ባለመተዋወቁ ህዝቡ ከዘርፉ ተጠቃሚ ሳይሆን ቆይቷል፡፡ በቀጣይ በጥናት የተለዩ የዞኑን የቱሪስት መስህቦች በማስተዋወቅ የኢኮኖሚ ምንጭ እንዲሆኑ ለማድረግ ሰፊ ስራ ይሰራል፡፡

የቱሪዝም ልማት ሰፊ መሰረተ ልማቶችን እንደሚጠይቅ ጠቅሰው፤ በዚህም ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉ ለማድረግ እየተሰራ ነው ሲሉ ዶክተር ጌትነት ተናግረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የሆቴል አገልግሎቶች እንዲስፋፉና እንዲሳለጡ የመንገድ መሰረተ ልማቶችም እንዲሻሻሉ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የማዜ ብሄራዊ ፓርክ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ መስፍን ቸርነት ፓርኩ ገና እየተዋወቀ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የጎብኚዎች ቁጥር ብዙ የሚባል እንዳልሆነ ጠቅሰው፤ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች የራሳቸውን ፓርክ በመጎብኘት በኩል ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ቱሪስቶች ፓርኩን እንዲጎበኙ የሚዲያ አካላት ሚና ከፍተኛ መሆኑን አመልክተው፤ በተለይ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ፓርኩን እንዲጎበኙ ማድረግ ላይ መሰራት እንዳለበትም አስገንዝበዋል፡፡

አቶ መስፍን እንዳሉት ፤ ፓርኩ ብሄራዊ ፓርክ የሆነበት ምክንያት በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኘው ስዊስ ቆርኬ መገኛ በመሆኑ ነው፡፡ በፓርኩ ውስጥ 39 አጥቢ የዱር እንስሳት መገኛ ነው፡፡ የቆላ አጋዘን ፣ደፋርሳ፣ አንበሳና አቦሸማኔ በብዛት የሚታዩበት ነው፡፡ ወደ 202 ስኩዌይር ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋትም አለው፡፡

የአለም ቱሪዝም ቀን በክልሉ ከመስከረም 30 እስከ ጥቅምት 3 ቀን 2015 እየተከበረ ነው፤ ቀኑ ከትናንት በስቲያ በክልሉ በሚገኘው ማዜ ብሄራዊ ፓርክ ጉብኝት በማድረግ ተጀምሯል፡፡ በዛሬው እለትም ሲፖዚየም እንደሚካሄድ ታውቋል፡፡ በማዜ ፓርክ በተደረገው ጉብኝት የክልሉ ባህልና ቱሪዝም እንዲሁም የጋሞ ዞን የስራ ኃላፊዎችና ከየዞኑ የተወከሉ የባህልና ቱሪዝም ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ተሳትፈዋል፡፡

ዜና



ወይዘሮ መዓዛ አሸናፊ

# በክረምቱ የእረፍት ጊዜ ከሁለት ሺህ 200 በላይ መዛግብት እልባት አግኝተዋል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች በክረምቱ የእረፍት ጊዜ ከ2 ሺህ 200 በላይ መዛግብት የውሳኔ እልባት እንዲያገኙ ማድረጋቸውን የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መዓዛ አሸናፊ ተናገሩ።

በእረፍት ምክንያት ለሁለት ወራት ዝግ ሆኖ የቆየው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አገልግሎት የፌዴራል የመጀመሪያ፣ የከፍተኛና የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች በተገኙበት ትናንት በይፋ ተጀምሯል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መዓዛ አሸናፊ፤ የዳኝነት አገልግሎት ማስጀመሪያ ፕሮግራሙ ላይ በመገኘት እንደተናገሩት፤በ2014 ዓ.ም ስራ ዘመን 25 ሺህ 480 መዛግብት ቀርበው 18 ሺህ 979ዎቹ ውሳኔ አግኝተዋል። በዳኝነትና አስተዳደር ስራ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚረዱ በርካታ መመሪያዎች ወደ ስራ ገብተዋል።

ባለፈው ዓመት የስራ ዘመን 6 ሺህ በላይ መዝገቦች ለ2015 ዓ.ም እንዲተላለፉ ቢወሰንም ዳኞች በክረምቱ የእረፍት ጊዜያቸው በሰጡት አገልግሎት ከ2 ሺህ 200 በላይ መዝገቦች እልባት እንዲያገኙ አድርገዋል ነው ያሉት።

በትናንትናው እለት እየተካሄደ ባለው የ2015 የስራ ዘመን ችሎት ማስጀመሪያ ስነ ስርአት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ከ270 በላይ መዝገቦች እንደሚታዩ ገልፀዋል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ሰለሞን አረዳ፤ ባለፈው በጀት ዓመት የዳኝነት አገልግሎት ነፃ፣ ገለልተኛ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆን በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል ብለዋል።

በ2015 የስራ ዘመንም ዳኞች በነፃነትና ያለምንም ጣልቃ ገብነት አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸው፤ የዳኝነት ጥራትን የማሳደግ ስራም ልዩ ትኩረት ይደረግበታል ብለዋል።

የዳኝነት ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ፣ በስነ ምግባር የተሞላ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት በመስጠት ውጤታማ ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግም ምክትል ፕሬዚዳንቱ መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# ምክር ቤቱ በዚህ ዓመት ስድስት የማንነት ጥያቄዎችን ለመፍታት አቅዷል

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- የፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ ዓመት ስድስት የማንነት ጥያቄዎችን ለመፍታት ማቀዱን የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር ተናገሩ።

ምክር ቤቱ 2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 1ኛ መደበኛ ስብሰባውን ትናንት ሲያካሄድ፤ የማንነት አስተዳደር ወሰን እና የሰላም ግንባታ ቋሚ ኮሚቴ የ2015 ዓ.ም ዓመታዊ እቅድ አቅርቧል።

ቋሚ ኮሚቴው የሚቀርቡ የማንነት ጥያቄዎች ላይ ጥናት ማካሄድ እንደሚያስፈልግ እና አሳታፊ ሊሆኑ እንደሚገባ የገለፀ ሲሆን፤ ውሳኔ ተሰጥቷቸውም ጭምር ከአፈጻጸም ጋር ተያይዞ በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች መኖራቸውን ገልጿል።

በርካታ የወሰን እና የማንነት ጥያቄዎች እየቀረቡ መሆናቸውን የተናገሩት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር፤ ትክክለኛውን ጥያቄ መለየት እንደሚያስፈልግ እና ክልሎች ለሚነሱ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት እንደሚኖርባቸው ገልፀዋል።

በዚህ ዓመት ስድስት የማንነት ጥያቄዎችን ለመፍታት መታቀዱን የተናገሩት አፈ ጉባኤው፤ ክልሎች መግባባት እና ተቀናጅተው መስራት እንደሚጠበቅባቸውም ማሳሰባቸውን ኢቢሲ ዘግቧል።

በሌላ በኩልም ምክር ቤቱ ከቀረቡለት 55 የይግባኝ አቤቱታዎች መካከል አንደኛውን መዝገብ ብቻ ተጨማሪ ጥናት እንዲካሄድበት አቅጣጫ በማስቀመጥ፣ በ54 የይግባኝ አቤቱታዎች ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልጋቸውም በማለት በሙሉ ድምጽ ውሳኔ



አቶ አገኘሁ ተሻገር

ሰጥቷል።

ምክር ቤቱ በተጨማሪም የሕገ መንግሥት ትርጉምና ውሳኔ አፈጻጸም ክትትል ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የ2015 በጀት ዓመት እቅድ ላይ በዝርዝር ተወያይቶ አጽድቋል፡፡

እንዲሁም የፌዴሬሽን ምክር ቤት የድጎማና የጋራ ገቢዎች ድልድል ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የ2015 በጀት ዓመት እቅድ ተወያይቶ ያጸደቀ ሲሆን፤ ከምክር ቤት አባላት እቅዱን አስመልክቶ የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቀርበው የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ሽመልስ አብዲሳ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በተለይም የፌዴራል ሥርዓቱ ዋናው መሠረት የፊሲካል ፌዴራሊዝም መሆኑን ጠቁመው፤ ቋሚ ኮሚቴው ከሀብት ክፍፍሉ ጋር በተያያዘ ካሁን በፊት የነበሩ ችግሮችን በጥናት በመለየት ለመቅረፍ እየሠራ ቢሆንም ችግሩን ከመሠረቱ ለመፍታት ግን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማካሄድ ይገባል ነው ያሉት።

ሰብሳቢው አክለውም፤ ቀመሩን ለመሥራት ቆጠራው ዋነኛው ጉዳይ እንደሆነ አስታውቀው፤ ያሉብን ሀገራዊ ችግሮች በቶሎ ተቀርፈው ቆጠራው እስከሚካሄድ ድረስ ቋሚ ኮሚቴው አስፈላጊ የቅድመ ዝግጅት ሥራ እየሠራ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ችግሩን በአንድ ጊዜ መሻገር ስለማይቻል በሚቀጥሉት ዓመታት ችግሩን ለማቃለል እንደሚሠራና በዚህ ዘርፍ የፕሮጀክት አፈጻጸም መጓተት፣ የበጀት እጥረትና ችግሮችን በአንድ ጊዜ እንዲፈቱ የመፈለግ አዝማሚያ ተግዳሮቶች በመሆናቸው በእነዚህ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባም አስረድተዋል።

አቶ ሽመልስ የመሠረተ ልማቱን ፍትሐዊነት በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ ሲያብራሩ፤ ቀደም ሲል በክልሎች መካከል ፍትሐዊነት የጎደለው አፈጻጸም እንደነበር መግለጻቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

# 17 የአፍሪካ አገራትን ያሳተፈ ቀጣናዊ አውደጥናት በአዲስ አበባ እየተካሄደ ነው

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- በዝቅተኛ ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ የሚገኙ 17 የአፍሪካ አገራትን ያሳተፈ ቀጣናዊ የአቅም ግንባታ አውደ ጥናት ከትናንት ጀምሮ በአዲስ አበባ መካሄድ ጀመረ።

ለአራት ቀናት የሚቆየውን ይህንኑ አውደ ጥናት ያዘጋጁት ዓለምአቀፉ ኢንሃንስድ ኢንቲግሬትድ ፍሬምወርክ (EIF) እና ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ናቸው፡፡

በአውደ ጥናቱ መክፈቻ ላይ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩ አቶ ገብረመስቀል ጫላ ባደረጉት ንግግር፤ ኢአይኤፍ ያደረገው የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ የንግድ ሴክተሩ በአገራዊ አጀንዳ ላይ እንዲካተት አቅም የሚገነባ ነው ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ እድገት ላይ የሚገኙ አገራት ንግድን በአገራዊ እድገታቸው እቅድ አካተው እንዲጠቀሙ፣ ሴቶች እና ወጣቶች የግሉ ዘርፍ ዕድገት አካል እንዲሆኑ በመደገፍ፣ አባል አገራቱ በተፈጠረው ትስስር ተጠቅመው ወጪ ንግዳቸውን እንዲያሳድጉ አቅም የፈጠረ መሆኑንም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በመጪዎቹ 10 ዓመታት በኢንዱስትሪ ያደገች፣ በኢኮኖሚ የጠነከረች እና ለህዝቦቿ የተሻሉ እድሎች ለመፍጠር የቀረጸቻቸው የአጭር እና የረጅም ጊዜ እቅዶችን በመጠቀም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ የመሰለፍ እቅዷን በመተግበር ላይ መሆኗንም ጠቁመዋል። መንግስት የ10 ዓመት እቅድና አጠቃላይ አገራዊ እድገቱን ለማስተዳደር ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ተቀርጸው ተግባራዊ እየሆኑ መሆኑን ሚኒስትሩ አመላክተዋል።

በኮቪድ፣ የተፈጥሮ አደጋዎች እንዲሁም ዓለም አቀፍ እና ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መካከል ቀጣይነት ያለው እድገት ማስመዝገብ መቻሉን የጠቀሱት አቶ ገብረመስቀል፤ ከፍተኛ ባይሆንም ኢአይኤፍ ያደረገው የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ የንግድ ሴክተሩ በአገራዊ አጀንዳ ላይ እንዲካተት አቅም የገነባ መሆኑን ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቱ ባለፉት ጊዜያት ኢትዮጵያ ወደ መካከለኛው ምስራቅ እና ሌሎች ገበያዎች ምርቶቿን እንድትልክ ከማገዙም በላይ የሚኒስትሩን አቅም ግንባታ



እና በቀጣናው እና ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ በመፍጠር ያገዘ መሆኑንም ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የኢንሃንስድ ኢንቲግሬትድ ፕሮጀክት ማዕቀፍ የኢትዮጵያ አስተባባሪ አቶ ኑረዲን መሀመድ በበኩላቸው፣ ለአራት ቀናት የሚቆየው ወርክሾፑ በዝቅተኛ ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚገኙ 17 የአፍሪካ አገራት ጋር የስራ ግምገማ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው ብለዋል።

ፕሮጀክቱ በተቋቋመበት የመጀመሪያ ዓመት የንግድን ሁለንተናዊ ችግሮች አጥንቶ መዋቅር መዘርጋቱን አስታውሰው፤ በሁለተኛው የንግድና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ወቅትም ንግድ ተገቢውን ቦታ እንዲያገኝ የማንቀሳቀስ ሥራዎች መስራቱን ጠቁመዋል።

የ2020/2030 የኢትዮጵያን የ10 ዓመት እቅድ ሥራ ላይም ንግድ ተገቢው ሚና እንዲኖረው አግሮ ኢንዱስትሪዎች በኢትዮጵያ እንዲስፋፉ፣ የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ እድገት እንዲያስመዘግብ አቅም በመገንባት ያገዘ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም ኢትዮጵያ ከዓለም የንግድ ድርጅት እና የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና አባል እንድትሆን የማመቻቸት፣ የሌሎች አገሮችን ልምድ መቅሰም፣ ጥናቶችን በማካሄድ፣ የልዑካን ቡድኖች ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ድጋፍ የሚሰጥ ሲሆን፤ የአገራችን የንግድ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እንዲቀረፅ ድጋፍ እያደረገ መሆኑንም አቶ ኑረዲን ጠቅሰዋል።

ኢአይኤፍ በመላው ዓለም በኢኮኖሚያቸው ዝቅተኛ ከሆኑ አገሮች በእስያ፣ በፓስፊክ፣ በላቲን አሜሪካ፣ እና በሌሎች አገራት የፕሮጀክት ፅህፈት ቤት ተቋቁሞ ንግድ አጀንዳ የማድረግ ስራ ላይ የሚሳተፍ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ኑረዲን፤ ከቀጣናዎቹ የተውጣጡ 48 አገራት የድርጅቱ አባል መሆናቸውን ጠቁመዋል። ከ24 በላይ ዓለም አቀፍ አገሮች እና ተቋማት ድጋፎችን በማሰባሰብ ኢትዮጵያን ጨምሮ ለአባል አገራቱ ነጻ ድጋፍ ይሰጣል ብለዋል።

ፕሮጀክቱ ኢትዮጵያን ከዓለም የንግድ ሥርዓት በማስተሳሰር አቅም እየገነባ መሆኑንም አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ጠንካራ፣ ዘመናዊ ቀልጣፋ እና በኢኮኖሚ የተደገፈ ለማድረግ በቴክኖሎጂ የተደገፉና ዘመናዊ የንግድ አሰራሮችን በመተግበር የዓለም የንግድ ትስስር መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን አመላክተዋል።

# አንዳንድ የምዕራባውያን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ ጋዜጠኛ ጥበቡ ገለፃ፣ ጦርነት በግንባር ብቻ ሳይሆን በሚዲያ፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በሁሉም ዘርፍ የሚደረግ በመሆኑ ምዕራባውያን በአሸባሪው ትህነግ በኩል የሚያገኙትን ጥቅም እንዳይቀርባቸው በሚዲያዎቻቸው ኢትዮጵያን እየወነጀሉ ነው።

እነዚህ ሀገራት ኢትዮጵያን ማሸነፍ ስላልቻሉ የተለያዩ ጥናቶችን በማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም፣ እድገትና አንድነት እንዳይኖር በሚዲያዎቻቸው እንደ አሸባሪው ትህነግ አይነት ተላላኪን በመደገፍ ኢትዮጵያን ለማፍረስና በተጽዕኖ ለማኖር እየሰሩ ይገኛሉ ብሏል።

የውጪ ሀገር የዜና ተቋማት ለአንድ ወገን የማድላት ተፈጥሮ ያላቸው በመሆኑ ቅርፃቸውና ይዘታቸው በብዙ ነገር ይለያያል። ፎክስና ሲኤንኤን የተባሉ የአሜሪካ መገናኛ ብዙኃንን አንዱ ለሪፐብሊካን ሲያደላ ሌላኛው ደግሞ ለዲሞክራት ያደላል።

የጋዜጠኝነት ሙያ ከእንደዚህ አይነት ድርጊቶች መቆጠብና መራቅ አለበት ብለው እያስተማሩ በኢትዮጵያ ላይ የውሸትና የሀሰት መረጃ እያስተላለፉ ይገኛሉ ያለው ደራሲ ጥበቡ፤ ከአንድ በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ ከበለጸገ ሀገር የማይጠበቅ ተግባር ነው ብሏል።

እንደ ጋዜጠኛ ጥበቡ ገለፃ፣ ኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ ተጽዕኖዎችን ስለምታሸንፍ ሁልጊዜ ከኋላ ችግር መፍጠር የሚፈልጉ አካላት የኢትዮጵያውያን ጥንካሬና ድክመት ምን እንደሆነ ለማወቅ ሲጥሩ አንዳንድ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ደግሞ ከአባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ የአባይን ምንጭ ለመቆጣጠር ልጆቻቸውን ሴራ ያስተምራሉ።

አብዛኛውን የውጪ መገናኛ ብዙኃን ስለአፍሪካ የሚያቀርቡት ዜና የልማት ሳይሆን የጦርነት፣ የግጭት፣ የረሃብ ዜና መሆኑን እንደ ባህል መወሰዱን የጠቆመው ጋዜጠኛ ጥበቡ፤ ይህን የሚያደርጉትም አንድ ድልድይ አፍሪካ ውስጥ ቢሰራ ላደጉ ሀገራት ዜና እንደማይሆን ስለሚረዱ ነው፡፡ ምክንያቱም ምዕራባውያን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ያደጉ ስለሆኑ አፍሪካ ውስጥ ድልድይ ተሰራ ብሎ መዘገብ ዋጋ አይኖረውም ብሏል።

በመሆኑም አፍሪካውያን መቅረፍ ያለባቸው በውስጣቸው ያለውን ግጭት፣ጦርነትና ርሃብን ነው። የአለም ህዝብ ግጭት፣ ጦርነትና ርሃብን የተመለከተ ዜና ሲያይ በመደንገጥ ዜናውን በትኩረት ይመለከታል። ይሄ ደግሞ በአብዛኛው የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ይገኛል። ነገር ግን የአፍሪካውያን ግጭትና ችግር መንስኤ ደግሞ የአንዳንድ ምዕራባውያን ሴራ መሆኑን ይዘነጉታል ብሏል፡፡

አንዳንድ ምዕራባውያን የሚያወጡት ፖሊሲና የሚደግፉት አሸባሪ ለአፍሪካ የርሃብና ግጭት መንስኤ ነው። ኢትዮጵያን በቅኝ መግዛት ስላልቻሉ በሚዲያ መግዛት፣ በፊልም፣ በኢኮኖሚና በልዩ ልዩ መስኮች የቅኝ ግዛት ስርዓትን መዘርጋት ይፈልጋሉ።

የአፍሪካ እድገት መጓተትና ችግር መብዛት ተጠያቂው ራሳቸው ቢሆኑም አፍሪካውያን ለራሳቸው እድገት ሰላምና ብልጽግና ጠንክረው መስራት ይኖርባቸዋል። ይህንን ሳይሰሩ በምዕራባውያን እያሳበቡ መኖር ተገቢ አይደለም። እነሱም አፍሪካ ላይ የሚዲያ ተጽዕኖ እያሳደሩ ይገኛሉ ብሏል።

እንደ ጋዜጠኛው ገለፃ፣ ጦርነት በግንባር ብቻ ሳይሆን በሚዲያ፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በሁሉም ዘርፍ የሚደረግ በመሆኑ አፍሪካውያን ነቅተው ተስማሚ ምላሽ መስጠት አለባቸው። ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለች ሀገር እንደመሆኗ መጠን ትውልዱን በማስተማርና የተማረ የሰው ሀይል በማምረት ያላትን ሀብት በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ስልጣኔ የነበራት ሀገር ሆና ሳለ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በጦርነትና በረሃብ የምትሰቃየው ለምንድን ነው ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል። ለዚህም ራስን ለመለወጥና ለነገሮች ዝግጁ መሆን ነው እንጂ ሁልጊዜ ወደ ምዕራባውያኑ እጅ መቀሰር አስፈላጊ አይደለም ብሏል። የአንዳንድ ምዕራባውያን ሀገራትን ተጽዕኖ ለመመከት መማርና ከዘረኝነት መውጣት እንደሚያስፈልግም ተናግሯል።

ትህነግ ኢትዮጵያ ላይ ያመጣባት ጣጣን ትውልዱ ሊቀለብስውና ሊያጠፋው ይገባል። ለዚህም ልማትና የዜጎች ተጠቃሚነት ላይ ትኩረት የሚደረግ ከሆነ ሀገራችን የማትቀየርበት ምክንያት የለም ብሏል።

# ግብርና ሚኒስቴር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሊወጣ ይገባል።

ድጋፉን የተረከቡት የመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ማርታ ሊዊጂ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በሉአላዊነቱ የሚመጣውን ማንኛውንም ኃይል ለመቋቋም ለመከላከያ ሰራዊት ስንቅ እያቀበለና ልጅ እየላከ ነው። አሁን ደግሞ የግብርና ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት ለሰራዊቱ ከ80 ሚሊዮን ብር በላይ የገንዘብና የአይነት ድጋፍ አድርገዋል።

በዚህም ስንቃ፣ ዘይትና ለምግብነት የሚያስፈልጉ ሁሉንም አዘጋጅተው በማምጣታቸው በመከላከያ ሚኒስቴር ስም አመስግነዋል። የግብርና ሚኒስቴር የሀገሪቱ የጀርባ አጥንት ሆኖ እያገለገለና ለመከላከያ ሰራዊትም በሰፊው ድጋፍ እያደረገ ያለ ነው።

እንደ አገር የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና ለውጭ አገራት ስንዴ ለመላክ የሚያደርገው ጥረት የሚደነቅ ነው ያሉት ወይዘሮ ማርታ፤ ይህንን ሥራችሁን በመከላከያ ቁመናና ዝግጁነት አጠናክራችሁ መቀጠል ይኖርባችኋል ብለዋል።

በተያያዘም በ2014 ዓመተ ምህረት በመስኖ ስንዴ ልማትና በክረምቱ በተደረገው እንቅስቃሴ ስንዴን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ዝግጅት እየተጠናቀቀ መሆኑን አስታውቋል፡፡

ኢትዮጵያ ከምንጊዜውም በላይ ከድህነት ለመውጣት ተግታ እየሰራች በመሆኗ በግብርናው ዘርፍ አመርቂ ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል ያሉት ፕሮፌሰር ኢያሱ፣ የግብርና ሚኒስቴር በሚሊየን ዶላር የሚገባ የስንዴ ምርትን ሙሉ ለሙሉ በአገር ውስጥ ለመተካት እና ከዚያም አልፎ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ዝግጅት እያጠናቀቀ መሆኑን ገልጸዋል።

በውጭ እርዳታና ድጋፍ ላይ ተንጠልጥሎ የአገርን ሉአላዊነት ማስከበር አዳጋች ስለሚሆን ለምግብ ዋስትና የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ሁሉም ዜጋ በተሰማራበት ዘርፍ ጠንክሮና ነቅቶ በመስራት ኢትዮጵያን ከድህነት ማስወጣት ይኖርበታል ብለዋል።

# የሳይበር ደህንነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ በዩኒቨርሲቲዎች እና መሰል ተቋማት ውስጥ ታዳጊዎችን በዘርፉ ኮትኩቶ ለማሳደግ የሚያስችሉ ማዕከላት ተቋቁመው አመርቂ ውጤት ማሳየት መጀመራቸውም ተስፋ ሰጪ መሆኑን አክለው ገልፀዋል፡፡

የኢትዮጵያ የሳይበር ደህንነትን የማረጋገጥ ሥራ በዋነኝነት ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የተሰጠ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ደመቀ፤ ሆኖም የሳይበር ደህንነት ውጤታማ እንዲሆን የባለድርሻ አካላት ቅንጅትና ተሳትፎ ያስፈልጋል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በመሆኑም ሀገራዊ የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን ለማረጋገጥ ብሎም የሳይበር ደህንነትን እውን ለማድረግ የግሉ ዘርፍ ሚና ወሳኝ ነው ሲሉ አክለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት አንዱ መገለጫ የሳይበር ምህዳሩ እንደመሆኑ መጠን በዘርፉ ከሌሎች ሀገራት ጋር በትብብርና በቅንጅት መሥራት ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ የሳይበር ዲፕሎማሲ ሥራችንን በከፍተኛ ሁኔታ ትኩረት ሰጥተን የምንሰራበት መስከ መሆኑ ነው ብለዋል፡፡

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዶክተር በለጠ ሞላ በበኩላቸው፤ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ካስቀመጣቸው አስቻይ ሁኔታዎች ውስጥ የመረጃ መረብ ደህንነት አንዱ መሆኑን ተናግረው፤ የዲጂታል መሰረተ ልማቶችን ከጥቃት መከላከል ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ጠቅሰዋል፡፡

ሚኒስትሩ አክለውም፤ የዲጂታል ክህሎት እና የመረጃ መረብ ደህንነት ላይ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ተቋማት በቅንጅት መሥራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ሶካ በበኩላቸው፤ በዲጂታል ስነ ምህዳሩ ላይ ተሳታፊ ሆኖ ለመቀጠል የመረጃ መረብ ደህንነት ሥራ ላይ ከፍተኛ ትኩረት እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል።

በ2014 በኢትዮጵያ በተለይ በባንኮች እና ፋይናንስ ተቋማት ላይ ያነጣጠሩ የሳይበር ጥቃቶችን በመከላከል በቢሊየን የሚቆጠር ብር ማዳን መቻሉን ያብራሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የመረጃ መረብ ደህንነትን ማስጠበቅ የአንድ ተቋም ሥራ ባለመሆኑ ሁሉም በትብብር ሊሠራ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ሦስተኛው የሳይበር ደህንነት መከበር ዋና ዓላማ የተቋማትን የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት መቀነስ፤ በሳይበር ደህንነት የግሉን ዘርፍ ሚና ማሳደግ፤ ጥራት ያለው የሳይበር ደህንነት ባለሙያ ለማፍራት ምቹ ሁኔታ መፍጠር እና የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ማሳደግ ሲሆን፤ መርሃ ግብሩ ከጥቅምት 1 እስከ 30 ቀን 2015 ዓ.ም በተለያዩ ዝግጅቶች እየተከበረ የሚቆይ መሆኑን መርሃ ግብሩ ያሳያል።

# ወረዳው ለውጭ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ዞኖች ከግብርናው ዘርፍ የተውጣጡ ታዳሚዎች በአርሲ ዞን በስንዴ አምራችነቷ ከምትታወቀው በሔጦሳ ወረዳ በሻቂ ሻራራ ቀበሌ ተገኝተው የልምድ ልውውጥ ባደረጉበት ወቅት የወረዳው ግብርና ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊው አቶ ዘሪሁን መኮንን እንዳስታወቁት፤ ኬምቴክስ የተባለ የእርሻ ግብዓቶች አስመጭ የግል ድርጅት ለአርሶ አደሮች የሚያቀርበውን ጸረ አረምና ጸረ በሽታ (ፈንገስ) ኬሚካል በአግባቡ መጠቀም በመቻላቸው ዘንድሮ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ 50 ሺ ኩንታል ስንዴ ለማምረት ተዘጋጅተዋል::

ከ26 ሺ ሔክታር መሬት ወደ 24 ሺ ሔክታር መሬት የዘራነው በኩታ ገጠም ነው ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ ከዚህም ውስጥ 15 ሺ 952 ሔክታር መሬት ላይ በኩታ ገጠም የተዘራ ስንዴ ነው ብለዋል:: በዚህ መልኩ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው ስንዴ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የቢራ ገብስ ነው:: ደጋማውን ክፍል ቢራ ገብሱ የያዘው ሲሆን፣ ወይና ደጋና ቆላማው አካባቢ ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ ስንዴ እየተመረተ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል::

ሔጦሳ ኩታ ገጠም በስፋት የሚሰራበት ወረዳ እንደመሆኑ አጠቃላይ ካለው መሬት ውስጥ ከ95 በመቶ በላይ የሚጠቀሙት በመካናይዜሽን እንደሆነ የገለጹት ምክትል ኃላፊው፤ ከዚህ የተነሳ ዘንድሮ ኢትዮጵያ እንደግብ የያዘችውን ስንዴ ወደውጭ ሀገር የመላክ እቅድ ስኬታማነቱን ለማረጋገጥ በብርቱ እየሰራን ነው ብለዋል:: ዘንድሮ በ50 ሺ ኩንታል ስንዴ ወደውጭ ሀገር የመላኩ ጅማሮ በየጊዜው እያደገ እንደሚመጣም በትጋት እንደሚሰሩ ተናግረዋል:: ምንም እንኳ በአካባቢያቸው ከፍተኛ መስኖ ባይኖራቸውም በክረምቱ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው የሰሩ ስለሆነ ስንዴ ወደውጭ ሀገር የመላካቸውን ውጥን እናሳካዋለን ሲሉ አስረድተዋል::

አቶ ዘሪሁን እንደተናገሩት፤ የወረዳዋ አርሶ አደሮች ምርትና ምርታማነታቸው የበለጠ እንዲጨምር ኬምቴክስ ከተባለ ድርጅት ጋር በቅርበት በመስራት ላይ ናቸው:: ድርጅቱ አብሯቸው የሚሰራው በሁለት አንኳር ጉዳዮች ላይ ሲሆን፣ አንዱ በጸረ አረም ኬሚካል ሁለተኛው ደግሞ ጸረ በሽታ ወይም ጸረ ፈንገስ ላይ ነው:: ባደረጉት ግምገማም ፓላስ ሱፐር የበለጠ ውጤታማ እየሆነ ነው:: መድኃኒቱን በአግባቡ ከተጠቀሙ አመርቂ ውጤት አለው:: ይህን ኬሚካል በመጠቀም በተግባር ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ ምርትና ምርታማነታቸውን ከፍ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል::

ሁለተኛው ጉዳይ ጸረ ፈንገስ ወይም በሽታ ላይ ሲሆን፣ በተለይ ሶስት መድኃኒቶች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ እየተጠቀምን ነው ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ አንደኛው ላይፍሾው የሚባለው እድሜው ረጅም ቢሆንም በውጤታማነቱ በጣም ጥሩ ደረጃ ላይ ያለ ነው ብለዋል:: አካንቶ የሚባለው ደግሞ አዲስ መድኃኒት ሲሆን፣ ላይፍ የሚባለው ደግሞ ከአምና ጀምሮ ስንጠቀመው የቆየንና ውጤትም ያገኘንበት ነው ሲሉ አመልክተዋል:: መድኃኒቶቹ ብዙ ድግግሞሽ የማይፈልጉ በመሆናቸው አንዴ ከተረጨ ውጤታማ የሚሆን ነው ሲሉ ገልጸው፤ ለምርትና ምርታማነት ትልቅ ድርሻ አለው ብለዋል:: አምሮ የሚታየው ሰብል የማማሩ ምስጢር የጸረ አረምና የጸረ በሽታ ወይም ፈንገስ መድኃኒቶች ናቸው ሲሉ ገልጸዋል::

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ ኬምቴክስን ለየት የሚያደርገው በየዓመቱ የመስክ ላይ ሙከራ ማድረጉ ነው:: ከዚህም በላይ ዘንድሮ በወረዳቸው ሔጦሳ ከሚገኙ ሶስት ቀበሌ ውስጥ ላሉ ለ90 አባወራዎች 30 ሔክታር መሬት ላይ የነጻ አገልግሎት ሰጥቷል:: እንደ ኬምቴክስ ያሉ ብዙ ድርጅት ያሉ ቢሆንም ይህ ድርጅት ግን እንደወረዳቸው ለአርሶ አደሮቹ ምርታማነት የአንበሳውን ድርሻ የያዘና አመርቂ ውጤት እንዲያመጡ ማድረግ የቻለ ነው::

የአርሲ ዞን የሰብል ልማት ባለሙያ አቶ ሙዘይን አማን በበኩላቸው፤ ኬምቴክስ የተባለው ድርጅት ከዞኑ ጋር በቅርበት ከሚሰሩ ተቋማት አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፤ ድርጅቱ የራሱን ውጤት ለገበያ ከማቅረብ ባለፈ በተጨባጭ አርሶ አደሩ ማሳ ድረስ በመውረድ የምርታቸውን ውጤታማነት እስከማረጋገጥ የሚሰራ ነው ብለዋል:: ድርጅቱ በዞናቸው ስንዴ አምራች ወረዳ በሆኑና ሌሎችንም ሰብሎች በሚያመርቱ ወረዳዎች ላይ በቅርብ በመስራቱ በምርታማነት ላይ እንደባለሙያ በተጨባጭ ያረጋገጡት ውጤት እንደሆነም አመልክተዋል::

የዞናችንን ሰፊውን እርሻ የሚሸፍነው ስንዴ ነው ያሉት ባለሙያው፣ ለአብነትም በዘንድሮ ዓመት ከ656 ሺ ሔክታር የመኸር ሰብል ከተሸፈነው ውስጥ 281 ሺ ሔክታር መሬት የተሸፈነው በስንዴ ነው ብለዋል:: ከአንድ ወር በኋላም ወደ ሰብል ስብሰባው እንደሚገቡ ተናግረዋል::

ዘንድሮ በሚሊዮን ኩንታል የሚቆጠር ስንዴ ለውጭ ገበያ እናቀርባለን ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሶማሌ ክልል በመገኘት የ2015 ዓ.ም አገር አቀፍ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በይፋ ባስጀመሩበት ወቅት መናገራቸው ይታወሳል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰላም፣ ሰላም፣ ሰላም የኢትዮጵያና ሕዝቦቿ የጸና አቋም!

በአሸባሪው ትህነግ ጠንሳሽነት የተጀመረው ጦርነት ከተጀመረ ሁለት ዓመት ሊሞላው ጥቂት ቀናት ቀርተውታል:: አሸባሪ ቡድኑ ሀገርን እየጠበቀ የነበረውን የሰሜን ዕዝን ከኋላው በመውጋት የጀመረው ጦርነት ዋነኛ ዓላማ ኢትዮጵያን ማፈራረስ ቢሆንም በኢትዮጵያውያን አኩሪ ተጋድሎ የሀገሪቱን ህልውና አስቀጥሎ ዛሬ ላይ መድረስ ተችሏል::

ያለ ጦርነት ህልውናውን ማስቀጠል የማይችለው የትህነግ የሽብር ቡድን በተደጋጋሚ ለሰላም የተዘረጉ የመንግስት እጆችን በመንከስ ኢትዮጵያ በጦርነት አዙሪት ውስጥ እንድትዳክርና ብሎም ተዳክማ እንድትበታተን አበክሮ ሲሰራ ቆይቷል:: ለትግራይ ሕዝብ ቆሜያለሁ በሚል ጭንብል የውጭ ኃይላትን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል በርካታ የትግራይ ወጣቶችን አስጨርሷል:: ከአንድም ሶስት ጊዜ በለኮሰው ጦርነት ሰፊ ቁጥር ያለውን የትግራይ ወጣት አስገድዶ በማሰለፍ በጦርነት ማግዷል:: አካል ጉዳተኞችን፣ ሴቶችንና ህጻናትን ብሎም መነኩሴዎችን ሳይቀር በጦር አውድማ በማሰለፍ ትውልድ ይቅር የማይለው በደል ፈጽሟል::

ይህም አልበቃ ብሎት አሁንም አዲስ የጦርነት ክተት አውጇል:: በአፍሪካ ኅብረት መሪነት የሰላም ውይይት ለማካሄድ ጥረት በሚደረግበት በዚህ ወቅት አሸባሪ ቡድኑ የጦርነትና የግጭት አማራጮችን በመምረጥ ግፋ በለው በማለት ላይ ይገኛል:: የተለያዩ ሰበቦችን በመደርደር የሰላም ውይይቱን ለማደናቀፍ ጥረት ሲያደርግ የቆየውና አሁንም እያደረገ ያለው የሽብር ቡድኑ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብን ለማደናገር የሰላም ንግግሩን የተቀበለ ቢያስመስልም ሳይውል ሳያድር እውነተኛ የጦርነት ባህሪው ተገልጾ የክተት አዋጅ አውጇል::

ሰላም ጠል የሆነው ግትር የፖለቲካ አካሄድን የሚከተለው አሸባሪው ትህነግ ከምስረታው ጀምሮም ውይይትን እንደሰላም አማራጭ እንደማይመለከት የድርጅቱ ነባር አመራሮች ጭምር ያስረዳሉ:: የሽብር ቡድኑ ሁሉንም ነገር በኃይል የመፍታት ልምድ ያለው ድርጅት ነው:: ድርድርን አማራጭ ካደረገ እንኳን ለታክቲክ አለበለዚያም ለጊዜ መግዣነት እንጂ በድርድር ለውጥ አመጣለሁ ብሎ በማመን እንዳልሆነ የሚያሳዩ በርካታ ተግባራትን መፈጸሙም ጸሐይ የሞቀው ሀቅ ነው::

የትህነግ አሸባሪ ቡድን በየጊዜው እየጫረ በሚለኩሰው እሳት የትግራይ ወጣቶች በገፍ እንዲያልቁ አድርጓል:: በደርግ ዘመነ መንግስት በአስራሰባት ዓመታቱ ጦርነት ከ60 ሺ በላይ የትግራይ ወጣቶች ህይወታቸውን እንዳጡ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ከዚህ ውስጥ 1/3ኛ የሆነው ለትግል የወጣው የትግራይ ወጣት በራሱ በአሸባሪው ቡድን ሴራ ህይወቱ እንደተቀጠፈ የድርጅቱ ነባር አመራሮች የሚናገሩት ሃቅ ነው:: በተለይም ከእርሱ የፖለቲካና የተሳሳተ መንገድ በተለየ መልኩ ሃሳብ ያቀረቡ ንጹህ የትግራይ ታጋይ ወጣቶችን ያለ ርህራሄ ሲረሽን መቆየቱን የድርጅቱ ዝክረ ታሪክ ያስረዳል::

አሸባሪው ትህነግ የሰላምን ወሬ መስማት አይፈልግም:: ያለ ጦርነት ህልውና ስለሌለው ለሰላም የተዘረጉ እጆችንም ደግሞ ደጋግሞ ሲነክስ ቆይቷል:: አሸባሪው ትህነግ በሴብነት አፈና ተግባሩ በሕዝቦች የተባበረ ትግል ከአዲስ አበባ አፈግፍጎ መቀሌ ከመሸገ ጊዜ ጀምሮ ከ11 ጊዜያት ያላነሰ የተለያዩ የሰላም ጥሪዎች ቢያቀርቡለትም የተዘረጉ የሰላም ጥሪዎችን ገፍቶ መልሷል:: የሃይማኖት አባቶችና ታዋቂ ግለሰቦች መቀሌ ድረስ ሄደው ሲለምኑት አዋርዶ በመመለስ ለሰላም ያለውን ጥላቻ በገሃድ አሳይቷል::

አሸባሪ ቡድኑ በሀገርና በሕዝብ ላይ የፈጸመው ግፍ ይቅር የማይባል ቢሆንም መንግስት ለትግራይ ህዝብ ሲል አሸባሪ ቡድኑ ወደ ሰላም እንዲመጣ ያደረጋቸው እልህ አስጨራሽ ጥረቶች በቡድኑ ተገፍተው መክነዋል:: በአንድ በኩል የሕዝቡን ሰላም የማስጠበቅ በሌላ በኩል የሀገሪቱን ህልውና የማስቀጠል ኃላፊነት የተጣለበት የኢትዮጵያ መንግስት የተገኙ የሰላም አማራጮችንና ዕድሎችን ሁሉ ለመጠቀም በብዙ ደክሟል::

‹‹መቼም ፤ የትም፣ በምንም ጉዳይ የሰላም ንግግር ለማካሄድ ቁርጠኛ መሆኑን ያለማሰለስ እየገለጸ ያለው የኢትዮጵያ መንግስት አሸባሪ ቡድኑ ጦርነቱን ለማራዘም ክተት ባወጀበት በዚህም ወቅትም ቢሆን የማይናወጥ የሰላም ሃሳቡ አሁንም የፀና መሆኑን ገልጿል:: የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ክብርት ሳህለ ወርቅ ዘውዴ በሁለቱ ምክር ቤቶች መክፈቻ ስነስርዓት ላይ ተገኝተው ያረጋገጡትም ይህንኑ ሃቅ ነው::

ከትናንት በስቲያ በተካሄደው ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት 2ኛ ዓመት የጋራ መክፈቻ ስብሰባ ላይ ፕሬዚዳንት ሳህለ ወርቅ ዘውዴ አጽንኦት ሰጥው እንዳብራሩት፤ “የአገሪቱን ጥቅም ባስከበረ” እንዲሁም “ዘለቄታን ባማከለ” መልኩ ከሕወሓት ጋር የሚደረገውን ድርድር የፌደራል መንግሥቱ እንደሚቀጥልበት ገልጸዋል። መንግሥት “ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለመደራደር” ያለውን ፍላጎት በንግግራቸው ጠቅሰው “የሰላም በር አይዘጋም” ሲሉ አስምረውበታል። “መንግሥት የሠላምና ዲሞክራሲ ጥያቄዎችን አንገብጋቢነት በመረዳት ባሳለፈው ቆራጥ ውሳኔ መሠረት ከሕወሓት ጋር የሀገሪቱን ጥቅም ባስከበረ እንዲሁም ዘለቄታን ባማከለ መልኩ ድርድር እንዲደረግ የተቻለውን ጥረት በማድረግ ይገፋበታል:: ነገር ግን ይህንን የሠላም አማራጭ በመርገጥ ለሚደረግ ማንኛውም ትንኮሳ አስፈላጊውን የማስታገሻ እርምጃዎች የሚወስድ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል” ሲሉም አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# በምግብ ራስን ከመቻል ከፍ ያለው የስንዴ ልማቱ ስኬታማ ጉዞ

**በየኔነው ስሻው**

ድህነት ክፉ ነው፤ ረሃብ ደግሞ ከዚህም በብዙ እጥፍ የከፋ፣ ከከፋትም በላይ ክብርና ማንነትን ለዕለት ጉርስ ዝቅ አድርጎ ማስገዛትን የሚያስከትል ነው:: ችግሩ እንደ ሕዝብና ሀገር ሲሆን ደግሞ፤ በልቶ የማደር ጥያቄን ለመመለስ ክብርና ሉዓላዊነትን አሳልፎ ወደሚያሰጥ፤ ለረጂ ሀገራትና ተቋማት በርን ከፍት አድርጎ እስከመቀበልና ለእነሱ ጥቅምና ፍላጎት እጅ እስከመስጠት የሚያደርስ አደጋን የሚጋብዝ ነው:: በዚህ ረገድ በርካታ ሀገራት የዜጎቻቸውን በልቶ የማደር ጥያቄ ለመመለስ፤ ከድህነት አረንቋ ለመውጣት ሲሉ ክብርና ሉዓላዊነታቸው ተደፍሮ፣ ሰላማቸው ከእጃቸው ወጥቶ በረጂዎቻቸው ፍላጎትና ጥቅም ላይ ተመሥርተው ለመራመድ ተገድደዋል:: በርካቶችም በድህነት በራቸው በገባ አካል እጃቸው ተጠምዝዞ እንደ ሀገር የመኖር ሕልውናቸው በእነዚሁ ሀገራትና ተቋማት መዳፍ ላይ ወድቆ ይታያል::

ኢትዮጵያም፣ ምንም እንኳን ድህነትን እና ጊዜ ጠብቆ የሚከሰተውን ድርቅና ሌላም ክስተት ተከትሎ እጆቿን ለምጽዋት ስትዘረጋ የኖረች ብትሆንም፤ የዜጎቿን በልቶ የማደር ፍላጎት ለማሟላት በምታደርገው ሂደት ውስጥ የተዘረጋውን እጇን ይዞ ለመጠምዘዝ ለሚደረግ ጥረት ግን በጅ ሳትል ዘመናትን ኖራለች:: ድህነቷን ተጠግተው ሊጠመዝዟትና ሊያንበረክኳት የሚሹ ኃይሎችን እንደየአመጣጣቸው ስትመክትና ስትመልስም ዘመናትን አስቆጥራለች:: ዛሬም ድረስ ይሄንኑ የድህነቷን ጥላ ተጠልለው የዜጎችሽን ሆድ ከሞላን እንዳሻን እንዘዝሽ ለሚሏት ሁሉ፤ ክብር በሆድ አይለወጥም በሚል በእንቢኝ ለክብሬ ቆፍጣና አቋማ ጸንታለች::

ይህ ሂደት ግን እንዲሁ በቀላሉ እንቢ ስለተባለ ብቻ የሆነ አይደለም:: ይልቁንም ብዙ ዋጋ እያስከፈላት የዘለቀ እንጂ:: ድጋፍ ከመከልከል ጀምሮ ጦርነት እስከማስነሳት ደርሶ በሚገለጸው በዚህ እጅ መጠምዘዣ ጫናቸው ላለመንበርከክ የዜጎቿን ውድ ሕይወት ከፍላለች፤ ከሌላት ቀንሳ የገነባቻቸውን የልማት አውታሮችም አጥታለች:: ነገር ግን ኩሩና ለክብሩ ሟች የሆነውን ሕዝቧን (በሰሜንም፣ በደቡብም፣ በምስራቅም፣ በምዕራብም ያለውን) ለአንድ ዓላማ እንዲሰለፍ፤ ለክብርና ሉዓላዊነቱ በሙላት መከበር እንቅፋት የሆነበትን ድህነት ለማሸነፍ በሚያስችለው መስመር ላይ በጋራ ለመቆም የሚግባባበትን፤ ተግባብቶም ወደ ተግባር የሚገባበትን ዕድል ፈጥሮላታል::

እናም ሃብት ላይ ተኝቶ ድህነትና ረሃብ ሊሆን የማይገባው የተቃርኖ ዓለም ነውና፤ አገር ያላትን እምቅ አቅም ለይቶና እንደየፈርጁ አልምቶ በመጠቀም ከድህነት መውጣት ይቻላል የሚለውን እምነት በሁሉም ዜጎች ማስረጽ ተቻለ:: ማስረጽ ብቻም ሳይሆን በግብርናው፣ በኢንዱስትሪው፣ በማዕድን፣ በቱሪዝም፣... ዘርፎች ያሉ እምቅ አቅሞችን በመለየት ማልማትና መጠቀም እንደሚቻል በተግባር መግለጥ ተጀመረ:: ለዚህ አንዱ ማሳያ ደግሞ ግብርናው ሲሆን፤ በተለይ ስንዴን አልምቶ ከራስ አልፎ ለሌሎች መትረፍ ሲቻል ስንዴ መለመን አይገባም የሚል እምነት ተይዞ ስንዴን በመስኖና በቆላማ አካባቢዎች በማምረት ጭምር እጅን በአፍ ያስጫነ ውጤት ማምጣት ተቻለ:: በዚህም የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ተደራሽነትን በራስ አቅም ከመደጎም ጀምሮ፤ ከውጪ የሚገባ የስንዴ ምርትን በከፍተኛ ደረጃ ማስቀረት የተቻለበትን እውነት አስመልክቷል::

በዘርፉ የተጀመረው ሥራ የበለጠ እየሰፋና እየተጠናከረ መሄዱ ደግሞ፤ አንደኛ፣ ሰፊ የሥራ እድል መፍጠር አስችሏል:: ይሄ ደግሞ ወጣቱ አቅምና ጊዜውን በአልባሌ ጉዳዮች ላይ ከማዋል ይልቅ ለልማት በማዋል ራሱንም፣ ወገንና አገሩንም የሚጠቅምበትን እድል በመስጠት፤ ለገንዘብ ሲል ራሱንም አገሩንም አደጋ ውስጥ እንዲከትት ከውጪ ሆነው ለሚነዱት የጥፋት ኃይሎች ተገዢ እንዳይሆን አድርጎታል:: ይሄን መልካም ጅምር ማስፋትና ማጽናት ከተቻለ ደግሞ ውጤቱ ከዚህም የሚልቅ ለመሆኑ እሙን ነው::

በሌላ በኩል፣ የስንዴ ልማት ሥራው አገር ከውጪ የምታስገባውን ስንዴ በአገር ውስጥ አምርታ እንድትሸፍን ያስቻለ ሲሆን፤ ይሄም በአንድ በኩል ስንዴን ለመግዛት የሚወጣውን የውጪ ምንዛሪ የሚያስቀር፤ በሌላ በኩል አርሶ አደሩ ለሚያመርተው ምርት ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝ እና ለላቀ ምርታማነት እንዲነሳሳ ያደረገው ሆኗል:: የዚህ አንዱ ማሳያ ደግሞ ስንዴን በራስ አቅም አምርቶ የራስን ፍላጎት ከመሸፈን ባሻገር፤ በመሰል ችግር ውስጥ ለሚገኙ የጎረቤት ሀገራት በሽያጭ ማድረስ የሚቻልበትን እድል ታሳቢ ያደረገ ህልም ተይዞ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመሩ ነው:: ይህ ደግሞ በአንድ በኩል የውጪ ምንዛሪን ከማዳን አልፎ የውጪ ምንዛሪን ወደማስገኘት መሸጋገር እንደሚቻል የሚያሳይ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ከተረጂነት ተላቅቃ ራስን መቻልና ለሌሎችም መትረፍ እንደሚቻል ምሳሌነቷን በተግባር የገለጸች አገር በመሆና ከፍ ያለ የገጽታ ግንባታ ስዕል የሚፈጥርላት ነው::

እነዚህ እውነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ግን፤ ስኬታማው የስንዴ ልማት ጉዞው በምግብ ራስን ከመቻል፣ የውጪ ምንዛሪን ከማዳን፣ የሥራ ዕድል ከመፍጠርና የውጪ ምንዛሪን ከማስገኘት ከፍ ያለ ትርጉም የሚሰጥ ነው:: ይሄውም ኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ክብሯን በዐውደ ውጊያዎች ብቻ ሳይሆን በልማት መድረኮች ላይም ፈርጥማ በመውጣት ለሉዓላዊነቷ የምታነሳቸውን ክንዶች ዘርፈ ብዙና በኢኮኖሚውም ፈርጥመው የሚገለጹ እንዲሆኑ የሚያስችላት ነው:: በዚህም በጦር ዐውዶች፣ በዲፕሎማሲውና በሌላውም ከፍ ብላ በታየችባቸው መስኮች እንዳደረገችው ሁሉ፤ ድህነትና ረሃቧን ተጠቅመው በርዳታና ድጋፍ ስም እጅሽን እንጠምዝዝ፤ ሉዓላዊነትሽን ተዳፍረን እንዘዝሽና እኛ እንወስንልሽ የሚሏትን ኃይሎች ቆም ብለው እንዲያስቡ፤ አደብ እንዲገዙና፤ ከኢትዮጵያ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በእጅ ጥምዘዛ ላይ ሳይሆን በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ትብብር ሊሆን እንደሚገባው የሚገነዘቡበትን አውድ የሚፈጥርላት ነው::

መረጃዎች እንደሚያሳዩት ደግሞ፤ መስኖ በመጠቀም በ2015 በ1ነጥብ3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት 52 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ በመስኖ፥ 101 ሚሊዮን ኩንታል በመኸር በድምሩ 153 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማምረት ግብ ተጥሎ እየተሠራ ይገኛል:: ከሰሞኑም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፣ በሱማሌ ክልል በመኸር እየለማ ያለውን ስንዴ ከመጎብኘት ጎን ለጎን፤ ሀገራዊ የበጋ መስኖ ስንዴ ማስጀመሪያ ይፋ ባደረጉበት ወቅት የታየውና የተሰማውም ይሄው እውነት ነው:: እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር፤ የ2015 የበጋ ስንዴ ልማት በይፋ ሲጀመር ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን በስንዴ ራሳቸውን ከመቻል አልፎ ወደ ውጭ ለመላክ የሚችሉበትን አቅም የሚፈጥር ነው::

ይሄ ሊሆን የማይችል የሚመስለው እውነትም በዚህ ዓመት ወደ ተጨባጭ እውነት የሚለወጥ ሲሆን፤ ይህ እንዲሆንና ለሂደቱ ስኬታማነት አመራሩና ባለድርሻ አካላት በቁርጠኝነት ሊሠሩ የተገባ ነው:: ምክንያቱም ሥራው የኢትዮጵያ ታሪክ የሚቀይር እንደመሆኑ፤ ይህ ታሪክ የሚቀየረው ደግሞ በልጆቿ ላብ በመሆኑ ነው:: እየለማ ያለው ስንዴም አስቀያሚ የነበረውን የኢትዮጵያና የስንዴ ታሪክ እጥፋት (ለውጥ) ማሳያ ነው። በዚህ መልኩ ከተሠራ እና ውጤቱን ማስቀጠል ከተቻለ ደግሞ፤ ኢትዮጵያ ከልመና ወደ መስጠት፤ ከመግዛት ወደ መሸጥ፤ ከድህነት ወደ ብልጽግና መሸጋገር ብቻ ሳይሆን፤ በድጋፍ ስም ከሚጫንባት ቀንበር ራሷን ማላቀቅ እና የዜጎቿን ክብር፣ የራሷንም ሉዓላዊነት አስጠብቃ መጓዝ የምትችልበትን ፈርጣማ አቅም ይፈጥርላታል::

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

# ተበደልን ያሉ መምህራን አቤቱታ

**ምሕረት ሞገስ**

የመንግሥት መመሪያ በተገቢው መንገድ ባለመተግበሩ በደል ተፈፅሞብናል ሲሉ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ቁጥራቸው 27 የሚሆኑ መምህራን ቅሬታቸውን ለማሰማት ወደ ዝግጅት ክፍላችን መጥተዋል። ጥያቄ አቅራቢዎቹ ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል በየደረጃው ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም ተገቢውን ምላሽ የሰጣቸው እንደሌለ በመግለጽ በደላችንን ሕዝብና መንግሥት ይወቀው ሲሉ የቅሬታቸው ምንጭ የሆነውን ጉዳይ ነግረውናል። ከቅሬታ አቅራቢዎቹ መካከል መምህር መንግሥቱ ቱፋ አንዱ ናቸው:: መምህር መንግሥቱ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በፍሬሕይወት ቁጥር 2 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማስተማር ላይ ይገኛሉ:: መምህሩ እንደሚናገሩት፤ በ2009 ዓ.ም በኪራይ መልክ ለአምስት ሺህ መምህራን የጋራ መኖሪያ ቤቶች ሲሰጥ እርሳቸውም የዕድሉ ተጠቃሚ ሆነዋል:: በዚህ ምክንያት ከአዲስ አበባ ቤቶች ኤጀንሲ ጋር የኪራይ ውል ተዋውለዋል:: እስከ 2011 ዓ.ም በውሉ ተመሥርተው ኪራዩን እየከፈሉ ቆይተዋል::

በ2011 ዓ.ም ደግሞ ሌላ አዲስ ዕድል አጋጠማቸው :: ይሄውም በ1997 ዓ.ም የተመዘገቡት የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣ ዕድለኛ ሆኑ:: 13ኛው ዙር የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ ሲወጣ የቤት ዕጣ ዕድለኛ ሲሆኑ ሁለት የጋራ መኖሪያ ቤት በእርሳቸው ስም ሊመዘገብ ሆነ:: በእርግጥ አንዱ ማለትም (የመምህራኑ ቤት) በኪራይ ስም ነው:: 2ኛው የ2011 ዓ.ም ደግሞ በስማቸው የወጣው የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣ ግን በግዢ ወደ እርሳቸው የሚተላለፍ ነው::

ቀድመው በኪራይ መልክ የተዋዋሉት ውሉ ሲፈፀም፤ በወጣው መመሪያ ቤት ከደረሳቸው ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው ተቀምጧል:: ስለዚህ ሪፖርት አደረጉ:: በጊዜው ማለትም በ2011 ዓ.ም በነበረው መመሪያ መሠረትም መምህሩ የቤት ኪራይ ተጠቃሚ ሆኖ መንግሥት በዘረጋው የቤት ልማት ፕሮግራም በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ስም የቤት ዕጣ ከደረሰው፤ ተመሳሳይ የቤት ዓይነት ከሆነና በኪራይ የያዙትን ቤት ከፈለጉ በወቅቱ በሚኖረው የቤት የማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረዥም ጊዜ ሽያጭ በስሙ እንዲተላለፍለት ይደረጋል የሚል በመሆኑ በረዥም ጊዜ ሽያጭ ቤቱን ለማግኘት ጥያቄ ማቅረብ መጀመራቸውን ይናገራሉ::

መምህር መንግሥቱ « መጀመሪያ በ13ኛ ዙር የጋራ መኖሪያ ቤቶች የቤቱ ዕጣ ሲወጣልኝ፤ በገባሁት የኪራይ ውል መሠረት ላለሁበት ወረዳ ቤቶች ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ማሳወቅ ግዴታ ነበረብኝ:: ስለዚህ ‹እኔ መምህር ነኝ:: የመምህራን የኪራይ ቤት ተጠቃሚ ነኝ:: አሁን ደግሞ ቤት ደርሶኛል:: ስለዚህ የቤቱን ልዋጭ እፈልጋለሁኝ:: › በማለት ላለሁበት ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 አመለከትኩኝ:: » ይላሉ::

ወደ ወረዳው ቤቶች ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ሔደው ማመልከታቸውን ተከትሎ፤ የወረዳው ባለሞያ ቤቱን ለመረከብ የሚያስፈልገው እና መሞላት ያለበት ቅፅ 9ኝ ላይ « የመምህራን ቤት ኪራይ ተጠቃሚ ናቸው» በማለት ከፃፈ በኋላ አሸጎ «ይዘህ ቦሌ ክፍለ ከተማ ሂድ» መባላቸውን ያስታውሳሉ::

የቦሌ ክፍለ ከተማ የቤት ዕድለኞችን የሚያስተናግደው በወረፋው ነው ተባሉ:: ታሽጎ የተሰጣቸውን ቅፅ 9ኝን ይዘው ለቀናት ተራቸውን ጠብቀው ወረፋቸው ሲደርሳቸው ሔዱ:: በሔዱበት ቀን ልክ እንደእርሳቸው አይነት ጉዳይ ያጋጠማቸው ከተለያዩ ክፍለ ከተሞች የተገኙ መምህራኖች ነበሩ:: በጊዜው 27 የሚደርሱ ሲሆን፤ በ2011 ተሻሽሎ በወጣው የመምህራን ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ የቤት መመሪያ ሰነድ መሠረት እንስተናገድ አሉ::

### መመሪያው

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርብ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለማስተላለፍና ማስተዳደርን በተመለከተ የተዘጋጀ ላይ እንደሚያመለክተው በአንቀፅ 20 ልዩ የተከራይ መብት በሚለው ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ መምህሩ እንዴት ቤቱን በሽያጭ ማግኘት እንደሚችል ያትታል:: አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 3 እንደሚያብራራው፤ መምህሩ የቤት ኪራይ ተጠቃሚ ሆኖ መንግሥት በዘረጋው የቤት ልማት ፕሮግራም በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ስም የቤት ዕጣ ከደረሰው፤ ተመሳሳይ የቤት ዓይነት ከሆነና በኪራይ የያዙትን ቤት ከፈለገ በወቅቱ በሚኖረው የቤት



የማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረዥም ጊዜ ሽያጭ በስሙ እንዲተላለፍለት ይደረጋል ይላል::

በንዑስ አንቀፅ 4 ላይ ደግሞ ተከራይ በኪራይ የያዘውን ቤት በረዥም ጊዜ ሽያጭ በስሙ እንዲተላለፍለት ከተደረገ አከራይ ተመሳሳይ የቤት አይነት በተለዋጭ የሚተካ ይሆናል ይላል:: መምህር መንግሥቱም በሰነዱ መሠረት በአንቀፅ 20 ላይ ቤቱ አቻ ከሆነ መምህሩ ተለዋጭ ቤት ለማግኘት ውል መዋዋል ይችላል ስለሚል ቤቱ በሽያጭ ይተላለፍልኝ አሉ:: በዕጣ የደረሳቸውን ቤትም ለአከራይ ማለትም ለቤቶች ልማት ኤጀንሲ እንደሚለቁ አሳወቁ::

በተጨማሪ በአንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ ተከራይ ሙሉ ዕድሜውን በመምህርነት እስከ ጡረታ ካገለገለ እስከዚያ የከፈለው ኪራይ ታስቦ ባለው መደበኛ አሠራር የቀሪውን የቤቱን ዋጋ በወቅቱ በሚኖረው የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረዥም ጊዜ ሽያጭ ቤቱ ይተላለፋል ይላል:: እዚህ ላይ የመምህራኑ ዋነኛ ጥያቄ በአንቀፅ 20 በንዑስ አንቀፅ 3 ላይም ሆነ በንዑስ አንቀፅ 1 ላይ ቤቱ መተላለፍ ያለበት በወቅቱ ዋጋ የሚለው በተለያየ መልኩ ተተግብሯል የሚል ነው::

### አቻ ቤት ስለመግዛት

መምህር መንግሥቱ ንፋስ ስልክ ቤት የደረሳቸው ባለአንድ መኝታ የጋራ መኖሪያ ቤት ነው:: 13ኛው ዙር የቤት ዕጣ ሲወጣ ኮዬ ፈጬም የደረሳቸው በተመሳሳይ መልኩ ባለአንድ መኝታ የጋራ መኖሪያ ቤት ነው:: መመሪያው ደግሞ አቻ ቤት ከሆነ መምህሩ ከሁለት አንዱን መርጦ በወቅቱ ዋጋ ውል በመግባት መግዛት ይችላል ይላል:: ይህንን መሠረት በማድረግ ኮዬ ፈጬ የደረሳቸው ቤት 2ኛ ፎቅ ላይ ሆኖ፤ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማው ደግሞ 4ኛ ፎቅ ላይ ቢሆንም በመምህርነታቸው ጊዜ የተሰጣቸውን መርጠዋል:: ቤቱን መርጠው በ2009 ዓ.ም ዋጋ መሠረት ለመዋዋል ተዘጋጁ:: ነገር ግን ያ ሊሆን አልቻለም:: የአቤቱታቸው መነሻም ይኸው ነው::

መምህር መንግሥቱ እንደሚገልፁት፤ የግዢ ውል ከመፈፀማቸው ቀደም ብሎ በተጨባጭ አሁንም በሕይወት ያሉና መናገር የሚችሉ ጡረታ የወጡ ከአንድም ሁለት አንጋፋ መምህራንን አግኝተው አነጋግረዋል:: እርሳቸው በሽያጭ ከመግዛታቸው በፊት ጡረተኞች ቤቱን ሲገዙ የከፈሉት የቤት ኪራይ ተይዞላቸው ቤቱን ሲረከቡ የነበረው በ2009 ዓ.ም የዋጋ ተመን መሠረት ነበር:: ጡረተኞች በ2009 ማስተላለፊያ ዋጋ የተላለፈላቸው የከፈሉት ኪራይም ተቀንሶላቸው ነው:: ያ ተገቢ ነው:: ነገር ግን ለእነርሱ እንደጡረተኞቹ የከፈሉት የቤት ኪራይ ባይታሰብም፤ መመሪያው ላይ እንደተቀመጠው ነገር ግን ቤቱ ሊተላለፍላቸው ይገባ የነበረው በ2009 ዓ.ም ታሪፍ መሠረት መሆን ነበረበት ይላሉ::

መመሪያው ላይ ምንም እንኳ እነመምህር መንግሥቱ ጡረታ ባይወጡም በ2011 ዓ.ም የቤት ዕጣ የወጣላቸው በመሆኑ ለአቻው ቤት መክፈል ያለባቸው ልክ እንደጡረተኞቹ ሁሉ በወቅቱ ዋጋ መሆን እንዳለበት በግልፅ ተቀምጧል:: ነገር ግን የቤቶች ልማት ኤጀንሲ እነመምህር መንግሥቱን በዛ መንገድ አላስተናገዳቸውም:: ይልቁኑ በአምስት ቀን ውስጥ በአስቸኳይ ቤቱን ለማግኘት በ2011 ዓ.ም ዋጋ ተመን መሠረት እንዲከፍሉ ያዘዘ መሆኑን ያስረዳሉ::

እነመምህር መንግሥቱም ቤቱን እንዳያጡ በመስጋትና ነገ የሚመጣው አይታወቅም ብለው እንደምንም ተሯሩጠው ገሚሱ ቅድመ ክፍያውን ማለትም 20 በመቶውን፤ የቻለ ደግሞ ሙሉ ክፍያውን በ2011 ዓ.ም ዋጋ ተመን መሠረት ከፈሉ:: እንደርሳቸው ሁሉ ቀሪውን 80 በመቶ በባንክ ወለድ እየከፈሉ ያሉም አሉ:: መምህር መንግሥቱ በዚህ ምክንያት ምን ያህል እየተጎዱ እንደሆነ ሲያመለክቱ፤ ለምሳሌ በ2009 ውል ተዋውለው ቢሆን ኖሮ ክፍያው 187 ሺህ ብር ብቻ ይሆን ነበር:: ነገር ግን በ2011ዓ.ም ተመን ክፈል በመባላቸው 248 ሺህ ብር እንዲከፍሉ ተገድደዋል::

ስለዚህ ከባንክ ጋር ሲዋዋሉ ወርሐዊ ክፍያው 420 ብር ነበር:: ከአንድ ዓመት ዕረፍት በኋላ ሲሔዱ ግን 2600 ብር ተደርጓል:: ወደ ፊትም ይጨምራል:: ይህ እርሳቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ መልኩ ቃሊቲ አካባቢ እንደርሳቸው ተመሳሳይ ሁኔታ ያጋጠመው መምህር ለተመሳሳይ ቤት 2500 ብር እየከፈለ ነው:: አሁን በቅርቡ የተዋዋሉት ግን በ2009 ዓ.ም ተመን መሠረት የሚከፍሉ በመሆናቸው ልዩነቱ ብዙ ነው:: ስለዚህ በተመሳሳይ ሙያ ላይ እየሠሩ አቻ ቤት ገዝተው የሚከፍሉት ግን የተለያየ አንዳንዴም ድብልቅልቅ ያለ መሆኑን ይናገራሉ:: ስለዚህ ጥያቄያውን እስከ ካቢኔ ጽሕፈት ቤት ለማቅረብ ተነጋግረው ሲንገታገቱ ሌላ ነገር መጣ፡፤

### በድጋሚ ጥያቄ

እንደመምህር መንግሥቱ ገለፃ፤ ቀደም ሲል የመምህራን የቤት ኪራይ የነበረው ሽያጭ የሚፈፀመው ለጡረተኞች ብቻ ነበር:: ተጨማሪ ደግሞ እንደርሳቸው አይነት የጋራ መኖሪያ ቤት ዕድለኛ ለሆኑ ሰዎች በተለዋጭነት የደረሳቸውን ቤት ሰጥተው አቻውን ይገዙ ነበር:: አሁን በቅርቡ የተከራዩ መምህራኖች ቤቱን ይግዙ ሲባል ደግሞ ለ5ሺ መምህራኖች በ2009 ዓ.ም ታሪፍ መሠረት ቤቱ በሽያጭ ይተላለፍላቸው ተባለ:: እስከ ጡረታ በኪራይ እንዲኖሩ የነበረው ደንብም ሆነ መመሪያ እንዲሁም ውሉም በሙሉ ተጥሶ ሌላ ማስተላለፊያ ደንብ ተዘጋጀ:: ከዛ ውስጥ ጡረታ የወጡም ሆኖ እንደእነርሱ ዓይነት ቤቱን ጠቅልሎ በልዋጭ የገዛው (የወሰደው) ሳይለይ ሁሉም በ2009 ዓ.ም ዋጋ ቤቱን ይውሰድ ተባለ::

ስለዚህ አሁንም ድረስ በወለድ ለቤቱ ሽያጭ እየከፈሉ ያሉት እነመምህር መንግሥቱ «ይህ እኛን ይመለከተናል» ብለው ጥያቄ አቀረቡ:: እንደሁሉም መምህራን ቤቱን በኪራይ መልክ የተዋዋሉት 2009 ዓ.ም ስለሆነ ለሽያጭም መዋዋል ያለባቸው በ2009 ዋጋ ተመን መሠረት መሆን ነበረበት ብለው ተከራከሩ:: ያንን መሠረት አድርገው የሚመለከተው እና መምህራንን ወክሎ ሊከራከርላቸው ይችላል ወደተባለው የሙያ ማኅበር ሄዱ:: እንዲሟገትላቸው ብዙ ጥረት አደረጉ::

መምህር መንግሥቱ እንደሚናገሩት፤ መጀመሪያ ቤቱ በኪራይ መልክ ሲሰጣቸው የመሰላቸው ትምህርት ቢሮ ቤቶቹን ገዝቶ ለመምህራን እንዳከፋፈለ ገምተው ነበር:: ስለዚህ ዋጋውን በሚመለከት ትክክለኛው አሠራር እንዲተገበር ሲሉ ትምህርት ቢሮ አመለከቱ:: ሆኖም አልሆነም:: ቤቱን ትምህርት ቢሮ ሳይሆን የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ጉዳይ መሆኑን ሲያውቁ ይህንን መሠረት አድርገው በ12/08/2013 ተነጋግረው ግንቦት 2013 ላይ ለሙያ ማኅበሩ ደብዳቤ ፅፈው የሙያ ማኅበሩ ጥያቄውን እንዲያቀርብላቸው አመለከቱ:: በወቅቱ ለማኅበሩ ፕሬዚዳንት አስረድተው እና በደንብ ተናግረው ማመልከቻውን ሲያስገቡ፤ የማኅበሩ ፕሬዚዳንትም የሚመለከተውን አካል እንደሚያነጋግሩ ገለፁላቸው::

እንደመምህር መንግሥቱ ገለፃ፤ ለሙያ ማኅበሩ ብቻ ሳይሆን ለከተማው ቤቶች ልማት ኤጀንሲም መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ.ም አመልክተዋል:: ሆኖም ምላሽ አላገኙም:: ቤቶች ኤጀንሲ በቃል የሰጠው ምላሽ ቢኖር «እኔ የሠራሁት በመመሪያው መሠረት ነው:: ምንም ዓይነት የጣስኩት መመሪያ የለም » የሚል ብቻ ነበር::

እነመምህር መንግሥቱ ደግሞ በበኩላቸው፡ ኤጀንሲው እነርሱን ያስተናገደበት መንገድ ፍትሐዊ አይደለም:: ነገር ግን ይሄ መንገድ ትክክል ከሆነ፤ አሁን ሌሎች በ2009 ዓ.ም ቤቶቹን ለተከራዩ መምህራን የተላለፈበት መንገድ ትክክል አይደለም:: ምክንያቱም መመሪያው በወቅቱ ስላለ ከእነርሱ በኋላ የሽያጭ ውል ለፈፀሙ መምህራን በ2009 ዓ.ም ዋጋ ማስተላለፋቸው ተገቢ አይደለም:: ስለዚህ አሠራሩ አንድ ዓይነት መሆን ነበረበት:: እነርሱ ላይ የተፈፀመው ትክክል ካልሆነ ማስተካከል ወይም የአሁኖቹን በአሁኑ ታሪፍ መሠረት ማዋዋል እና ሽያጭ መፈፀም ሲገባ የተለያየ ክፍያ መፈፀሙ ፍትሃዊነት የጎደለው ነው ባይ ናቸው::

እነመምህር መንግሥቱ ይህንን መሠረት በማድረግ እስከ መምህራን ማህበር ድረስ ሔደው መሟገት ጀመሩ:: በእርሳቸው በኩል ለክፍለ ከተማው መምህራን ማኅበርም ጥያቄያቸውን አቅርበዋል:: ነገር ግን ከአዲስ አበባ መምህራን ማኅበርም ያገኙት ምላሽ በቅድሚያ ሌሎቹ ውሉን ተዋውለው ይጨርሱ ከዛ የእናንተ ይቀጥላል መባላቸውን ይናገራሉ:: በኋላም እንደመምህር መንግሥቱ ተመሳሳይ ተበድለናል ያሉ መምህራን እርስ በእርስ ተነጋግረው፤ ሁላችንም ግር ብለን ከምንሔድ እና የመንግሥት ሥራ ከምንበድል የተመቸው ሰው እየመጣ ሒደቱን ይከታተል ተባብለው በዛ መሠረት መከታተል ጀመሩ::

በዛ መሠረት ምላሽ ሲያጡ በየካቲት 2014 ዓ.ም መምህራን ማኅበሩ ጋር በድጋሚ ሔደው ሲጠይቁ የተሰጣቸው ምላሽ «ለተወካያችሁ በቴሌግራም ጥሪ አቅርበን ነበር» ተባሉ:: ነገር ግን በቴሌግራም ጥሪ የተደረገው ከ5ሺው መካከል ክፍያቸውን በተለያየ ምክንያት ያላከናወኑ እና ውል ያልተዋዋሉ መምህራን የጊዜ ይራዘምልን ጥያቄ አቅርበው ስለነበር እነርሱ ስለተፈቀደላቸው ለእነርሱ ጥሪ ቀርቧል:: ጥሪው እነርሱን እንጂ እነርሱን እንደማይጋብዝ መምህር መንግሥቱ ይናገራሉ::

«ቀድሞም ቢሆን የወከልነው ሰው የለም:: የወከልነው ሰው ሳይኖር ለተወካያችሁ ጥሪ አስተላልፌያለሁ» የሚል ምላሽን የመምህራን ማኅበሩ መስጠቱን ተከትሎ ሰዎች ተስፋ ቆርጠው መበታተናቸውን መምህር መንግሥቱ ያስረዳሉ:: ማኅበሩ እንደው በእውነት ተወካይ ለማነጋገር ከሞከረ ምንም እንኳ የተወከለ ባይኖርም የአንዱ ሰው ስልክ እምቢ ቢል ለሌላው ሰው መደወል ነበረበት:: » ሲሉ ያስረዳሉ::

እንደመምህር መንግሥቱ ገለፃ፤ በዚህ ምክንያት ቅሬታ ላላቸው መምህራን ስልክ እንኳ ሲደውሉ ፈቃደኛ የሚሆን ጠፋ፤ ሁሉም ተስፋ ቆረጡ:: ምክንያቱም ፍርድ ቤት ለመሔድ አቅም የለም:: ስለዚህ ቢያንስ ሕዝብ ይወቀው በማለት ወደ መገናኛ ብዙኃን መጥተዋል::

ሌላኛዋ አቤቱታ አቅራቢ መምህርት ዘውድነሽ መለስ በቀለመወርቅ ጥሩነህ ትምህርት ቤት ሾላ አዲሱ ገበያ አካባቢ በማስተማር ላይ ይገኛሉ:: መምህርት ዘውድነሽ በበኩላቸው እንደሚገልፁት፤ እርሳቸውም ለመምህራን ቤት በኪራይ ሲሰጥ እንደመምህር መንግሥቱ ሁሉ ጀሞ አካባቢ ቤት አግኝተው ተከራይተው ሲኖሩ ነበር፡ ፤ በመሐል በ1997 ዓ.ም የተመዘገቡት የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣ በ2011 በ13ኛው ዙር እንደወጣላቸው ሰሙ::

በዛ ጊዜ መምህራን የተከራዩትን ቤት እንዲገዙ አመራሩ ውይይት ቢያደርግም እነርሱ ግን ባለማወቃቸው በመመሪያው መሠረት የደረሳቸውን ቤት ወደ ኪራዩ ማዘዋወር መብታችሁ ነው በመባላቸው የደረሳቸውን ቤት ትተው የተከራዩትን ቤት ለመግዛት ለቤቶች ልማት ኤጀንሲ አሳወቁ::

«እንደአንዳንድ ሰዎች ሁለት ቤት የምናገኝበት ሁኔታ ቢያጋጥመንም አጭበርብረን ለመሸጥ አላሰብንም፤ ምክንያቱም ጓደኞቻችን ሽንት ቤትና ማዕድቤት

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

ተከራይተው እየኖሩ እያየን የመሸጥ ሞራል ስላልነበረን አንዱን እናስረክብ አልን:: » የሚሉት መምህርቷ፤ በመመሪያው መሠረት አንዱን አስረክበው ሌላውን ሲወስዱ ቤቱን የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኤጀንሲ በቀድሞ ዋጋ ማለትም በ2009ዓ.ም ታሪፍ መሠረት ማስተላለፍ ሲገባው በአዲሱ ዋጋ እንዲወስዱ ማድረጉ ፍፁም ግፍ መሆኑን በምሬት ይናገራሉ::

« አቤቱታ ለማቅረብ ብንፈልግም የትም ቦታ ሔደን የሚያነጋግረን የለም:: ‹ቤቶች ኤጀንሲ የሠራነው በመመሪያው መሠረት ነው› አለ:: ሌላ ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ አይደለም:: ነገሩን ትምህርት ቢሮ፣ መምህራን ማኅበርም ሆነ ቤቶች ልማት ተገቢውን ምላሽ ሳይሰጥ፤ በመጨረሻ አሁን ደግሞ ሁሉም የተከራየው መምህር በ2009 ዓ.ም ታሪፍ መሠረት ቤቱን ይግዙ ተባለ ይላሉ::

በእነርሱ በኩል « እኛም ጥያቄ እያቀረብን ነበር:: እኛም መስተናገድ ያለብን በ2009 ዓ.ም ዋጋ ነው» ብለው ቢጠይቁም መምህራን ማኅበሩ «ቀድማችሁ መዋዋል አልነበረባችሁም፤ መተው ነበረባችሁ» ያላቸው መሆኑን ይናገራሉ:: ጠበቃ ጋር ሲሔዱ ማሸነፍ እንደሚቻል ቢያሳይም ሁለት ዓመት ይፈጃል ሲባል ተጎጂ እሆናለሁ ብለው በመገመታቸው ጉዳዩን እንዳቆሙት ይጠቁማሉ::

እንደመምህርቷ ገለፃ፤ በወቅቱ የኪራይ ቤቱን የማግኘት ዕድል በዚህ መልኩ የሚከናወን ስላልመሰላቸው በዕጣ የደረሳቸውን 66 ካሬ ሜትር የጋራ መኖሪያ ቤት ትተው የወሰዱት 44 ካሬ ሜትር የሆነውን በኪራይ አግኝተውት የነበረውን ቤት ነው:: ነገር ግን አሁን ለ44 ካሬ ሜትር እየከፈሉ ያሉት ግን ለ66 ካሬው መሆን የሚችል ነበር::

«የቤቶች ልማት ኤጀንሲ የ2011 መምህራን የቤት ዕድለኞችን ያለአግባብ ከሌሎቹ በተለየ መልኩ ከ50ሺህ ብር ጀምሮ ተጨማሪ ዕዳ ከፋይ አድርጎናል:: ለእዚህም ማንንም ብንጠይቅም ኃላፊነት የሚወስድ የለም:: የአሁኑ ውሳኔ ደግሞ እኛንም ያማከለ ቢሆንም የሚያስተናግደን የለም:: በተለይ ቤቶች ኤጀንሲ መመሪያው አይመለከታችሁም እያለ ነው:: ሊያስተናግደን የወደደ ባለመኖሩ ተስፋ ቆርጠናል:: » ሲሉ ቅሬታቸውን አሰምተዋል::

## የአዲስ አበባ መምህራን ማኅበር ምላሽ


የአዲስ አበባ መምህራን ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ድንቃለም ቶሎሳ ከመምህራኑ የቀረበውን አቤቱታ አስመልክቶ ላነሳነው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ፤ መንግሥት በዝቅተኛ የቤት ኪራይ ዋጋ ለመምህራን በ2009 ዓ.ም ቤት ሰጥቷል:: ቤቱ ሲሰጥ አገልግሎትን መሠረት ያደረገ መስፈርት የነበረ ነው ። ከ16 ዓመት በላይ አገልግሎት የነበራቸው ቤት የሌላቸው ከ70 በመቶ በላይ መምህራን እንዲያገኙ ተደርጓል:: 30 በመቶ የሚሆነው ደግሞ የቤተሰብ ቁጥርን ማዕከል በማድረግ ከአራት ቤተሰብ በላይ ያላቸው ባለሁለት መኝታ፤ አንድ ልጅ ያላቸው ባለ ሶስት ቤተሰብ ባለአንድ መኝታ፤ ትዳር ያላደረጉ ስቱዲዮ እንዲከራዩ ተወስኖ ተሰጥቷል::

ከ2009 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 2013 ዓ.ም ድረስ በየቤት ዓይነቱ እንደየተመኑ ኪራዩን እየከፈሉ ኖረዋል የሚሉት አቶ ድንቃለም፤ « ቀደም ሲል እኛ ጥያቄ እያቀረብን ነበር:: አንደኛው ጥያቄ ከአምስት ሺ ሌላ ለሌሎችም ቤቶች ሌሎች መምህራኖች ቤት ይሰጥ እያልን ነበር:: በተጨማሪ ‹5ሺው መምህራን ቤቱ በኪራይ ብቻ መሆኑ በቂ አይደለም:: ወደ እኛ መዘዋወር አለበት› የሚል ጥያቄ ነበራቸው:: ይህንን ተከትሎ በ2013 ዓ.ም ከተማ አስተዳደሩ የካቢኔ ስብሰባ በማካሔድ መምህራን በኪራይ የያዟቸውን ቤቶች በግዢ ወደ ስማቸው እንዲያዞሩ ውሳኔ አስተላልፏል:: » ሲሉ ሂደቱን ያብራራሉ::

ትምህርት ቢሮ፣ መምህራን ማኅበር እና የከተማው ቤቶች ልማት ኤጀንሲ ተገናኝተው የጋራ ሰነድ በማዘጋጀት ጥቅምት 2014 ዓ.ም ላይ ቤቱን ማስተላለፍ ተጀመረ:: ቤቶቹ ሲተላለፉ የወጡ 26ት አካባቢ መስፈርቶች እንደነበሩ በማስታወስ፤ በዛ መሠረት ቤቱን የማስተላለፍ ሥራውን ሲያከናውኑ መቆየታቸውን ያስረዳሉ::

መንግሥት ያሳለፈው ውሳኔ ቤቱ ይተላለፍላቸው የሚል ብቻ ነበር:: ማኅበሩ ግን ለመምህራን ቤቱ መተላለፍ ያለበት በኪራይ ሲተላለፍላቸው በነበረበት ወቅት በነበረ የቤት ሽያጭ ዋጋ መሆን አለበት አለ:: ምክንያቱም መመሪያው ላይ በወቅቱ የሚል ቃል ስለነበረ ቤቱ አሁን ባለው የዋጋ ተመን ከተላለፈ መምህራንን የሚጎዳ በመሆኑ መተላለፍ ያለበት በ2009 ዓ.ም ዋጋ ተመን መሠረት ሊሆን ይገባል የሚል ሃሳብ ያቀረቡ መሆኑን ይገልፃሉ::

ካቢኔውም መምህራን አገርን እያገለገሉ በመሆናቸው በ2009 ዓ.ም ዋጋ መሠረት እንዲተላለፍ ወሰነ:: ዘመናቸውን በሙሉ በዝቅተኛ ደመወዝ አገራቸውን ሲያገለግሉ የኖሩ ለጡረታ የቀረቡ መምህራን ይህም ቢሆን ሊፈትናቸው ይችላል:: ስለዚህ ለአገልግሎታቸው ሲባል ብዙም ባይመጥናቸውም እነርሱን ለመደገፍ በማሰብ



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ
የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA
HOUSING DEVELOPMENT AND ADMINISTRATION BUREAU
HOUSING DEVELOPMENT CORPORATION

Date መጋቢት 2-9-2013 Ref.no /ቤ/ል/ኮ/ ቀ1/19/8938

ለአቤቱታ አቅራቢ መምህራን
አ/አበባ


ጉዳዩ፡- ለቀረበዉ ቅሬታ/አቤቱታ ከመመሪያ አንጻር መልስ መስጠትን ይመለከታል

በቀን 02/07/13 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ከአሁን በፊት ለመምህርን መንግስት ባመቻቸዉ ፕሮግራም በኪራይ ጋራ መኖሪያ ቤት አግኝታችሁ እየኖራችበ ት መሆኑን በምለጽ በጋራ መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ተመዝግባችሁ ስትጠባበቁ በ13ኛዉ ዙር እጣ ባለ እድል መሆናችሁን በመግለጽ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለማስተላለፍና ለማስተዳደር በወጣዉ መመሪያ ቁጥር 1/2011 ክፍል 4 በአከራዩና ተከራዩ መብትና ግዴታ በተዘረዘረዉ ቁጥር 20 ልዩ የተከራይ መብት ንኡስ ቁጥር 3 ላይ በተገለጸዉ መሰረት፣ መምህሩ የቤት ኪራይ ተጠቃሚ ሆኖ መንግስት በዘረጋዉ የቤት ልማት ፕሮግራም በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ስም የቤት እጣ ከደረሰዉ ተመሳሳይ የቤት ዓይነት ከሆነና በኪራይ የያዙትን ቤት ከፈለጉ በወቅቱ በሚኖረዉ የጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጂም ጊዜ ሽያጭ በስሙ እንዲተላለፍለት ይደረጋል ይላል ነገር ግን በ13ኛው ዙር ቤት ደርሶን ቅያሬ በመጠየቅ በመመሪያው መሰረት መዋዋል ሲገባን፡-

1. በ13ኛዉ ዙር የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ እንድንዋዋል መደረጋችን መመሪያዉን የጣሰ በመሆኑ፣
2. በተለያዩ ዙሮች የተላለፉ ቤቶችን በአንድ አይነት የማስተላለፊያ ዋጋ እንድንከፈፍል መደረጋችን፣
3. ሙሉ እድሜውን በመምህርነት እስከጡረታ እያገለገለ ያለዉን መምህር ተጠቃሚነት ያላገናዘበ እና መመሪያ ተራ ቁጥር 20 ንኡስ ቁጥር አንድን ከግመምት ውስጥ ያላስገባ አሰራር እየተሰራ መሆኑ፣
4. ተመሳሳይ የቤት ዓይነት በተለዋጭ ተተክተዉ ለሌላ ለሚተላለፍለት ወገን የማስተላለፊያ ዋጋ እና እየኖርንበት ያለዉ ኮንዶምኒየም የተላለፈበት ዋጋ ከግምት ውስጥ ያለስገባ በመሆኑ የከተማ አስተዳደሩ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርቡ መኖሪያ ቤቶች በወጣዉ መመሪያ መሰረት እንዲያዋዉለንና እና በወቅቱ በሚኖረዉ የማስተላለፊያ ዋጋ እንድንከፍል ስንል በሙሉ ድምጽ በፊርማችን በማረጋገጥ እናመለክታለን በማለት በጠየቃችሁት መሰረት፡-

ሁሉም ጥያቄዎቻችሁ በአንድ ጉዳይ ላይ ማለትም በወቅታዊ የጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፊመያ ዋጋ እንድንከፍል መደረጉ መመሪያ የጣሰ ስራ ተፈጽሞብናል የሚል እና የመምህራንን ተጠቃሚነት ያላገናዘበ አሰራር እየተሰራ ነው የሚል ነዉ።ይሁንና ተቋሙ በመመሪያና አሰራር የሚመራ በዚህም መሰረት በ13ኛዉ ዙር የጋራ መኖሪያ ቤት እጣ እድለኞች ሆነዉ በኪራይ ከያዙት ቤት ጋር ተመሳሳይ ለሆነ መምህራን በእጣ የደረሰን ቤት ተመላሽ ተደርጎ በኪራይ የተሰጠን ቤት በመመበሪያዉ መሰረት በሽያጭ ይተላለፈፍልን ብላችሁ ባቀረባችሁት ጥያቄ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቅርቡ ቤቶች ለማስተላለፍና ለማስተዳደር በወጣዉ መመሪያ ቁጥር 1/2011 ክፍል አራት፡-

-0118-33-35-53 ዜጐችን የቤት ባለቤት በማድረግ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እናረጋ ግጣለን0118-12-23-65E-Mail
aahdpo@telecom.net.et
0118 12234 75



1. አንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጽ 1 «ተከራይ ሙሉ እድሜዉን በመምህርነት እስከ ጡረታ ካገለገለ እስከዚያ የከፈለዉ ኪራይ ታስቦ ባለዉ መደበኛ አሰራር የቀሪዉን የቤቱን ዋጋ በወቅቱ በሚኖረዉ የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጅም ጊዜ በሽያጭ ቤቱ ይተላለፍለታል» በሚለዉ መሰረት እየተሰራ መሆኑ፣
2. በዚሁ እንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 «መምህሩ በቤት ኪራይ ተጠቃሚ ሆኖ መንግስት በዘረጋዉ የቤት ልማት ፕሮግራም በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ስም የቤት እጣ ከደረሰዉ ተመሳሳይ የቤት ዓይነት ከሆነና በኪራይ የያዙትን ቤት ከፈለጉ በወቅቱ በሚኖረዉ የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጅም ጊዜ ሽያጭ በስሙ እንዲተላለፍለት ይደረጋል» በሚለው እና ባቀረባችሁት ጥያቄ መሰረት እንድትስተናገዱ የተደረገ ሲሆን በወቅቱ በሚኖረው የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ማለት አሁን ያለዉን ማለት ስሆን በዚህም መሰረት በ13ኛዉ ዙር የጋራ መኖሪያ ቤት በተወሰነዉ የካሬ ማስተላለፊያ ዋጋ መሰረት እንድትከፍሉ መደረጉ ትክክለኛ በመመሪያዉ እና በላዉ አሰራር መሰረት የተሰራና እየተሰራ ያለ መሆኑን እናሳዉቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ካሳሁን ዘውዴ ሁሪሳ
የጋራ መኖሪያ ቤቶች ማስተላለፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ
- ለዋና ዳይሬክተር
- ለቤ/ማስ/አስ/ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለኮርፖሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፍ ቡድን

ቤ/ል/ኮ

-0118-33-35-53 ዜጐችን የቤት ባለቤት በማድረግ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እናረጋ ግጣለን0118-12-23-65E-Mail
aahdpo@telecom.net.et

ካቢኔው ውሳኔውን ካስተላለፈበት ቀን ጀምሮ ቤቱን እስከሚረከቡበት መጨረሻ ቀን ድረስ ጡረታ የሚወጡ መምህራን የቤት ኪራይ ተመላሽ ይሆንላቸዋል የሚል ውሳኔም የተላለፈ መሆኑን ያስረዳሉ:: ለሌሎች ግን 2009 ዓ.ም ላይ በነበረው ዋጋ ይተላለፍላቸው ተብሏል የሚሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በዛው መሠረት ከሐምሌ 3 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 2014 ዓ.ም ድረስ ጡረታ የሚወጡ መምህራኖች የቤት ኪራዩ ታስቦ ከሽያጩ ላይ እንዲቀነስላቸው የተደረገ መሆኑን ይናገራሉ::

ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ለማኅበሩ ፕሬዚዳንት ለመምህራን 5 ሺዎቹ ቤቶች ይተላለፉ የሚል ውሳኔ ከመተላለፉ በፊት ቤቱ የተሸጠላቸው መምህራኖች ነበሩ:: ይህንን አታውቁም? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ከዛ በፊት ቤቱ የተላለፈላቸው መምህራኖች በማን እውቅና ቤቱ እንደተላለፈላቸው አናውቅም:: ውሳኔው የተላለፈው ሐምሌ 3 ቀን 2013 ዓ.ም ነው:: ከዛ በፊት ያዘዋወሩትን ማኅበሩ አያውቅም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል::

የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ከዛ በፊት ሊያዘዋውሩበት የሚችሉበት መመሪያ አልነበረም ብለዋል:: ነገር ግን ከላይ እንደገለፅነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርብ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለማስተላለፍና ማስተዳደርን በተመለከተ በተዘጋጀ መመሪያ ላይ የቤት ተከራይ መምህራን ዕጣ ከደረሳቸው ቤቱን በሽያጭ የሚያገኙበትን ሁኔታ በአንቀፅ 20 ላይ አስቀምጧል::

የመምህራኑን አቤቱታ በዝርዝር ያቀረብንላቸው የማኅበሩ ፕሬዚዳንት፤ በሌላ በኩል የ2011 ዓ.ም የቤት ዕጣ የወጣላቸው መምህራን በ2011 ዓ.ም ታሪፍ ስለከፈሉ ሌሎቹም ሁሉም በ2011 ዓ.ም ታሪፍ መሠረት ይክፈሉ የሚል አቋም የለንም ይላሉ:: በወቅቱ ዕጣው የወጣላቸው መምህራኖች የሚያዋጣቸውን የመረጡ መሆኑን በመግለፅ፤ የአሁኖቹ በ2013 ዓ.ም ቤቱን የገዙ መምህራኖች በ2009 ዓ.ም ታሪፍ ቤቱን በማግኘታቸው እንጂ፤ እነኚህኞቹ በ2013 ዓ.ም ታሪፍ ቤቱን ቢገዙ ኖሮ ጥያቄ ከማንሳት ይልቅ ተጠቃሚ ነን ሲሉ ጉዳዩን ያልፉት ነበር የሚል ምላሽ ሰጥተዋል::

ማኅበሩ ከዛ በፊት የሆነውን ነገር ወደ ኋላ ሔዶ እንደዚህ አድርጉ ብሎ ጥያቄ ለማቅረብ ለእርሱ በጣም አስቸጋሪ ነው ሲሉ መግለፃቸውን ተከትሎ፤ የዝግጅት ክፍሉ መምህራን ወደ እናንተ መጥተው አቤቱታ አላቀረቡም ወይ? በሚል ላቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የትኛው እንደሆነ ባይገባቸውም በ13ኛ ዙር የወጣው የቤት ዕጣን በሚመለከት የቀረበ አቤቱታ እንደነበር ያስታውሳሉ:: ያንን በተመለከተ ከቤቶች ልማት ጋር ተነጋግረናል የሚሉት አቶ ድንቃለም፤ ቤቶች ልማት ኤጀንሲ የገለፀው « እነዚህ መምህራን ማመልከቻ ፅፈው አስገብተዋል:: በ13ኛው ዙር የቤት ዕጣ የወጣልን ቢሆንም በመምህርነታችን በኪራይ መልክ ላገኘነው ቤት የማፅኛ ወጪ ስላወጣን የመምህራኑን ቤት በስማችን አዘዋውሩልን የሚል ጥያቄ አቅርበዋል:: ሆኖም ኤጀንሲው የመምህራን ቤትን ማዘዋወር አንችልም፤ እኛ የተባልነው አከራዩ በመሆኑ አንችልም» የሚል መልስ መስጠቱን እንደገለፀ ተናግረዋል::

መምህራኖቹ የቤቶች ልማት ኤጀንሲ የሰጠውን ምላሽ ተከትሎ «ዓላማችሁ እኛን መጉዳት ነው:: » በማለታቸው፤ ቤቶች ልማት ማመልከቻ እንዲጽፉ ጠይቆ በራሱ መመሪያ መሠረት ማመልከቻ አስጽፏቸው በስማቸው አስተላልፎላቸዋል› የሚል ምላሽ የተሰጣቸው መሆኑን ገልፀዋል::

አቶ ድንቃለም በሌላ በኩል በመመሪያው መሠረት መምህራን በዕጣ አቻ ቤት ከደረሳቸው የፈለጉትን መርጠው መውሰድ ይችላሉ የሚል መመሪያ በመኖሩ በዛ ምክንያት መርጠው ወስደዋል በማለት፤ ካቢኔው 5ሺውን ቤት ለመምህራን ከመወሰኑም በፊት ቤቱ ለመምህራን ሲተላለፍ እንደነበር ይናገራሉ:: እንደማኅበሩ ፕሬዚዳንት ገለፃ፤ ቤቶች ልማት በ2009 ዓ.ም ታሪፍ መሠረት አስተላልፉ የሚል መመሪያ በወቅቱ ስላልነበር ጥያቄውን አስተናግደናል የሚል ምላሽ የሰጣቸው መሆኑን ይናገራሉ::

እንደማብራሪያቸው ጉዳዩ ለቤቶች ልማት ኤጀንሲም ሆነ ለመምህራኑ ለሁለቱም አስቸጋሪ ነው:: መምህሩ አቻው መምህር የተሻለ ተጠቃሚ ሆኗል:: ይህ ፍትሐዊ አይደለም፤ ይላል:: በሌላ በኩል ደግሞ ኤጀንሲው «እኛ ቤቱን በስማችሁ አዙሩ ብለን አላስገደድናቸውም ራሳቸው ማመልከቻ ጽፈው ጠይቀው ቤቱ በስማቸው በመሆኑ ወደ ኋላ ብለን መሥራት አንችልም» ብሏል:: ቤቶቹ በቦንድ ብድር የተሠሩ በመሆናቸው ወደ ባንክ ብድር ስለተከፈለ ወደ ኋላ ተመልሰን በ2009 ዓ.ም ታሪፍ ልናደርግ የምንችልበት ዕድል የለም ማለታቸውን አቶ ድንቃለም ገልፀዋል::

የዝግጅት ክፍሉ ቀድሞም ቢሆን መምህራኑ ቤቱን የተከራዩት በ2009 ዓ.ም መሆኑን በመጥቀስ፤ በዛ ጊዜ በመመሪያው በዕጣ ቤት ያገኘ በወቅቱ የነበረውን የዋጋ ተመን ከፍሎ አንዱን ቤት መውሰድ ይችላል ስለሚል በዚህ መልኩ አስተናግዱን የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡም ምላሽ አላገኙም:: እናንተ ከመመሪያው አንፃር በወቅቱ የሚለውን መመሪያው ውስጥ ያለውን ቃል መሠረት በማድረግ ለምን አልተከራከራችሁላቸውም? የሚል ጥያቄም ያቀረበላቸው ሲሆን፤ የመምህራን ማኅበር ፕሬዚዳንቱ እንደተናገሩት፤ ቃሉን በመጥቀስ ከመምህራን ማኅበር ጋር ተገናኝተው ተነጋግረዋል:: ነገር ግን በመመሪያው በወቅቱ የሚለው ቃል የተተረጎመው አሁን ካቢኔው ሲወስን ማኅበሩ መምህራንን ተጠቃሚ ለማድረግ በማሰብ በወቅቱ የሚለው ቃል ቤቱ በተከራዩበት ዘመን የጠቀሰ እንዲሆን ተወሰነ:: በፊት ግን በወቅቱ የሚለው ቃል አወዛጋቢ ነበር ይላሉ::

እንደአዲስ አበባ መምህራን ማኅበር ፕሬዚዳንት ገለፃ፤ ከዛ በፊት ግን በወቅቱ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የጊዜውን ዋጋ ሲሆን፤ ጡረታ የወጡ መምህራኖች ሲስተናገዱ የነበረው በ2009 ዓ.ም ዋጋ ሳይሆን ጡረታ በወጡበት ዕለት በነበረው ዋጋ መሠረት ነው:: ከሐምሌ 2013 ዓ.ም በፊት ጡረታ የወጡ መምህራኖች በዚህ ወቅት የነበረውን ዋጋ እየከፈሉ ሲስተናገዱ ቆይተዋል:: ይህን አቤቱታ ያመጡ መምህራን ከሐምሌ 2013 ዓ.ም በፊት ጡረታ ሲወጡ የነበሩ መምህራን በወቅቱ የሚለው ቃል የ2009 ዓ.ም ትርጉም ተሰጥቶት በዛ መልክ ተስተናግደው ስለመሆኑ መረጃ ይዘው ከቀረቡ በእነርሱ በኩል ከቤቶች ልማት ጋር ለመነጋገር ያመቻል ሲሉ ገልፀውልናል::

የመምህራኑን አቤቱታ ተከትሎ ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ጥያቄ አቅርበናል:: ለአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኤጀንሲ በ2009 ዓ.ም ቤት በኪራይ መልክ 5000 መምህራን የተሰጣቸው መሆኑ ይታወሳል:: ቤት በኪራይ መልክ ካገኙ መምህራኖች መካከል የተወሰኑት በ2011 ዓ.ም በዕጣ ቤት ደርሷቸዋል:: እነኚህ ሁለት ቤት ማግኘት ስለሌለባቸው አንዱን ቤት ምረጡ ተብለው የመረጡትን ቤት በግዢ ወስደዋል:: ነገር ግን ቤቱን ሲወስዱ ሙሉ ክፍያም ሆነ ቅድመ ክፍያ የከፈሉት በ2011 ዓ.ም የዋጋ ተመን ነበር::

በጊዜው ማለትም በ2011 ዓ.ም «መምህራን የኪራይ ቤት ደርሷቸው በድጋሚ ዕጣ ቢደርሳቸው ቤቱን ማግኘት ያለባቸው በወቅቱ ዋጋ ነው» የሚል መመሪያ ቢኖርም፤ ቤቶች ልማት ኤጀንሲ ግን በአምስት ቀን ውስጥ በ2011 ዓ.ም ታሪፍ እንድንዋዋል አስገድዶናል:: ከውሉም በኋላ ተደጋጋሚ ጥያቄ ብናቀርብም ምላሽ አጥተናል:: በ2013 ዓ.ም ደግሞ ለሌሎቹ መምህራኖች ግን ተመሳሳይ ቤት በ2009 ዓ.ም ታሪፍ ተሰጥቷቸዋል:: ይህ ፍትሐዊ አይደለም:: የሚመለከተውን አካል አነጋግሩልን ሲሉ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አቤቱታ አቅርበዋል::

ጨምረውም ለግማሹ በ2011 ታሪፍ ለግማሹ በ2009 ዓ.ም ታሪፍ ቤቶቹ ለመምህራኖች መተላለፋቸው ምን ያህል ተገቢ ነው? እንደመምህራኖቹ ገለፃ፤ «በ2009 ዓ.ም ታሪፍ አለመዋዋላችን እኛን ጎድቶናል አሁንም እየከፈልን ያለነው ከሌሎች ሰዎች በላይ ነው:: » ሲሉ መምህራኖቹ አቤቱታ አቅርበዋል:: ስለዚህ ኤጀንሲው መምህራኖቹን ለምን በ2011 ዓ.ም በ2009 ዓ.ም ታሪፍ አላስተናገዳቸውም? እነርሱ በዛ መልክ ካልተስተናገዱ ሌሎቹ ማለትም በ2013 ዓ.ም ቤቱን የገዙ መምህራን ለምን በ 2009 ዓ.ም ታሪፍ ተስተናገዱ? በመመሪያው ላይ «በወቅቱ ታሪፍ» የሚለው የ2009 ዓ.ምን ታሳቢ የማያደርግ ከሆነ ወይም በወቅቱ የሚለው የግዢ ውል ሲፈፀም የሚያመለክተው ጊዜን ከሆነ ለምን በተለያየ መልኩ ተስተናገዱ? ከዚህ በኋላ ማድረግ የሚቻለው ምንድን ነው? ስንል ጥያቄ አቅርበናል:: ነገር ግን ጥያቄውን ባቀረብንበት ጊዜ የኤጀንሲው የኮሙኒኬሽን ኃላፊ አዳማ መሆናቸውን ገልጸውልናል:: ከአዳማ ከመጡም በኋላ ጥያቄው እንዲላክላቸው እና ለሚመለከተው አካል የሚያቀርቡ መሆኑን በስልክ ስለገለፁልን ከላይ የጠቀስናቸውን ጥያቄ አካተን በቴሌግራማቸው ልከናል:: ሆኖም ግን ጥያቄውን ከላክን በኋላ በተደጋጋሚ ስልክ ብንደውልም ምላሽ ማግኘት አልቻልንም:: በመሆኑን የቤቶች ልማት ኤጀንሲን ምላሽ አላካተትንም። ሆኖም ግን ኤጀንሲው በቀጣይ ምላሽ ከሰጠን የምናስተናግድ ይሆናል::

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# “ወደ ብራናችን እንመለስ!?”

**ተቃርኗዊ ወግ፤**

ሀገራዊ ኢኮኖሚያችን ጨርቁን ጥሎ ካበደ ሰነባብቷል፡፡ የእብደቱ መጠን ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አይስተዋልም፡፡ የወፈፍታው መንስዔ ምን እንደሆነ እቅጩን ነግረው ቁርጣችንን ያሳውቁናል በማለት በተስፋ የምንጠብቃቸው የሙያው ልሂቃንም እንደ ተራው ዜጋ ሁሉ እብደቱ በፈጠረባቸው ጫና መታመማቸውን እንጂ ሀገራዊው መፍትሔ ይህ ነው ብለው “ገገርዎቻችንን” ሊሞግቱልንም ሆነ ሊያረጋጉን አልቻሉም፡፡ “አውሮፓ በኢኮኖሚው ጣጣ ሲያስነጥስ እኛ በኑሮ ኢንፍሉዌንዛ” እየተቀጠቀጥን እስከ መቼ እንደምንኖር ግራመጋባት ብቻም ሳይሆን እህህታው ራሱ የእለት ቀለባችን እስከ መሆን ደርሷል፡፡

ምሑራኑ በየጓዳቸው፣ “በየዝግ ሴሚናሮቻቸው”፣ በየሚያስተምሩባቸውና “በየምሽቱ መሰባሰቢያቸው” ምን የመፍትሔ ሃሳብ ሲመክሩና ሲቀምሩ እንደሚውሉ ሊነግሩን የማይፈልጉት አንድም ባዕድ ባለሀገር አድርገው ስላገለሉን ነው፤ ወይንም የተራው ሕዝብ ቋንቋ ለገለጻ ስለማይመጥናቸው ነው፡፡ እንዘንላቸው ካልንም የቀመሩት ቲዎሪ አልሠራላቸው ብሎም ሊሆን ይችላል፡፡

በአዘቦቱ ቋንቋችን ቢያስረዱንና ሰበበ ምክንያቱን ቢነግሩን ኖሮ ቢያንስ “ሆድ ይፍጀው” በሚለው ብሂላችን ተጽናንተን ማቃሰቱ ሊቀንስልን ይችል ነበር፡፡ አልፎ አልፎ የሚሰነዝሯቸው መላምቶችና ምክንያቶችም ቢሆኑ የምኞታችንን ሀገራዊ የተራራ ጫፍ ይጠቁሙ ካልሆነ በስተቀር ቁልቁል ዝቅ ብለው የዕለት እንጀራ መሸመቻ የጉልቶቻችንን ቁስል ስለማይነካኩ ከኑሯችን ጥዝጣዜ ፋታ ለማግኘት ያለመቻላችን ሊሰመርበት ይገባል፡፡

የአድአ ጤፍን (ወይ መቅበጥ አሉ!) ሰማይ ላይ ያሽቀነጠረው ምንድን ነው? ከአዋሽ ወንዛችን ፀጋ የሚታፈሰው ሽንኩርትና ቲማቲም ለምን ስማቸው እንጂ መልካቸው ጠፋብን? የሸዋ ቅቤና ምስር፣ የማረቆ በርበሬ፣ የላንቴ ሙዝ፣ የባሌና የአርሲ ስንዴ፣ የቡልጋ ቃሪያ፣ የጎጃም ማር፣ ከወልቃይትና ከሁመራ ሰሊጥ ይመረት የነበረው ዘይት፣ የሐረርና የሲዳማ ቡና ወዘተ. ስለምን በወርቅ መስፈሪያ ሊቸረቸሩ ቻሉ? እያልን ስናጉተመትም “በፈረደበት የምርጫ ካርድ አደራ የጣልንባቸው ሹመኞቻችንና ‹ያስተማርናቸው› ጠቢባኖቻችን” ለዩክሬን-ራሺያ ልቅሶ ሙሾ እያሞሹ እንድናላቅሳቸው ይጎተጉቱናል - “የራሷ እያረረባት…” እንዲሉ፡፡

“የደም ወዛችንና” ገበያው ተኳርፈው ጀርባ ለጀርባ ከተሰጣጡ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ባዕድነታቸውም ሰፍቶ ተራርቀዋል፡፡ ስለዚህም ሽንኩርት የለመደው ድስታችን፣ ምስር የለመደው ጉርሻችን፣ ጥቁርና ማኛ እያልን ስናማርጥ የኖርነው የጤፍ ሬሽናችን፣ ልጆቻችንን የምንደልልበት የመክሰስ “ብጤሌ” ቂጣ ከደሃው ሕዝብ ማጀት እንኳን ሊገኙ ቀርቶ ከእህል በረንዳ ጆንያም ተራግፈው ገበያው በድርቅ ተመትቷል፡፡ “ምድሪቱ አላበቅል ብላ ይሆን (?)” ብለን ስንጠይቅ እንደ ማኅበረሰባዊ የጅል ባህርይ እየታየ ይሳቅብናል፡፡ በርግጥም ብራችን እንደ ስሙ ብር እያለ መክነፍ የጀመረው ዘንድሮ ሳይሆን አይቀርም፡፡ “ስሙን መላእክት አውጥተውለት ይሆን?”

ይሄ ሁሉ ጫና ያነሰ ይመስል የትራንስፖርቱ በጀት፣ የልጆቻችን ት/ቤት ወጭ፣ የአልባሳቱ ሸመታ ጉዳይ ወዘተ. እያልን በመዘርዘር ብሶታችንን መዘርዘሩ በፈጣሪ ድካም ላይ ሌላ ጫና ማሸከም እየመሰለን የባሰ እንዳያመጣብን እየተማጸንን “በሰላም ያዋልከን በሰላም አሳድረን!” ማለቱን መርጠናል፡፡ አስተዳዳሪው መንግሥታችንም ቢሆን “እንዴት መታገስ አቃታችሁ፣ ለምንስ በተስፋ መኖር ተሳናችሁ?” በሚል ቁጣ ሊገስጸን ስለሚችል “መጀን ለሁለቱም!” እያልን “ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል” በሚለው ሀገራዊ ብሂል መጽናናቱ ሳይሻል እንደማይቀር ደምድመናል፡፡

**ብራናችንን እንግለጥ፤**

“ይህ ሁሉ የኑሮ ሸክም እያንገዳገደን ስለምን ሌላ ቅንጡ ጉዳይ አንስታችሁ እንድናማርር ትጎተጉቱናላችሁ” በማለት ዋነኛውን ርዕሰ ጉዳያችንን እንደ “ቅብጠት” የሚያዩ “ሆደ ባሻዎች” እንደማይጠፉ ብንጠረጥርም ጨክነን ወደ ዋናው የመነሻችን መሪ ሃሳብ እናቀናለን፡፡ ምክንያታችን ግልጽ ነው፡፡ ሆዳችንም ተርቦ፣ አዕምሯችንም በጠኔ ተጠቅቶ ሕይወትን መግፋቱ “በቡሃ ላይ ቆረቆር” እንዳይሆንብን በመስጋት የሚሰማ ጆሮ ካለ ሌላኛውንም ብሶታችንን እንዲያደምጥልን በስልጣነ መንበሩ ስም ለመማጠን ነው፡፡ እነሆ ሀገራዊ ብሶታችን፡፡

በሀገራችን ታሪክ የወርቅና የኅትመት ወረቀት ዋጋ ልክ እንደ ዛሬው ተቀራራቢ ደረጃ ላይ ደርሰው የነበረበት ዘመን ኖሮ ከሆነ “ለጸሎትም ለእውቀትም” ስለሚረዳን የሚያውቁ ቢያሳውቁን ከብሶትም ከስህተትም ልንጠበቅ እንችላለን፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር መጻሕፍት እናሳትማለን ብለው የሚወስኑ ደራስያን ሊመሰገኑ የሚገባቸው “እስከ ሞት ድረስ ለሙያቸው ክብር ለመሰዋት እንደሚጨክኑ ጀግኖች” ነው፡፡ ይደልዎ! ብለናል፡፡

ከመቶ ገጽ የሚያንስ መጽሐፍ በመቶዎች የሚቆጠር ዋጋ ሲሰላለት ስናስተውል “መሳቁን ይስቃል ጥርሴ መች አረፈ፤ ልቤ ነው በጣሙን እጅጉን ያዘነ” ብለን እንድናንጎራጉር እንገደዳለን፡፡ ስቅስቅ ብሎ ከብዕር ጋር መላቀሱ እጅግም ስለማይበረታታ ብሶትን አምቆ በእህህታ ጊዜውን መግፋት ይበጃል፡፡ አጽናኝ የሌለበት ልቅሶ መጨጨሁ ስለሚበረታ፡፡

“የኅትመት ዋጋ ናረ!” የሚለው አገላለጽ ትርጉም የነበረው ከዓመታት በፊት ነበር፡፡ ዛሬ ዛሬ “የኅትመት ዋጋ ናረ ሳይሆን ክንፍ አውጥቶ ተሰወረ” ማለቱ ይቀላል፡፡ ለማተሚያ ቤቶች የተነገረው የሚከተለው የሙገሳ ሐተታ እንደትናንቱ በዚህች በእኛይቱ ጨፍጋጋ ጀንበርም “ቁብ” ተሰጥቶት “አሜን!” ይባልለት ከሆነ እርግጠኞች አይደለንም፡፡ ለማንኛውም ፍካሬውን እናስታውስ፡፡

“ይህ ማተሚያ ቤት ነው፡፡ የሥልጣኔ መገኛ፡፡ በጊዜ ምክንያት እንዳይቃወሱ የጥበቦች ሁሉ መድኅን፣ የወሬ ብቻ ሳይሆን የእውነት ማህደር፣ የማያቋርጥ የንግድ እምቢልታ ነው፡፡ ከማተሚያ ቤት ቃሎች ወደ ሩቅ ይበርራሉ፡፡ ንግግርና ድምጽ ብቻ ሆነው እንዳያልፉ፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዳይለወጡ ግን ታርመው ለዘለዓለም እንዲኖሩ፡፡ ክቡር ሆይ! አሁን በተቀደሰ ቦታ ይገኛሉ፡፡ ይኼውም በማተሚያ ቤት ነው፡፡” (አርትስቲክ ማተሚያ ቤት ደጃፍ ላይ “በወርቅማ ቀለም” የተጻፈ ማስታወሻ)፡፡ “ቃሎች ወደ ሩቅ ይበራሉ!” የሚለው አገላለጽ ከይዘቱ ጋር ከሚያያዝ ይልቅ ከኅትመት ዋጋ መክንፍ ጋር ቢተያይ መልካም ሳይሆን የሚቀር አይመስለንም፡፡

ወደ ሰማየ ሰማያት እየጎነ ያለውን የኅትመት ዋጋ በሩጫም ይሁን በተማጽኖ ማስቆም የማይቻል ከሆነ የሀገሬ ደራስያን ያላቸው አንድ ብቸኛ መፍትሔ ብራና ፍቀውና ቀለም በጥብጠው ራሳቸው ድጉሱን በማሳመር እንደ ቀድሞ አባቶች የውስጣቸውን የተሰጥኦ ወላፈን እንዲያበርዱ መምከር ብቻ ነው፡፡ ለየበዓላቶቻችን የሚሰውት የበግና የፍየል መንጋ ሌጦ ገገዝ አጥቶ በየመንገዱ እየተጣለ ስለሆነ የጥሬ ዕቃ ችግር ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ለክፉም ለደጉ ከወረቀት ኅትመት ወደ ጥንቱ የብራና ጥበባችን መመለሱ ግድ መሆኑ ስለማይቀር ለብዕረኞቹ ወዳጆቻችን መሠረታዊውን የብራና አዘገጃጀትና የቀለም ቅመማውን እውቀት እንድንጋራቸው መልካም ሆኖ ታይቶናል፡፡

ብራና የሚሠራው ከጥጃ፣ ከበግ፣ ወይንም ከፍየል ቆዳ (አንጋሬ) መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ደራስያን ወዳጆቻችን ከበሬ ቆዳና ሌጦ ጋር እንዳትታገሉ አደራ፡፡ አንጋሬው በውሃ ተዘፍዝፎ ወይንም በርጥቡ ተወጥሮ ፀጉሩ ከላዩ ላይ ሲላጭና ሲጸዳ ወረቀት መሰል የጽሕፈት ሰሌዳ ይወጣዋል፡፡ “ግዛዋ ሳለ ከደጅሽ፤ ለምን ሞተ ልጅሽ?” እንዲሉ፤ ዘዴው ከደጃፋችን ስላለ የደራሲዎቻችን ጽንስ እንዳይጨነግፍ ብልሃቱ ሳይረዳ አይቀርም፡፡

ቀለም የሚቀመመው ደግሞ እንደሚከተለው ነው፡፡ የተለያዩ ቅጠላ ቅጠሎችን፣ የበግ ቀንድና የበሬ ሸኮና፣ የብራናው ፍቅፋቂ፣ ከሰል፣ የእንጆሪ ፍሬ፣ ቀይ አበባ፣ ቀይ አፈር ወዘተ. አንድ ላይ አጅሎና ዘፍዝፎ በማሰንበት ወደሚፈለገው ደረጃ ሲደርስ በግራር ሙጫ በመቀቀል አንጥሮ በማውጣት መጠቀም፡፡ የቀለማቱን ዓይነት ለመወሰንና ዝርዝር አተገባበሩን ለማወቅ ተጨማሪ ንባብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ከዚያም ብራናውን ዘርግቶ በመቃ ብዕር እየቀሸሩ እንደ ቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን “የጽሑፍ ቅርስ” ማቆየት ነው፡፡

ቅርሱ ከደራሲዎቹ ዕድሜ በላይ መሰንበቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ምናልባትም በሰማይ ቤት ከሀዲስ ዓለማየሁ፣ ከበዓሉ ግርማ፣ ከብርሃኑ ዘርይሁን፣ ከዳኛቸው ወርቁ፣ ከስንዱ ገብሩ፣ ከፊርማዬ ዓለሙና ከሌሎች ነፍስ ሄሮች ጋር መገናኘቱ ስለማይቀር፤ “ለመሆኑ የዘመናችሁ የኅትመት ደረጃ ከምን ደረሰ?” ብለው ቢጠይቁ የሚከተለውን መልስ አስቦ መዘጋጀቱ አይከፋም፡፡

“ኢትዮጵያ ከወረቀት ጋር ተኳርፋ፣ ከዲጂታሉ ዓለም ጋር ከንፋ፣ ለደራሲያዎቿ ክብር ነፍጋ፣ ለጠፊው ዶላር ቅድሚያ ሰጥታ፣ የወረቀት ዋጋን ከወርቅ ዋጋ ጋር አቀራርባ ስለገፋችን የመጻሕፍት ኅትመት ጉዳይ ጉዳዩ አይደለም በማለቷ ወደ ቅድመ አያቶቻችን ዘመን ወደ ጥንቱ የብራና ጥበብ ለመመለስ ተገደናል፡፡” ብሎ መመለሱ አያሳፍርም፡፡ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ቤተ መጻሕፍት በዋና መዲናዋ ያስገነባች ሀገር ለኅትመቱ ጉዳይ ለምን ቸል እንዳለችም ሪፖርት ማቅረቡ ክፋት የለውም፡፡

ማስረጃ ከተጠየቀም በየትኛውም የዓለም ክፍል ተዘውትሮ የማይተገበረውን የመጻሕፍት ኅትመት ግብዓት የታክስ አወሳሰን በማስረጃ ማሳየት ይቻላል፡፡ ኢምፖርት/ዲዩቲ ታክስ 10%፣ ሱር ታክስ 10% (በቅርቡ ይህ ታክስ ቀርቶ ከሆነ እናጣራለን)፣ ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ 3% ለተጨማሪ እሴት ታክስ 15% (ወደ ምርት ሲለወጥ)፣ በአጠቃላይ ድምር ወደ 43% ገደማ ግብር ከመጻሕፍት ግብዓቶች ላይ መንግሥታችን ይቀርጣል ማለት ነው፡፡

በአንድ አብነት ማሳየት ከተቻለም 61X86 ሴ.ሜ ስፋት ባለው አንድ ሪም (400 ወይም 500 ቅጠል የሚይዝ ፓኬጅ) ዛሬ በሀገር ውስጥ ከብር 5000.00 በላይ ደርሷል፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት ይህ ዋጋ ከአራት መቶ ብር በታች እንደነበር ጸሐፊው ያስታውሳል፡፡ ይህ ጸሐፊ የአንጋፋው ማተሚያ ቤት ባልደረባ በነበረበት ዘመን የኅትመት ግብዓቶችን ግዢ ሲያዝ የነበረውን ዋጋ ማስታወስ ተረት ስለሚመስል ያለመጥቀሱ ይበጃል፡፡ ወረቀት ከነዳጅ በልጦ በየዕለቱ ማሻቀቡን ሲታሰብ “ወየው ለነገ ያሰኛል፡፡”

ከውጭ ሀገራት ታትመው የሚገቡ መጻሕፍት ግን ከተጨማሪ ታክስና ከታሪፍ ቀረጥ ነፃ ስለሆኑ በሀገር ውስጥ መጻሕፍትን ከማሳተም ይልቅ ውጭ ሀገር አሳትሞ ማስገባት በእጅጉ ይቀላል፡፡ መጻሕፍትን ውጭ ሀገራት ለማሳተም ብልሃቱ የውሃ መንገድ የሆነላቸው እድለኞችና “ምርጥ የሀገሪቱ በኩራን” ግን “እንኮኮ” እየተባሉ መጻሕፍት ከውጭ ሀገራት እንዲያስገቡ ጎዳናው ይጠረግላቸዋል፡፡

ስለዚህ የሀገሬ ደራስያንና ደራስያት ሆይ! “ዝም አይነቅዝም!” በማለት የብዕራችሁን አንደበት ከመዘጋት ባህላዊውንና ጥንታዊውን የብራና ጥበብ በመጠቀም ከተሰጥኦ ምጣችሁ ለመገላገል ሞክሩ፡፡ “የጨነቀው እርጉዝ ያገባል” ይባል የለ፡፡

ቀድሞውንም ቢሆን የዚህች ሀገር ደራስያንና ደራስያት እንባቸውን ከቀለም ጋር እያጣቀሱ ሲጽፉ መኖራቸው እየታወቀ ወረቀትን በወርቅ ሚዛን እየመዘኑ የፈጠራ ሥራዎቻቸውን እንዲያሳትሙ የፈረደችባቸውን ኢትዮጵያን ትዝብት ላይ የሚጥል ክፉ ድርጊት ነው፡፡ ወርቅና ወረቀት ለመዋቢያ ካልሆነ በስተቀር የአዘቦት ቀናት መገልገያዎች እንደማይሆኑ ብዙ ምልክቶች እየታዩ ነው፡፡ ስለዚህም ብራና ፍቆ የመጻሕፍትን ኅትመት ማስቀጠሉ ውዴታ ብቻም ሳይሆን ግዴታ ጭምር ነው፡፡ “የተሸከመው ከብዶታል፤ እንደገና ይጨምሩበታል” አሉ አበው፡፡

ወላጆችም ቢሆኑ በቀጣዩ ዓመታት የልጆቻቸውን የብራና ድጉስ የመማሪያ መጻሕፍት እንደ ባህላዊ “የቆሎ ተማሪዎች” አሸክመው ወደ ትምህርት ቤት መላካቸው ስለማይቀር ከወዲሁ ዝግጅት ቢያደርጉ ይበጃቸዋል፡፡ የብራና አዘገጃጀቱን ጥበብ ወላጆችም በየቤቱ እንዲማሩ አደራ እንላለን፡፡ “ፊርማና ወረቀት ጠፊ ነው ተቀዳጅ፤ መተማመን ብቻ ይበቃል ለወዳጅ” የሚለው የአበው ትንቢታዊ ብሂል በእኛ ዘመን ተፈጽሞ ማየት “ዕድለኛነትም ይሁን እርግማን” ብቻ ከሁለቱ አንዱ ላይ መውደቁ አይቀርም፡፡ የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርም ለወደፊቱ ስሙ ላይ ማስተካከያ በማድረግ “የኢትዮጵያ የብራና ደራስያን ማኅበር” ወደሚል “ከፍታ” መሸጋገር ግድ ይለዋል፡፡ ይኼው ነው፡፡ ሰላም ይሁን!

# ላልተረጋጋው የሲሚንቶ ገበያ-ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ በተለያዩ አገልግሎቶች ላይ እያጋጠመ ባለው የዋጋ መናር የተነሳ በህብረተሰቡ ላይ የኑሮ ጫና እየተፈጠረ ነው:: ከምግብ ሸቀጦች ጀምሮ በአልባሳት፣ በቤትና በቢሮ ዕቃዎች እንዲሁም በተለያዩ የግንባታ ዕቃዎች ላይ በሚስተዋለው የዋጋ ጭማሪ ሸማቹ እያማረረ ነው:: መንግሥት ገበያን ለማረጋጋት በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል:: በተለይ ደግሞ በሲሚንቶ ምርት ላይ የሚስተዋለው የተጋነነ የመሸጫ ዋጋና የምርት አቅርቦት አለመኖር ጥያቄ ሆኖ ቀጥሏል::

ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣውን የሲሚንቶ ዋጋ መናርና የአቅርቦት እጥረት በተመለከተ የተለያዩ አካላትን አነጋግረን እንደሚከተለው አቅርበናል:: በአዲስ አበባ መገናኛ አካባቢ በሚገኙ የሲሚንቶ መሸጫ ሱቆች ያለውን የገበያ ሁኔታ እንደቃኘነው፣ለወትሮው በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የሚርመሰመሱበትና መተላለፊያ መንገድ የማይገኝበት ይህ የሲሚንቶ መሸጫ አካባቢ እኛ በሥፍራው በተገኘንበት ወቅት ከወትሮው በተለየ መልኩ ጭር ብሏል:: የገበያተኛው እንቅስቃሴ ቀንሷል:: አብዛኞቹ የሲሚንቶ መሸጫ ሱቆችም ዝግ ነበሩ:: ሱቃቸውን የከፈቱ ቢኖሩም የሲሚንቶ ምርት አልነበራቸውም:: በሲሚንቶ መሸጫ ደጃፎቹ ላይ ብዛት ያላቸው ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች ቆመዋል:: አሽከርካሪዎች፣ጫኝና አውራጆች ያለሥራ መቀመጣቸው የሲሚንቶ ንግድ መቀዛቀዝን ያሳያል:: ምክንያቱን ለማወቅ ከመካከላቸው ለማነጋገር ፈልገን በተናጠል ሀሳብ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም:: በአንድ ድምጽ መንግሥት ባወጣው መመሪያ መሰረት ሲሚንቶ አግኝተው መሸጥ እንዳልቻሉና በዚህም እየተቸገሩ እንደሆነ ነው የገለጹት::

በዚሁ ሥፍራ ያገኘናቸው የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት በመሥጠት ሥራ ላይ የተሰማሩት አሽከርካሪ አቶ ሰለሞን ከበደ በሰጡት ሀሳብ፣መንግሥት እየናረ ያለውን የሲሚንቶ ገበያ ለማረጋጋት በተለያየ ጊዜ የሚያወጣቸው መመሪያዎች ስለመኖራቸው ጠቅሰው፣መመሪያው ግን ከሲሚንቶ ነጋዴው በተጨማሪ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ አሽከርካሪዎችን፣ጫኝና አውራጆችን እየጎዳ መሆኑንና እነዚህ አገልግሎት ሰጭዎች ከሶስት ወራት በላይ ያለሥራ ለመቀመጥ መገደዳቸውን አስረድተዋል:: እንደ አቶ ሰለሞን ገለጻ፤ቀደም ሲል በነበረው አሰራር አንድ ሰው ከማምረቻው እስከ ሁለት መቶ ኩንታል ሲሚንቶ መግዛት ይችል ነበር:: በመካከል ላይ መንግሥት የሲሚንቶ ፋብሪካዎችንና ነጋዴውን የሚያገናኝ ወኪሎች (ኤጀንቶች) በማቋቋም ግብይቱ በወኪሎቹ አማካኝነት እንዲከናወን አደረገ:: ወኪሎቹ በተመጣጣኝ ዋጋ በበቂ ሁኔታ እያቀረቡ ባለመሆናቸው የሲሚንቶ ገበያው ቀላል ሊሆን አልቻለም:: ይህ ደግሞ በዘርፉ በተለያየ አገልግሎት ላይ የሚገኘውን ጎድቶታል:: አቶ ሰለሞን መንግሥት ያወጣውን ህግ ተግባራዊ በማያደርጉ ነጋዴዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ተገቢ መሆኑን ቢያምኑም ነጋዴው ሲሚንቶ ባላገኘበት ሁኔታ ህግ ማውጣት ግን ተገቢ አይደለም ሲሉ ቅሬታቸውን ይገልጻሉ::

ለሲሚንቶ ገበያ አለመረጋጋት ሌላው ምክንያት የምርት አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም መሆኑን ያነሱት አቶ ሰለሞን፤ መንግሥት ፋብሪካዎችን መደገፍና ምርታማነታቸው እንዲጨምር ማድረግ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት እንዳለበት ጠቁመዋል:: እንደ አቶ ሰለሞን ማብራሪያ ለሲሚንቶ ምርት ዋናው ግብዓት የከሰል ድንጋይ ነው:: ይህ ግብአት ደግሞ በሀገር ውስጥ በስፋት ይገኛል:: መንግሥት ግብአቱ ጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ በማመቻቸት ችግሩን መቅረፍ ይኖርበታል::

ዋጋውን በተመለከተም እንደየሲሚንቶው አይነት የሚለያይ መሆኑን በመግለጽ፤ ዳንጎቴ ተፈላጊ በመሆኑ ከፍ ባለ ዋጋ እንደሚሸጥ ጠቅሰው፤ መንግሥት አንድ ኩንታል ሲሚንቶ በሰባት መቶ ብር እንዲሸጥ ተመን ያወጣ ቢሆንም፣ገበያ ላይ በአንድ ሺ አምስት መቶ ብር እንኳን ማግኘት እንደማይቻል ነው የተናገሩት:: የማከፋፈል ሚና ያለው ጅንአድ የተባለው ድርጅት በምን ሁኔታ እንደሚያከፋፍል በመከታተልና ቁጥጥር በማድረግ ገበያውን ማረጋጋት እንደሚያስፈልግ ሀሳብ ሰጥተዋል::



የአቡቀለም ኮንስትራክሽን ሥራ አስኪያጅ፣የዲዛይን ማማከርና የግንባታ ሥራዎችን እንዲሁም የግንባታ ቁጥጥር ሥራ የሚሰሩት ኢንጅነር ደሳለኝ ከበደ፤በጉዳዩ ላይ በሰጡት ማብራሪያ የግንባታ ዕቃዎች እንደማንኛውም ምርት የገበያ አለመረጋጋት ይታይበታል:: የገበያ አለመረጋጋቱ ደግሞ ኮንትራክተሮች ቃላቸውን ጠብቀው ግንባታ እንዳያከናውኑ ከማድረግ ባለፈ ለኪሳራ በመዳረጉ የተለያዩ ፕጀክቶች ሥራ እንዳይፋጠንና ሥራውም በወቅቱ እንዳይጠናቀቅ ያደርጋል:: ይህ ደግሞ በሀገር ሀብት ላይ ብክነት ያስከትላል:: ገበያው እየተመራበት ያለው መንገድ ጤናማ እንዳልሆነ ይሰማቸዋል:: ተጠቃሚው የሚፈልገውን ምርት በቀጥታ አያገኝም፤ ቢያገኝም ያለደረሰኝ እንዲገዛ ይገደዳል:: ይህ ደግሞ ከዘርፉ የሚገኘውን የግብር ገቢ ያሳጣል:: እየሆነ ያለው ይህ ነው:: በሲሚንቶ ግብይት ላይ የሚስተዋለው ችግር ዘርፈ ብዙ ነው ይላሉ::

በተለያዩ ምክንያቶች የሲሚንቶ እጥረት በአገሪቷ ላይ ስለመኖሩ የታዘቡት ኢንጅነር ደሳለኝ፤ መንግሥት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተለያዩ መመሪያዎችን ቢያወጣም የሲሚንቶ ገበያን ሊያረጋጋ እንዳልቻለና በዚህ ምክንያትም በርካታ ሥራዎች እየተስተጓጎሉ መሆናቸውን ተናግረዋል:: የሲሚንቶ ግብይት ችግር ላይ ሲወድቅ የአሸዋ፣ የብረት፣ የጠጠርና የሰው ኃይልም ጭምር ከሥራ ውጭ እንዲሆኑ የሚያደረግ በመሆኑ ዘርፈ ብዙ ችግሮች አብረው ይፈጠራሉ:: ስለዚህ የሲሚንቶ ግብይት ላይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በባለሙያ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል:: መንግሥት በቅርቡ በሲሚንቶ ገበያ ላይ ያወጣው መመሪያ በባለሙያ የተጠና ስለመሆኑ ጥርጣሬ እንዳላቸው የሚናገሩት ኢንጅነር ደሳለኝ፤ ለአብነትም መመሪያው ለአንድ ቤተሰብ 15 ኩንታል ሲሚንቶ ብቻ ይፈቅዳል:: ነገር ግን ሲሚንቶ በቤተሰብ ብዛት ሳይሆን፣በፕሮጀክት የሚለካ ነው ብለዋል::

እንደርሳቸው ገለጻ፣15 ኩንታል ሲሚንቶ ሊሠራ የሚችለው ሥራ በጣም ትንሽ ነው:: 15 ኩንታል ሲሚንቶ አገሪቷ አሁን እያከናወነች ካለው ትላልቅ ፕሮጀክቶች አንጻር አቅርቦቱ በቂ አይደለም:: ዋጋውን በተመለከተም ፋብሪካዎች አንድ ኩንታል ሲሚንቶ ከአምስት መቶ እስከ ስድስት መቶ ብር ነው የሚሸጡት:: ይሁን እንጂ ገበያው ላይ መንግሥት ባወጣው የዋጋ ተመን እየተሸጠ አይደለም:: በመሆኑም ከፋብሪካዎች በላይ በንግድ ሰንሰለት ውስጥ መሀል ላይ ያሉት ደላሎች ተጠቃሚ ሲሆኑ፣መጨረሻ ላይ ያለው ገዢው ደግሞ በከፍተኛ መጠን ተጎጂ ይሆኗል::

ኢንጅነር ደሳለኝ፤ በዘርፉ እየተስተዋለ ያለውን ችግር ለመቅረፍና የሲሚንቶ ገበያን ለማረጋጋት መፍትሔ ይሆናል ያሉትን ሃሳብ ሲያካፍሉም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ቀዳሚው መፍትሔ እንደሆነ አስገንዝበዋል:: ለዚህም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች እንዲስፋፉና በብዛት ማምረት እንዲችሉ ማበረታታት አስፈላጊ እንደሆነ በመመከር በተለይም በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች አነስተኛ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች መኖራቸውን ጠቁመዋል:: እነዚህን አነስተኛ የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግና ምርቱን በማብዛት ገበያውን ማረጋጋት ይቻል ይሆናል እንጂ በየጊዜው በሚወጣ የገበያ ቁጥጥርና መመሪያ ውጤት ማምጣት አይቻልም ብለዋል::

ለሲሚንቶ ምርት ዋና ዋና ግብዓቶች ናቸው የሚባሉት ጅብሰም፣ የድንጋይ ከሰልና ሌሎችም በአገር ውስጥ ስለመኖራቸው የጠቀሱት ኢንጅነር ደሳለኝ፤ የኃይል አቅርቦትን በተመለከተም የዓባይ ግድብ ኃይል እያመነጨ እንደሆነ አንስተው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር እያወጡ ህንጻ የሚገነቡ ሰዎችን ወደ ሲሚንቶ ፋብሪካ ማምጣት ያስፈልጋል:: እነዚህን ጥሬ ዕቃዎች ተጠቅመው ሲሚንቶ ፋብሪካ መገንባት ቢችሉና ከአገር አልፎ ለምስራቅ አፍሪካ መትረፍ እንደሚቻል ተናግረው የመንግሥት ትኩረት መሆን ያለበት ምርቱን ማብዛት ላይ ነው ብለዋል::

የሲሚንቶ ዋጋ ረጅምና ጤናማ ባልሆነ የግብይት ሰንሰለት አማካኝነት ያለአግባብ እየናረ ስለመሆኑና በዚህም ምክንያት በአገራዊና ማህበረሰባዊ እድገት ላይ ፋይዳ ያላቸው የግንባታ ፕሮጀክቶች ተስተጓጉለዋል:: በመሆኑም ሰንሰለቱን ለማሳጠርና ገበያውን ለማረጋጋት በሚል የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ በየደረጃው ካሉ የንግድ ዘርፍ መዋቅሮችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የተለያዩ ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቷል::

መንግሥት በዘርፉ የሚስተዋለውን ችግር ለመቅረፍ የሚያደርገው ቁጥጥርና ክትትል ምን ውጤት አስገኘ፤ የተወሰዱ እርምጃዎችስ እንደምን ያሉ ናቸው፤ አሁን ያለው የሲሚንቶ ገበያስ እንዴት እየተመራ ነው ስንል ላነሳነው ጥያቄም የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ቁምነገር እውነቱ፤ የሲሚንቶ ገበያን ለማረጋጋት በሚል ከሐምሌ 5 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ መመሪያ በማዘጋጀት ወደ ተግባር መግባቱን አስታውሰው፤ በመመሪያው አተገባባርም መንግሥት እጁን በማስገባት ፋብሪካዎችም በመንግሥት መመሪያ እንዲገዙ ሆኖ ዋጋ አቅርበው መመሪያው ተግባራዊ መሆን እንደቻለ አስረድተዋል::

ይሁንና መመሪያውን ተግባራዊ ማድረግ ያልቻሉና በአቋራጭ መክበር የሚፈልጉ የፋብሪካ ባለቤቶችን ጨምሮ አንዳንድ አከፋፋዮች በመኖራቸው የሲሚንቶ ገበያ መረጋጋት እንዳልቻለ አንስተው፤ ማህበረሰቡ ሲሚንቶን በተጋነነ ዋጋ እየገዛ እንደሆነ ነው የተናገሩት:: መንግሥት ያወጣውን መመሪያ ተግባራዊ ማድርግ ያልቻሉትንም ግብረኃይል ተቋቁሞ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ እየተወሰደ ስለመሆኑ ያነሱት ኃላፊዋ፤ ከሰሞኑ ብቻ በሶስት ክፍለ ከተሞች ላይ በተደረገ ቁጥጥርና ክትትል 22 ሺ ኩንታል ሲሚንቶ ተወርሶ መንግሥት ባወጣው የሲሚንቶ ዋጋ ተሸጦ ለመንግሥት ገቢ መደረጉን ተናግረዋል:: ከዚህ በተጨማሪም የታሸገባቸውና እርምጃ የተወሰደባቸው ፋብሪካዎች ስለመኖራቸውና ግብረኃይሉ መሰል ሥራዎችን እየሠራ እንደሆነ አንስተዋል::

አሁን ያለውን የሲሚንቶ ገበያ አስመልክተውም እየታየ ያለው የዋጋ ንረት ከምርት እጥረት ጋር ተያይዞ የመጣ እንዳልሆነና የመንግሥትን መመሪያ ጠብቀውና ተከትለው የሚሠሩት ጥቂቶች በመሆናቸው ያነሱት ኃላፊዋ፤ ለአብነትም እንደ አዲስ አበባ ከተማ መመሪያውን በጠበቀ መንገድ በሁለት ክፍለ ከተሞች በሚገኙ ማከፋፈያዎች ብቻ እንደሚከፋፈል ነው ያስታወሱት:: እነዚህ ማከፋፈያዎችም ፒያሳ የሚገኘው ኤግልድ ኮርፖሬሽንና የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ናቸው::

ከእነዚህ ሁለት አከፋፋዮች ውጭ ማንም ነጋዴ እንደፈለገ ሲሚንቶ መሸጥ የተከለከለ እንደሆነ መመሪያው ያዛል:: ነገር ግን የተፈቀደላቸውና የመንግሥትን መመሪያ መሠረት በማድረግ ለሚሸጡት ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መንገድ እንዲሸጡ ተደርጓል:: ይህም ማለት የመንግሥትና የግል አልሚዎችን ግንባታ እየፈጸሙ ላሉት ቀጥታ ከፋብሪካ በር ላይ እንዲገዙ ነው የተደረገው:: ምክንያቱም በርካታ ግንባታዎች በሲሚንቶ እጥረት በየቦታው እየተስተጓጎሉ በመሆናቸው ነው::

በቁጥር አነስተኛ መጠን ያለው ሲሚንቶን ለሚፈልጉ ተጠቃሚዎች ማለትም ለቀብርና መሰል ጉዳዮች ግለሰቦች ሲፈልጉ ሲሚንቶ እንዳያጡ ባልተጋነነ ዋጋ እንዲያገኙ የተዘጋጁ መሸጫ ቦታዎች በየአካባቢው ይገኛሉ:: ነገር ግን በእነዚህ አካባቢዎች የሚቀርበው የሲሚንቶ ዋጋ እጅግ የተጋነነ ስለመሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መረጃ እየደረሰው ሲሆን፤ መረጃውን መሰረት በማድረግም ጥቆማው በተሰጠባቸው አካባቢዎች በመዘዋወር የእርምት እርምጃ መወሰዱንና በቀጣይም ቁጥጥሩና ክትትሉ በከፍተኛ ሁኔታ አጠናክሮ በማስቀጠል ገበያውን ለማረጋጋት ይሠራል ብለዋል::

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ተማሪዎች ለምን ይወልዳሉ?

**ዋለልኝ አየለ**

የ10ኛ እና የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ሲሰጥ ፈተና ላይ የሚወልዱ እናቶች ያጋጥማል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የ10ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ስለቀረ ክስተቱ የሚታየው 12ኛ ክፍል ላይ ነው። ብዙ ጊዜ አገር አቀፍ ጉዳዮች ላይ (ለምሳሌ ምርጫና ፈተና) የሚወልዱ እናቶች ዜና ይሆናሉ።

የዘንድሮ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች መውለድ ግን ከባለፉት አንፃር ቁጥሩ የጨመረ ይመስላል። ዋናዎቹን መገናኛ ብዙኃን ጨምሮ በማህበራዊ የትስስር ገጾች ከብዙ ዩኒቨርሲቲዎች የወሊድ ዜና ተሰምቷል። ለዚያውም ገና መግባት እንደጀመሩ እና በመጀመሪያው ዙር ፈተና ነው። በሁለተኛው ዙር ፈተናም የሚከሰት ከሆነ ቁጥሩ ይጨምራል ማለት ነው። ልጅ መውለድ ፀጋ ስለሆነ ለእናቶችና ለቤተሰቦቻቸው ልጆቻቸውን አሳድገው ለቁም ነገር እንዲያበቁ እንመኛለን።

የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች መውለድ አጀንዳ ስለሆነ የትዝብቴ መነሻ አደረኩት እንጂ የጽሑፉ ዓላማ ምን ያህል የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ወለዱ የሚለውን አይደለም። ሽፋን የማግኘት ዕድል ስላለው በብዙዎች ዘንድ ተዳረሰ እንጂ ከ4ኛና 5ኛ ክፍል ጀምረው የሚወልዱትን ቤት ይቁጠራቸው።

ዋናው ጥያቄ ‹‹ተማሪዎች ይወልዳሉ?›› የሚለው ነው። አዎ! ለምን ይወልዳሉ?

ይህ ክስተት በብዛት የሚስተዋለው በገጠሪቱ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ነው። የሰሞኑ ዜናዎችም ይህንኑ ያረጋግጣሉ። የገጠርን ሕይወት በመኖር ስለማውቀው እየታዘብኩት የኖርኩትን ልናገር።

ልጆቹ ገና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ ነው እንዲያገቡ የሚደረገው። የአንዳንዶቹ የትዳር አጋሮች እስከ ሁለተኛ ደረጃ ወይም እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ያስተምሯቸዋል፤ የአብዛኞቹ ግን እንዲያቋርጡ ነው የሚያደርጓቸው። እነዚህን አግብተው ትምህርት የሚያቋርጡ ሴቶች ማንም ልብ አላላቸውም። እነዚህ 12ኛ ክፍል ፈተና ላይ ወልደው የዜና ሽፋን ያገኙት በጣም ጥቂቶች ናቸው።

11ኛ፣ 10ኛ፣ 9ኛ... ክፍል ሁሉ የሚወልዱ አሉ። ሲወልዱ ከአራት እስከ ስድስት ወር ያህል ክፍል ውስጥ አይገቡም። የማጠቃለያ ፈተና ላይ ሊገኙ ቢችሉ ነው፤ ለዚያውም ከወለዱ በኋላ ትምህርቱን ያላቋረጡት ማለት ነው። እንዲህ እንዲህ እያሉ አገር አቀፍ ፈተና ላይ ይደርሳሉ። ስለዚህ ለትምህርቱ በቂ ጊዜ አልሰጡም ማለት ነው።

አሁንም ‹‹ተማሪዎች ለምን ይወልዳሉ?›› ብለን እንጠይቅ። የሚወልዱት ወደውና ፈቅደው ሳይሆን ተገደው ነው። ተገደው ሲባል በአስገድዶ መድፈር አይነት አይደለም። የቤተሰብ እና የአካባቢ ዘመድ አዝማድ ጫና ይደረግባቸዋል። ቤት ውስጥ ቁጣ ይበዛባቸዋል። ‹‹ትምህርትሽን አታቋርጭም፤ አግቢና ተማሪ›› እያሉ ያታልሏታል።

ካገባች በኋላ ደግሞ ልጅ መውለድ እንዳለባት ግፊት ይደረግባታል። የትዳር አጋሯ ደግሞ እሷን ለመያዝ ሲል እንድትወልድ ይፈልጋል፤ ልጅ የትዳር ማፅኛ ነው ተብሎ ይታመናል። እንዲህ እንዲህ እያሉ ታረግዛለች፤ ከዚያም ትምህርቱን ታቋርጣለች ማለት ነው። በኖርኩበት አካባቢ በዚህ ሁኔታ ትምህርት ያቋረጡ ብዙ ሴት ልጆችን ስለማውቅ ነው።

ይህን ትዝብት ሳጋራ አንድ ነገር ልብ ይባልልኝ። ሁሉም ተማሪዎች ተገደው ነው የሚያገቡ ማለቴ አይደለም፤ እያወራሁ ያለሁት ስለአብዛኞቹ ስለሆነ ነው። የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ክስተትም መነሻዬ እንጂ መደምደሚያ አይደለም። ወደውና ፈቅደው እንዲሁም የማግባትና ልጅ የመውለድ ደረጃ ላይ የደረሱ ሴቶች አሉ። እነርሱ የራሳቸው የሆነ መተዳደሪያ ያላቸው ወይም የትዳር አጋራቸው በቂ መተዳደሪያ ያለው ናቸው። ግን የሴት ልጅ ሕይወት በዚህ መገደብ የለበትም።

አንዳንድ ሰዎች ተማሪ ሆኖ መውለድን እንደ ትልቅ ነውር የሚያዩት አሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ እንደ ትልቅ ስኬት የሚያዩት አሉ። ስኬትም ነውርም አይሆንም።

ነውር አይደለም ስንል፤ ልጆቹ የሚወልዱት ከትዳር ውጭ ሲወሰልቱ አይደለም፤ በወግና ሥርዓት ያገቡ ናቸው። ልጅ መውለድም መታደል ነው፣ ፀጋ ነው። ሌላው ነውር የማይሆንበት ምክንያት ተገደውና ጫና ተደርጎባቸው ስለሚሆን ነው።

ስኬት አይደለም፤ ስንል ደግሞ ተማሪዋ መድረስ ያለባት ደረጃ ላይ እንዳትደርስ ስለሚያደርግ ነው። የሴት ልጅ ሕይወት ገና በልጅነቷ ልጅ ታቅፋ መኖር አይደለም። ተመራማሪ የሚያደርግ ደረጃ ላይ መድረስ አለባት። ልጅ እየወለዱም ይቻላል ይባል ይሆናል፤ ግን ይለያያል። ልጅ ለመውለድ ቢያንስ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በሚገባ መጨረስ ያስፈልጋል። በሰርግ፣ እርግዝና እና በወሊድ ጊዜያት ከትምህርት ርቀው ነው የሚቆዩ፤ ለዚህም ነው አብዛኞቹ የሚያቋርጡት።

አንዳንዶቹን ፎቶ ላይ ስናያቸው ትልልቅ ይመስሉን ይሆናል፤ ግን በተጎሳቆለ እና በገጠር ሕይወት ውስጥ ስለሚኖሩ እንጂ በዕድሜ ትልቅ ሆነው አይደለም። ስለዚህ የሴቶች ጉዳይ ተቋማት እና የትምህርት ተቋማት ጉዳዩን ሊያጠኑት ይገባል።

ሌላው ልብ ሊባል የሚገባው ነገር በብዙ አካባቢዎች ለትምህርት የሚሰጠው ዋጋ ዝቅተኛ እየሆነ ነው። በተለይም አንዳንድ ወላጆች ‹‹የእገሌ ልጅ ተምራ የት ደረሰች?›› በማለት ተመርቀው ያልተቀጠሩ ልጆችን ይጠቅሳሉ። ወይም አገር አቀፍ ፈተና ላይ ውጤት ያልመጣላቸውን ልጆች በመጥቀስ እንደ እነርሱ ከመሆን በሚል እንዲያገቡና ልጅ እንዲወልዱ ያደርጓቸዋል። እውነታው ግን እነዚያ የአካባቢያቸው ልጆች ውጤት ያልመጣላቸው ለትምህርት በቂ ጊዜ ስላልተሰጣቸውና ክትትል ስላልተደረገላቸው ነው።

ሌላኛው እውነታ በዚህ ዘመን ያልተማረ ምንም መሥራት እንደማይችል አለመታወቁ ነው። በ20 እና 10 ዓመታት ውስጥ እንኳን ያለውን ልዩነት ልብ እንበል። ከዛሬ 20 ዓመት በፊት 12ኛ ክፍል መድረስ ትልቅ ደረጃ ነበር። ዛሬ ግን የመጀመሪያ ዲግሪ ራሱ ምንም ነው። ምክንያቱም የዓለም ነባራዊ ሁኔታ እየተቀየረ ነው። ከዛሬ 20 ዓመት በፊት የወረቀት ደብዳቤ የሚያነብ ሰው የተማረ የሚባል ነበር፤ ዛሬ ግን በረቂቅ የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች ነው።

በዚህ ስሌት ከሄድን ከዛሬ 20 ዓመት በኋላ ደግሞ የት ላይ እንደምንሆን አይታወቅም። ስለዚህ መማር ሥራ ለመቀጠር ብቻ ሳይሆን ለመኖር ራሱ የግድ ይሆናል ማለት ነው። መማር ለመኖር የግድ መሆኑን ማህበረሰባችን ልብ ያለው አይመስልም። ለዚህ ነው ልጆች በልጅነታቸው እንዲወልዱና ከትምህርት እንዲያቋርጡ የሚደረገው። ይህን የትምህርት ተቋማት ሊሰሩበት ይገባል።

የሴቶች መብት ላይ የሚሰሩ ተቋማትም የቀሚስ ማጠር እና መርዘም ላይ ከሚጨቃጨቁ ያለፍላጎታቸው የሚዳሩ ልጆች ላይ ሊሰሩ ይገባል። መብት የሚባለው ነገር የሚገባቸው መጀመሪያ የትምህርት ዕድል ሲያገኙ ነው። የሴት ልጅ ዕጣ ፋንታ ሚስት መሆን እና ልጅ ወልዶ ማሳደግ ብቻ እስከሚመስል ድረስ ያለዕድሜያቸው የሚዳሩ ልጆች አሉ።

በአጠቃላይ ሴቶች ልጆች ላይ የሚደረገው ጫና አሁንም አልተቀረፈም። አገር አቀፍ ፈተናዎች ላይ ለዜና የበቁት ልጆች ማሳያ ናቸው፤ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች (አንደኛ ደረጃ ጨምሮ) የሚከሰት ነው። የሚከሰተውም ትልልቅ እናቶች ሆነው ሳይሆን በልጅነታቸው እየተዳሩ ነው፤ በፍላጎታቸው ሳይሆን በአካባቢ ጫና ነው።

ስለዚህ መንግሥትም ሆነ የሲቪክ ተቋማት በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩ ይገባል!

# ዓለም አቀፍ



## ከጎርፍ የሸሹ ናይጄሪያውያንን የያዘች ጀልባ በመስጠሟ 76 ሰዎች ሞቱ

በናይጄሪያ ደቡብ ምሥራቅ በምትገኘው የአናምብራ ግዛት በደረሰ የጀልባ መስመጥ አደጋ ቢያንስ 76 ሰዎች መሞታቸው ተዘገበ።ቢያንስ 80 ሰዎችን አሳፍራ ስትጓዝ የነበረችው ጀልባ አርብ ዕለት በአናምብራ ግዛት ኦግባሩ አካባቢ ስትደርስ ሰምጣለች።

አብዛኛዎቹ ሟቾቹ ሴቶች እና ህጻናት ሲሆኑ አካባቢያቸው በጎርፍ በመጥለቅለቁ ከአካባቢው ሲወጡ አደጋው እንደገጠማቸው ተነግሯል።ፕሬዝዳንት ሙሐመዱ ቡሃሪ “በአሳዛኙ” አደጋ ለተጎጂዎች ቤተሰቦች መጽናናትን ተመኝተዋል።

በተጨማሪም የሃገሪቱ የውሃ ትራንስፖርት ስርዓት የደህንነት እርምጃዎች እንዲከለሱ አዘዋል። የአደጋ ጊዜ ሠራተኞች የጠፉትን ለማግኘት ሁሉንም ነገር ማድረግ አለባቸውም ብለዋል።

ቡሃሪ አክለውም የመንግሥት ተቋማት “በእነዚህ የመጓጓዣ ጀልባዎች ላይ የደኅንነት ፕሮቶኮሎችን እንዲፈትሹና ተመሳሳይ አደጋዎች እንዳይከሰቱ እንዲከላከሉ” ጠይቀዋል።

የአገሪቱ መገናኛ ብዙሃን እንደዘገቡት በጀልባው ላይ የተሳፈሩት ሰዎች በአከባቢው ወደሚገኘው ንኮዎ ገበያ በማምራት ላይ ነበሩ። ባለስልጣናት ጀልባዋ የሞተር ችግር ካጋጠማት በኋላ ድልድይ ገጭታ ሰምጣለች ብለዋል።

በብሔራዊ ድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ኤጀንሲ የደቡብ ምስራቅ አስተባባሪ የሆኑት ቲክማን ታኒሙ ለኤኤፍፒ የዜና ወኪል እንደተናገሩት “የውሃው መጠን በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ለፍለጋ እና ለማዳን ሥራው በጣም አደገኛ ነው” ብለዋል።

የአናምብራ ገዥ ቻርለስ ሶሉዶ በበኩላቸው አደጋው ነዋሪውንም ሆነ የግዛቱን መንግስትም ያስደነገጠ መሆኑን ጠቅሰው ለተጎጂ ቤተሰቦችም ሃዘናቸውን ገልጸዋል።

በናይጄሪያ የጀልባ አደጋዎች የተለመዱ ናቸው። ለአብዛኛዎቹም ከልክ በላይ መጫን ወይም ዝቅተኛ የደህንነት እርምጃዎች በምክንያትነት ማቅረባቸውን የዘገባው ቢቢሲ ነው።



## በሊቢያ በ15 ስደተኞች ላይ አሰቃቂ ግድያ መፈጸሙን ተመድ ገለጸ

በሊቢያ በ15 ስደተኞች ላይ የተፈጸመውን አሰቃቂ ግድያ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አውግዟል።ግዲያው በተቀናቃኝ አዘዋዋሪዎች መካከል በተፈጠረ ግጭት የተፈጸመ ሊሆን ይችላል ተብሏል፡፡

በያዝነው ዓመት ብቻ 216 ሰዎች የሜድትራኒያን ባህርን ለማቋረጥ ሲሞክሩ መሞታቸው የዓለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት ገልጿል፡፡ድርጊቱ ጥገኝነት ጠያቂዎች ምንም አይነት ዋስታና እንደሌላቸውና ጥበቃ እንደማይደረግላቸው የሚያሳይ ነው ብሎታል ተመድ ባወጣው መግለጫ።

ባለፈው አርብ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በየዓመቱ ወደ ጣሊያን የባህር ዳርቻ ለመድረስ ለሚፈልጉ አስፈላጊ መነሻ በሆነችው በሊቢያዋ ሳብራታ የባህር ዳርቻ 15 አስከሬኖች መገኘታቸው ተገልጿል።ነገሩ አሰዛኝ የሚያደርገው ደግሞ የተገኙት አስከሬኖች 11ዱ የተቃጠሉ እንዲሁም አራቱ ከተቃጠለችው ጀልባ ተጥለው የተገኙ መሆናቸው ነው ተብሏል፡፡

የሊቢያ ባለስልጣናት ሁሉንም ወንጀለኞች ለማምጣት ፈጣን ፣ ገለልተኛ እና ግልጽ ምርመራ እንዲያደርጉ አጥብቆ ያሳሰበው የተመድ “ትክክለኛው ሁኔታ ገና በትክክል ባይታወቅም ግዲያው በተቀናቃኝ አዘዋዋሪዎች መካከል በተፈጠረ ግጭት የተፈጸመ ሊሆን ይችላል” ብሏል።

ይህ አሳዛኝ ክስተት “በሊቢያ ውስጥ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሚያጋጥሟቸውን ከለላ እጦት እንዲሁም በአደገኛ ህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች እና የወንጀል መረቦች የሚፈጸሙትን ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት መኖሩ የሚያሳይ ነው” ሲልም ነው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የገለጸው።የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙሀን እንደዘገቡት፤ ፍልሰተኞቹ በአብዛኛው ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራት የመጡ ናቸው፡፡

እንደፈረንጆቹ በ2011 የሙዓመር ጋዳፊን መንግስት መውደቅ ተከትሎ የተፈጠረው ትርምስ ሊቢያን ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ፣ የአረብ ሀገራት እና ከደቡብ እስያ በጣሊያን በኩል አቋርጠው ወደ አውሮፓ ለመድረስ ለሚጓጉ በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ስደተኞች ተመራጭ መንገድ አድርጓታል።

እነዚህ ስደተኞች አደገኛውን የሜዲትራኒያን ባህር ለማቋረጥ ሲሞክሩ በህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች እጅ እንደሚወድቁና በዚህም ለተለያየ አደጋ እንደሚጋለጡም የተመድ መረጃዎች ያመለክታሉ።በያዝነው የፈረንጆች ዓመት ብቻ 14 ሺህ 157 ስደተኞች በቁጥጥር ስር ውለው ወደ ሊቢያ መመለሳቸው እንዲሁም ቢያንስ 216 ሰዎች ሜዲትራኒያን ባህርን ለማቋረጥ ሲሞክሩ መሞታቸው የዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (አይኦኤም) በሪፖርቱ ይፋ አድርጓል።

እንደፈረጀቹ ጥቅምት 3 ቀን 2013 በርካታ ኤርትራውያን የሚገኙባቸው 350 ስደተኞች በላምፐዱሳ ባህር ዳርቻ የሞቱበት አሳዛኝ አደጋ አይዘነጋም። አደጋው ከደረሰ ባሳለፍነው ሳምንት 9 ዓመት መሆኑን የዘገባው አል ዐይን ነው።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ዘገር ነቅናቂው ባለቅኔ

ግርማ መንግስቴ

ገሞራው በበርካታ መገለጫዎች የሚታወቅ ሲሆን የኪነጥበብ አድባር፣ ታላቁ የኢትዮጵያ የጥበብ ዝግባ፣ የለውጥ ሀዋርያ፣ ሞገደኛው ብእረኛ፣ "ባለመርዘኛው ብዕርተኛ"፣ ያልተነገረለት ባለ ቅኔ ... ወዘተርፈ ጥቂቶቹ ናቸው።

"የገጣሚና ባለቅኔ ኃይሉ (ገሞራዉ ዜና እረፍት)" በሚልዕ ርእሰ ዜና የታወጀውና በዶች ቬሌ "ባለፈዉ ዕሑድ በስደት በሚኖርበት ስዊድን ሐገር ያረፈዉ የኢትዮጵያዊው ባለቅኔ የኃይሉ ገብረዮሐንስ (ገሞራው) የቀብር ሥነ-ሥርዓት ሰሞኑን እንደሚፈጸም ወዳጆቹ አስታወቁ። ኃይሉ በኢትዮጵያ ዘመናይ ሥነ-ፅሁፍ ሥመ ጥር ከነበሩ ደራሲዎች አንዱ ነበር። ይሁንና በስራዎቹ ምክንያት በተደጋጋሚ እስር እና እንግልት ተዳርጎ በመጨረሻም ሕይወቱ በስደት አልፋለች።" የሚለው። እንዲሁም "ታላቁ የኢትዮጵያ የጥበብ ዝግባ ኃይሉ ገብረዮሐንስ (ገሞራው) (እ. ኤ. አ. 1935 – 2014) አረፈ" (Ethiopian Poet Hailu Gebreyohannes (Gemoraw) passed away ሲሉ የዘገቡለት የውጭ ሚዲያዎችም በርካታ ናቸው) ዜና እና የመሳሰሉት ለኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይም ለአድናቂዎቹና የኪነጥበብ ቤተሰቦች የተነገሩ፤ እ.ኤ.አ በ1935 በአዲስ አበባ የተወለደውን ኃይሉ ህልፈተ ሕይወት "ሃሎ" ያሉ ... ከባድ መርዶዎች ነበሩ።

### ትምህርትና ኃይሉ

በአዲስ አበባ (ኢሲኤ አካባቢ) የተወለደውና በልጅነቱ የቤተክህነት ትምህርት እየተከታተለ ያደገው ኃይሉ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ከተማረ በኋላ፣ በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የስነ መለኮት ትምህርት ተከታትሏል (በሥላሴ ቤተ ክርስቶያን በድቁና ያገለግል የነበረው ሲሆን፤ በልጅነቱ የተካነበት የግእዝ ቋንቋ ከቀሳውስቱ ጋር እንደፈለገ በቅኔ እንዲግባባ እንዳስቻለው ይነገርለታል።)

ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ስር የሚገኘውን መንፈሳዊ ኮሌጅ ተቀላቀለ። ይሁን እንጂ፣ ከመንፈሳዊ ትምህርት ይልቅ ፍልስፍና ቀልቡን ስለገዛው ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ተቀይሮ የሚወደውን ሥነጽሁፍ ማጥናት ቀጠለ።

በዩኒቨርሲቲ ቆይታው በግዕዝ፣ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የተለያዩ የስነጽሁፍ ስራዎችን በማቅረብ ታዋቂነትን አትርፏል፡፡ በዩኒቨርሲቲው ይካሄድ በነበረ የግጥም ውድድር አሸናፊ በሆነበት "በረከተ መርገም" ነጎድጓዳማ ግጥሙም ይታወቃል፡፡ በተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ በስፋት ይካፈል የነበረው ገጣሚው፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ከዩኒቨርሲቲው ተባርሯል፡፡

በኮሌጅ ቆይታው ወቅት በሥነ-ፍጥረት፣ በስነሕይወት፣ በሡብአዊነት እና በእነኝህ ዙሪያ ባሉ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ምርምር ማድረጉ፤ በሥነ-ጥበብ ፋካሊቲ የሥነ-ቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ እንደገባም በግዕዝ፣ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች በሚጽፋቸው ጥልቅ፣ ህብረ-ምርምራዊ አባባሎች ችሎታው በዩኒቨርስቲው ተማሪዎች እና ሠራተኞች ዘንድ ስሙ ገኖ የነበረ መሆኑም ይነገራል።

"በረከተ መርገም" ባመጣበት "ጦስ" ምክንያት ከዩኒቨርሲቲ ቢባረርም፣ ባገኘው የትምህርት እድል መሰረት ወደ ቻይና በማምራት በቤጂንግ ዩኒቨርሲቲ የቻይናን ሥነጽሁፍን ማጥናት ጀመረ። ይሁን እንጂ፣ በዚሁ ነቋሪና ለእውነት ሟች ብእሩ ምክንያት ከዛም ተባረረ። የዶክትሬት ማሟያ ስራውንም አቋረጠ።

### ገሞራውና ስራዎቹ

ከገሞራው በርካታና ተወዳጅ ሥራዎች መካከል (አብዛኞቹ በስደት በኖረበት፣ በስዊዲን አብያተ መጻሕፍት ዝርዝር የሚገኙ ናቸው) በረከተ መርገም (ግጥምና ቅኔ) - ይህ ስራው በ1980 ዓ.ም በስዊድን በድጋሚ ታትሞለታል፤ ፍንደታ (ግጥምና ቅኔ)፤ ቅኔ ለዘመን (ግጥምና ቅኔ)፤ ዘር ነው በሽታዋ (ግጥምና ቅኔ)፤ እናትከንና አባይ (ግጥምና ቅኔ)፤ ዜሮ ፊታውራሪ (ግጥምና ቅኔ)፤ የመንጎሌ ጥሪ (ግጥምና ቅኔ)፤ ቆርጠሃት ጣልልኝ (ግጥምና ቅኔ)፤ መንገድ ስጡኝ ሰፊ (ግጥምና ቅኔ)፤ የሽግግር ደባ (ልቦለድ)፤ አንድነት ግጥም (እማማ አፍሪካን ለማስታወስ)፤ የበሰለው ያራል፤ በናቴኮ ሴት ነኝ፤ ወይዘሪት ወይዘሮ፣ ርጉም ሐዋሪያ፣ ድግሪማ ነበረን፣ Robot፣ ጎጆዬ ጠላቸኝ እስና ሌሎችም የሚገኙ ሲሆን፤ በአንባቢያን ዘንድ የማይታወቁለት በርካታ ስራዎች እንዳሉትም ይነገራል።

የ1953 መፈንቅለ መንግሥት ሙከራን ተከትሎ "ሲያል" በሚል ርዕስ ግጥም ፃፈ (ይህ ዘመን በንጉሡ የምስጢር ፖሊስ ሃይል "ባለመርዘኛው ብዕርተኛ" በሚል ስም ይጠራበት የነበረ ወቅት ነው)። እ.ኤ.አ. በ1963 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ በዓል ላይም "ዋንነስ" በሚል ርእስ አንዲት አነስተኛ ግጥም በእንግሊዝኛ አዘጋጅቶ በበዓሉ ላይ ለተገኙት መሪዎች ስለ አፍሪካዊ አንድነት ያለውን ሀሳብ አካፍሏል።

ገሞራው አማርኛ፣ ግዕዝ፣ እንግሊዝኛ፣ ቻይንኛ፣ ኖርዌጅኛ እና ስዊድሽኛ የፃፋቸው ስራዎች አሉት። በተለይ ስለ ማዖ የፃፈው የቻይንኛ ግጥም ከሁሉ የተለየ አድናቆትን አትርፎለታል። መሠረታዊ የቻይንኛ ቋንቋ ጥናቱን እንዳገባደደም የቻይንኛ-አማርኛ መዝገበ-ቃላት እና ሌላም የቻይንኛ-እንግሊዝኛ ሐረጋት መጽሐፍ አዘጋጅቷል።

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት፣ ኋላም አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ገብቶ በመምህርነት አገልግሏል።

### እሱና ዘመነኞቹ

የአማርኛ ግጥም በጽሑፍ ውሎ ተገኝቷል ከሚባልበት 4ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በርካታ ውጣ ውረዶችን በማሳለፍ እዚህ ደርሷል። የሩቁን እንኳን ትተን፤ የቅርቡን፣ ከአብዮቱ ጋር የተያያዘውን ብንመለከት ገፅታው የተለያየ ነው።

ጥናቶች (ለምሳሌ ደበበ ሰይፉ፣ 1974) እንዳረጋገጡት የአማርኛ ግጥም በአብዮቱ ዋዜማ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ወቅት ነበር። ከአብዮቱ ማግስት ጀምሮ ደግሞ እየቀነሰ መጣ። በአብዮቱ ዋዜማ (ቅድመ '66) በርካታ ነባርና ወጣት ገጣሚያን የጨቋኝ መደብ አባላት በህዝቡ ላይ ሲያደርሱት የነበረውን ጭቆና አንፀባርቀዋል። በአብዮቱ ዋዜማ የነበረው አለመረጋጋት፣ የህዝቡ መራራ ስሜቶች፣ አመፅና የተቃውሞ ጥሪዎች ሥነግጥም (በተለይም የአማርኛ) እንዲዳብር ምክንያት ሆነዋል። የዳኛቸው ወርቁ "እምቧ በሉ ሰዎች"፣ የአበራ ለማ "ኩል ወይስ ጥላሸት"፣ የተስፋዬ ገሰሰ "መተከዣ"፣ የሀይሉ ገብረዮሀንስ "በረከተ መርገም" እና "ፍንዳታ"፣ የመንግስቱ ለማ "ባሻ አሸብር ባሜሪካ"፣ የመስፍን ወልደማሪያም "እንጉርጉሮ" ... እና ሌሎች በርካቶችም በአብዮቱ የመጀመሪያ ሁለት አመታት ውስጥ የታተሙ ቢሆንም አብዛኞቹ ግጥሞች በአብዮቱ ዋዜማ የተገጠሙ ናቸው። በ1969 ኣ.ም የወጣው የሰይፈ መታፈሪያ ፍሬው "የተስፋ እግር ብረት"፣ በ1971 የወጣው የአሰፋ ገብረማሪያም "የመስከረም ጮራ" ... ድህረ አብዮት ቢታተሙም አብዛኞቹ ግጥሞች ቅድመ አብዮት የተገጠሙ ናቸው።

ከዚህ የምንረዳው ገሞራውና ዘመነኞቹ ለአማርኛ ሥነግጥም እድገት ብቻ ሳይሆን ለነበረውም ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ከፍተኛ ትግል ሲያደርጉ የነበረ መሆኑን ነው።

ታላቁ የኪነጥበብ ሰው ከሌሎች ዘመነኞቹ (ለምሳሌ፣ ዮሐንስ አድማሱ (እስኪ ተጠየቁ)፤ ኢብሳ ጉተማ (ኢትዮጵያዊ ማነው?) እና የመሳሰሉት) ለየት የሚያደርጉት በርካታ ጉዳዮች ያሉ ሲሆን፤ ጨቋኝና ጭቆናን ያጋለጠበት የ"በረከተ መርገም" ገጣሚ መሆኑ፤ ለረዥም አመታት ቻይና መኖሩ "(በሚጽፋቸው ጽሑፎች ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ የቻይና ምሳሌዎችን (አባባሎችን ጭምር) ይጠቅሳል)፤ በስደት (ስዊድን) መኖሩ፤ በስደት ላይ እያለም በአገሩ ጉዳይ ላይ ሳያሰልስ በተለያዩ መጽሔቶች (በ"ጦቢያ"፣ "ኢትዮጵ" እና የመሳሰሉት) እና ጋዜጦች ላይ መጻፉ (ከቻይና ምሳሌዎችና አባባሎች ጋር በተያያዘ፣ እነዚህንም በስራዎቹ ውስጥ አጠቃቀሙን ያስተዋሉ ሰፊ ፅንሰ ሀሳብ የሆነውን፣ "paper tiger"ን በምሳሌነት የሚጠቅሱለት ሲሆን ትርጓሜውም zhǐlǎohǔ ሆኖ፤ በራሳቸው ቀላል አገላለፅ ሲቀመጥ (simplified Chinese: 纸老虎; traditional Chinese: 紙老虎) ማለት እንደ ሆነ ይናገሩለታል።)

ገሞራውና ተፅእኖ ፈጣሪ፤ አብዝተውም ተጠቃሽ አንጓዎቹ

እነዚህ፣ በተለያዩ ስራዎቹ ውስጥ የሚገኙት የገሞራው አንጓዎች በተለያዩ ስራዎች ውስጥ ለተለዩ ጉዳዮች ማሰሪያ፣ መልእክቶች ማጉያና ማድመቂያ፤ አስተሳሰቦችን መትከያና ማፅደቂያ ያገለግሉ ዘንድ በብዙዎች አብዝተው የሚጠቀሱ ሲሆን ይህም በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በቃል ንግግር ወቅትም ተዘውታሪዎች ናቸው።

በመንቃት ላይ ባሉ ፍጡራን መካከል
ህይወት የምንለው እንደጥሬ እህል፤
በኑሮ ምጣድ ላይ ቢቆላ ቢማሰል
የበሰለው ያራል! ጥሬው እስኪበስል
* * *
መርዝን በመርዝነት ስለመርዝ መመረዝ
የመርዝን ለመርዙ በመርዙ ማስመረዝ!!!

(ይህ ግጥሙ በበጎ ካልታዩለትና ካሳሰሩት ስራዎቹ አንዱ ነው።)፡፡

* * *



መኖር ሕልው ነው - በመንፈስ በአካል፣
ያላዩኝ ወገኖች ቢሉም ሞቷል አልፏል፣
ለሚፎክሩትም - ፀረ ሰብ ተንባላት!
ግልጡ አካሌ ይሸው ነፍሴን ግን አይገኟት!።
* * *
ነገሩ አልሆን ብሎ ሁኔታው ሲጠጥር፣
ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር።
* * *
ነቅናቂው ነቅንቆ ቢያነቃንቀው፣
የተነቃነቀው ነቅንቆ ጣለው።
* * *
ከጥንት ጀምሮ ስናየው የኖርነው
ሲነድ ሲቃጠል የሚሥቅ እሳት ነው።

እነዚህ በተለያዩ ስራዎቹ ውስጥ የሚገኙና በአንባቢያብ ላይ በከፍተኛ ደረጃ በጎ ተፅእኖ የፈጠሩ ሲሆኑ፤ እንደ አንድ ወጥ ስራ የገሞራው መለያና መታወቂያ ሆኖ በውክልና ገሞራውን የሚያስታውሰውና ቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበረበት ጊዜ የፃፈው፣ የእውቀት አድማሱን ጥግ (እነዛን ሁሉ ፈላስፎች ሳያውቃቸው አይፅፍምና) ያሳየበት፣ በአንድ ስንኝ እስከ ስምንት ገረጋትና እስከ 48 ቀለማት ድረስ በመጠቀም (በስንኝ ስልቱ) ጎልቶ የታየበት ደግሞ ባለ 17 ገጹ "በረከተ መርገም" ነው። (ይህንን፣ በ1957 ዓ.ም የተፃፈ ግጥም ኦሪጂናሉ ካልተገኘ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 50ኛ አመቱን ሲያከብር ባሳተመው "የኮሌጅ ቀን ግጥሞች" ስብስብ ውስጥ ያገኙታል።)

ይህ ስራው "በተማሪዎች የለውጥ እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ የነውጥ መንፈስ የፈጠረ የግጥምና የቅኔ ማእበል ነው።" የሚል ስምምነት ላይ የተደረሰበት ሲሆን፤ እነሆ እስካሁንም ይህ አስተያየት ምንም ሳይሸራረፍ እዚህ፣ አሁን ያለንበት ዘመን ላይ ደርሷል።

የዚህ ግጥም ሌላው ተፅእኖ አንጋፋው ጋዜጠኛና ደራሲ (የ"ነፃነት" እና "ከጣራው ሥር")፤ በአሁኑ ሰአት እየሩሳሌም የሚኖረው ዜናነህ መኮንን ‹‹በረከተ መርገም››ን የሚሞግት) ‹‹በረከተ ራዕይ›› በሚል ርዕስ የግጥም ሲዲ በ1999ዓ.ም ከማውጣቱ ጋር ሊታይ የሚችል ነው። ("በረከተ ራዕይ" ተስፋን – ነግን ለማየት እንድንታትር የሚያመላክት ‹‹መልዕክተኛ›› ሥራው ነው፡፡)

በገሞራው ተፅእኖ ስር ከወደቁት አንድ የሆነው በእውቀቱ ስዩምም "በረከተ መርገም"ን ወደ አሁኑ ዘመንና ትውልድ ያሻገረ ሲሆን፤ ለዚህም በ"በረከተ መርገም" የሰየመው ግጥሙ ተጠቃሽ ነው። ይህ የሚያሳየን የገሞራው ሥነፅሁፋዊ ተፅእኖ በቀላሉ የሚታይ አለመሆኑን ነው። በኪነጥበብ ከበባት፣ ኮንፈረንሶች፣ ዜማዎች ...፤ እንዲሁም በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ በሚከናወነው በእለት ተእለት ንግግርም እንደዛው።

ሌላውና ገሞራውንና ቤተቡን ለየት የሚያደርገው ጉዳይ፣ እውቀት፣ ምሁርነት፣ አገር ወዳድነት ... በቤተሰብ፣ የዘር ሀረግ ... እስኪመስል ድረስ መሆኑ ሲሆን፤ ይህም ገሞራው የእውቁ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ዶ/ር እጓለ ገብረየሆንስ ወንድም መሆኑ ነው። (ዶ/ር እጓላ "የከፍተኛ ይትምህርት ዘይቤ" ደራሲ መሆናቸውን ልብ ይሏል።) አሁን ከቴክኒካዊ ጉዳዮች በመውጣት ወደ ማጠቃለያችን እንሂድ።

### ገሞራውና ስደት

ቻይና ትምህረርቱን በመከታተል ላይ እያለ የዶክትሬት ዲግሪውን ማሟያ ጽሑፍ ለማዘጋጀትም "The Influence of Anarchism on Chinese Literature: With a particular focus put on the case "Ba-Jin" በሚል ርዕስ ምርምሩን ጀመረ። ይህ ርዕስ ግን በራሱ ጣጣ አመጣበት። የዲግሪ ማሟያ ጽሑፉ በቻይና ሥነ-ጽሑፍ ላይ ፖለቲካዊ ትችት የሚያዥጎደጉድ ይሆናል ብለው የፈሩት የቻይኛ ባለሥልጣናት በእጁ የሚገኙ ሥራዎችን እንዲያስረክብና በአስቸኳይ ሀገር ለቆ እንዲወጣ አዘዙት። ቀይ ሽብር ይካሄድባት ወደ ነበረችው ሀገሩም መመለስ የሚታሰብ አልነበረም። ስለዚህም በአምነስቲ እና በዩ.ኤን.ሲ.ኤች. አር ትብብርም ወደ ኖርዌ፣ ኦስሎ አመራ። በኦስሎም የፃፋቸውን ስራዎች ማሳተምም ሆነ የቻይንኛ ቋንቋ ጥናትህን መቀጠል አትችልም ስለተባለ፣ አሁን ሕይወቱ ወደ አለፈባት፣ ወደ ስዊድን በመሄድ በስቶክሆልም መኖር ጀመረ።

### ማጠቃለያ

በኢትዮጵያና ሃበሻ ተኮር ዝግቶች ላይ በመታደም ከእንባ ጋር ግጥሞቹን ያነባል። ሳይኖረው ዘወትር ለወገኖቹ ይረዳል። ረዥም የስደት ዘመኑን በግለኝነትና የብህትውትና ኑሮን ኖሯል። ወደ ጥበብ በማድላቱ ምክንያት ኑሮ ገፍቶታል፤ ግን የሃገር ወዳድና የጥበብ አድናቂዎቹ እገዛ አልተለየውም - እስከ ህልፈቱ። ይህ ‹‹ከዘመኑ ቀድሞ የተፈጠረ›› ሲሉ ቡዙዎች የሚስማሙበት ብዕረኛ ከሀገር ናፍቆት፣ ስደት፣ ባይትዋርነትና፣ ብቸኝነት ባሻገር ለበርካታ ዘመናት አብሮ በኖረው የስኳር ህመምና ተያይዥ ችግሮች ተጎድቷል። እዛ፣ ስዊድን።

ኃይሉ ገብረዮሐንስ (1928 — 2007 ዓ.ም) ከዚህ በፊት የታተሙትንም ሆነ ያልታተሙትን ሥራዎቹን አቀነባብሮ በቅጽ በቅጽ በማድረግ በቅደም ተከተል ይታተሙ ዘንድ አቅርቦ፣ ይህንን ለማድረግም የቅርብ አድናቂዎቹ ገንዘብ አዋጥተው በእንቅስቃሴ ላይ እያሉ ነው በድንገት ያረፈው። ይህ ምኞቱም በወዳጅ ዘመዶቹ እውን ይሆናል ተብሎ እየተጠበቀ ነው።

የሕይወት ዘመኑን በውጭ አገራት (ስደት) ያሳለፈው ገጣሚ ኃይሉ ገ/ዮሃንስ፤ ባደረበት የስኳር ህመም ምክንያት በሚኖርባት ስዊድን በሚገኝ ሆስፒታል ህክምና ሲከታተል ቆይቶ፣ እሁድ (ጥቅምት 30 ቀን 2007 ዓ.ም) በመኖሪያ ቤቱ በተወለደ በ79 አመቱ ከዚህ አለም በሞት ተለየ፡፡

ይሁን እንጂ፣ ስም ከመቃብር በላይ ነውና ገሞራው ትቶልን በሄዳቸው ስራዎቹ አማካኝነት እነሆ አብሮን አለ።

# ስፖርት





## አንጋፋው የስፖርት ሰው አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ አረፉ

ቦጋለ አበበ

ታዋቂው የስፖርት ሰው አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። አቶ ፍቅሩ ባደረባቸው ህመም በሚኖሩበት ሃገር ፈረንሳይ በህክምና ሲረዱ ቆይተው ከትናንት በስቲያ ሌሊት ላይ በ88 ዓመታቸው ማረፋቸውን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አረጋግጧል።

በኢትዮጵያ የስፖርት ታሪክ በስፖርት ጋዜጠኝነት፣ ቀዳሚ በመሆን እና በአለም አቀፍ ተቋማት በስፖርት እና በተለያዩ ዘርፎች በሀላፊነት እንዲሁም በከፍተኛ ሙያተኛነት በማገልገል እውቅናን የተጎናፀፉት የአንጋፋው የስፖርት ሰው አቶ ፍቅሩ ስርአተ ቀብር መቼና የት እንደሚፈጸም እስከ ትናንት አመሻሽ የተገለጸ ነገር የለም።

አቶ ፍቅሩ በህይወት በነበሩ ጊዜ በተለይም የመጀመሪያው የስፖርት ጋዜጠኛ ከመሆናቸው በተጨማሪ የኢትዮጵያ ስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር እንዲመሰረት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። በኢትዮጵያ የስፖርት ጋዜጠኝነት ሙያ እንዲጎለብት በማድረግም ለበርካታ ወጣቶች አርአያ መሆን ችለዋል። ከስፖርት ጋዜጠኝነት ሙያቸው ጎን ለጎን በታላላቅ በአለም አቀፍ ተቋማት በሰሩባቸው ወቅቶች አገራቸውን በማስጠራት ታላላቅ ሽልማቶችን ለመቀበል በቅተዋል።

‹‹የፒያሳ ልጅ›› መፅሀፍ ደራሲ የሆኑት አቶ ፍቅሩ፣ በኢትዮጵያ የስፖርት ጋዜጠኝነት ታሪክ ፈር ቀዳጅ ከሚባሉ ግለሰቦች አንዱ ከመሆናቸው ባሻገር የእግር ኳስ ጨዋታን በቀጥታ በሬዲዮ በማስተላለፍ የመጀመርያው ኢትዮጵያዊ ነበሩ። አቶ ፍቅሩ በቀጥታ የሬድዮ ስርጭት ያስተላለፉት ጨዋታም እኤአ በ1957 የኢትዮጵያና የሱዳን ብሔራዊ ቡድኖች አዲስ አበባ ስቴድየም ላይ ያደረጉት ጨዋታ እንደነበር በታሪክ ማህደሮች ተሰንዶ ይገኛል። ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ በተለያዩ ቋንቋዎች የስፖርት ዘገባዎችን በማቅረብም ይታወቃሉ። ኦሊምፒክ፣የአለም ዋንጫ፣ የአፍሪካ ዋንጫና የአለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናን በመሳሰሉ ታላላቅ የአለማችን የስፖርት መድረኮች ላይ በአካል በመገኘት የተለያዩ ዘገባዎችን ሰርተዋል። ከጋዜጠኝነት ህይወታቸው ባሻገር በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፣ በካፍ እና በኦሊምፒክ ኮሚቴ አመራርነት ፣ በጋዜጠኞች ማህበር መስራችነት እና አመራርነትም ከፍተኛ ግልጋሎት ሰጥተዋል።


በኢትዮጵያ የስፖርት ጋዜጠኝነት ታሪክ ስማቸው በቀዳሚነት የሚነሳው ጋዜጠኛና ደራሲ ፍቅሩ ኪዳኔ የተወለዱት በ1927 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ሲሆን የአንጋፋው ቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ክለብ የተመዘገቡ የልብ ደጋፊ መሆናቸውን የህይወት ታሪካቸው ያስረዳል።

አቶ ፍቅሩ በተለይም የኢትዮጵያ የስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር በ1961 ዓ.ም ሲመሰረት የመጀመሪያው ፕሬዝደንት የነበሩ ሲሆን በብስክሌት ፌዴሬሽን፣ቴኒስ ፌዴሬሽን እና በኢትዮጵያ የኦሊምፒክ ኮሚቴ በዋና ፀሐፊነት፣ በኢትዮጵያ የእግር ኳስ ፌዴሬሽን የሕዝብ ግንኙነት በመሆን አገራቸውን አገልግለዋል።

በዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ እና የአፍሪካ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ውስጥም በአመራርነት ፣ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) የቀድሞ ፕሬዝደንት የነበሩት የኢሳ ሃያቱ አማካሪ እንደነበሩም ይታወሳል።

ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ ኑሯቸውን በፈረንሳይ መዲና ፓሪስ ያደረጉት አቶ ፍቅሩ በሀገሪቷ ለሚገኘው ዕለታዊ የስፖርት ጋዜጣ ለኪፕ እና ሳምንታዊ የእግር ኳስ መጽሔት ፉትቦል ፍራንስ፣ ዶቼቬሌ (የጀርመን ድምፅ) እና ሌሎች የአለም አቀፍ ታዋቂ መገናኛ ብዙሃን መስራት የቻሉት ጋዜጠኛና ደራሲ ፍቅሩ ኪዳኔ የአንድ ልጅ አባት ሲሆኑ ሁለት የልጅ ልጆችንም አይተዋል።

የአቶ ፍቅሩን ከዚህ አለም በሞት መለየት አስመልክቶ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እንዲሁም ሌሎች የስፖርት ተቋማትና የስፖርት ቤተሰቦች የተሰማቸውን ሃዘን ገልጸዋል። አዲስ ዘመን ጋዜጣም በአንጋፋው የስፖርት ሰው አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ ህልፈት የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን እየገለፀ ለቤተሰባቸው ፣ ለሙያ ባልደረቦቻቸው እና ለስፖርት ቤተሰቡ መፅናናትን ይመኛል።





## የጨረታ ማስታወቂያ

በቂርቆስ ክ/ከተማ የብሄራዊ አፀደ ህፃናትና የመ/ደ/ት/ቤት 2015 በጀት ዓመት የሚያስፈልጉ የደንብ ልብስ፣ የስፖርት መምህር ትጥቅ፣ አላቂ የትምህርት ዕቃዎች፣ አላቂ የቢሮ ዕቃዎች የጽዳት ዕቃዎች፣ የቢሮፈርኒቸሮች እና ኤሌክትሮኒክስ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

**በዚህ መሰረት በጨረታው መሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች ማሟላት ያለባችሁ ቅድመ ሁኔታዎች፡-**

1. በመንግሥት የአቅራቢ ስም ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች በተሰማሩበት የሥራ መስክ የታደሰ ንግድ ፈቃድና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች ቫት ተመዝጋቢ ስለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
4. የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ 50/ሃምሳ ብር/ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 /አስር/ ተከታታይ የሥራ ቀናት በብሔራዊ አፀደ ህፃናትና የመ/ደ/ት/ቤት ለዚህ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ እስከ 10ኛው ቀን 4፡00 ድረስ ብቻ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የሚያገለግል የመጫረቻ ዋጋ ብር ለደንብ ልብስ 1500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር ብቻ) ለአላቂ የትምህርት ዕቃዎች እና የቢሮ ዕቃዎች 4,500 (አራት ሺህ አምስት መቶ ብር ብቻ) ለጽዳት ዕቃዎች እና ህትመት 2000 (ሁለት ሺህ ብር ብቻ) ለቋሚ ዕቃዎች እና ኤሌክትሮኒክስ 500 (አምስት መቶ ብር ብቻ) በብሔራዊ አፀደ ህፃናትና የመ/ደ/ት/ቤት ስም ሲፒኦ(CPO) በማሰራት ኮፒው ውስጥ በማስገባት ማረጋገጫቸውን ከማወዳደሪያ ሰነዶቻቸው ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
6. ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ10ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡ 30 ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት ቢሮ ቁጥር 02 ይከፈታል፡፡ ቀኑ በዓል ወይም ከሥራ ቀን ውጪ ከሆነ በሚቀጥለው ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይሆናል፡፡
7. ተጫራቾች ለሚያቀርቧቸው ዕቃዎች ናሙና (ሳምፕል) ማቅረብ አለባቸው፡፡
8. ተጫራቾች አንድ ተጫራች በሰጠው ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ መስጠት የለባቸውም፡፡
9. ከገዙት የጨረታ ሰነድ ውጪ ተሞልቶ የመጣ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡
10. ተጫራቾች የገዙትን ሰነድ ኮፒ በማድረግ እና የተጠየቁትን መረጃ ኮፒ እና ዋናውን ለየብቻ በማሸግ ሁለቱንም በጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
11. የሚሞላው ዋጋ ቫትን ጨምሮ መሆን አለበት፡፡
12. ት/ቤቱየተሻለአማራጭካገኘጨረታውንሙሉበሙሉወይምበከፊልየመሰረዝመብቱየተጠበቀነው፡፡

**አድራሻ-** አዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል በስተጀርባ ብሔራዊ አፀደ ህፃናትና የመ/ደ/ት/ቤት፡፡

**ስልክ ቁጥር፡- 0115-57-37-84**

**በቂርቆስ ክ/ከተማ የብሔራዊ አፀደ ህፃናትና የመ/ደ/ት/ቤት**

## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር 001/2015

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የቂሊንጦ ቁ.2 የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት በ2015 ዓ.ም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ግዢዎች ለመፈፀም አቅራቢ ድርጅቶችን በጨረታ እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡፡

1. የደንብ ልብስ
2. አላቂ የቢሮ እቃዎች
3. አላቂ የትምህርት እቃዎች
4. የተለያዩ የፅዳት እቃዎች
5. ልዩ ልዩ መሳሪያዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

**በዚሁ መሠረት፡-**

1. በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያላቸው፣
2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
3. በመንግሥት እቃ አቅራቢነት የተመዘገቡና የምስክር ወረቀት ያላቸው፣
4. የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣
5. ተጫራቾች የማይመለስ 100 /አንድ መቶ/ ብር ብቻ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን ከት/ቤቱ ከፋይናንስ ክፍል ቢሮ ቁጥር 3 መግዛት ይችላሉ፡፡
6. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ በገዙት ሰነድ ላይ ባለው የዋጋ ማቅረቢያ ቦታ ላይ ስርዝ ድልዝ ሳይኖረው በመሙላት ማህተም ስምና ፊርማቸውን በማኖር ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዘወትር በሥራ ሰዓት ከ2፡30 እስከ 11፡00 ሰዓት ድረስ በት/ቤቱ ፋይናንስ ክፍል ቢሮ ለጨረታ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፡፡
7. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ የሚውል /CPO/ሁለት ፐርሰንት/ 2% በማሰራት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ጨረታው የሚከፈተው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው በወጣ በ11ኛው የሥራ ቀን በ4፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡

ት/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡- አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ማረሚያ ፊት ለፊት**

**ሞባይል 0913082316 /0925002398/0982004775/**

**ቂሊንጦ ቁ2 የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት**